ፍኖተ መንግሥት

ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ አንድ መጽሐፍ እሰጣለሁ!

በመርዓዊ ንጉሤ/ፓስተር/

2004 ዓ.ም

የሽፋን ስዕል ማስታወሻ

ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። ይህች አያሩላትም ናት፤ በአሕዛብም መካከል አደርጌአታለሁ፥ ለገርችም በሐሪያዋ አሉ ሕዝ 5:5

በሽፋኑ ላይ ያለው ምስል፣ የኢየሩሳሌም ከተማ ፎቶ ሲሆን፣ ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ የተነሣችው ነው። ከፊት ለፊት ጥንታዊቷ ኢየሩሳሌም፣ ጎላ ብላ ስትታይ፣ ዘመናዊቷ ምሥራቅ ኢየሩሳሌም በርቀት ትታያለች። ባለ ወርቃማ ጉልላቱ መስኪድ «ዶም አፍ ዘ ሮክ» ይባላል። አይሁዳውያን «አሁን መስኪዱ ያለበት ስፍራ፣ ቀድሞ የሰለሞን ቤተ መቅደስ የነበረበት ነው» በማለት የይገባኛል ሙግት አላቸው። ሙስሊሞች ግን «ነብዩ መሐመድ አንድ ሌሊት ወደ ገነት የተነጠቁበት ስፍራ በመሆኑ፣ ከመካና መዲና ቀጥሎ ሦስተኛው ቅዱስ ስፍራችን ነው» በማለት የአሁዳውያኑን ሙግት አምርረው ይቃወማሉ። በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት መርማሪዎች ደግሞ «ስፍራው ወደፊት በምድር አንደሚገለጥ የሚጠበቀው የሐሰተኛው ክርስቶስ መቀመጫ መሆኑ ስለማይቀር፣ አንድ ቀን የአይሁዳውያኑ ቤተ መቅደስ በስፍራው መሠራቱ አይቀርም» ይላሉ። ከዚህ አንጻር ወደፊት በዚህ ስፍራ የሚሆነው ነገር እጅግ ያጓጓል፣ ያሳቅቃል፣ ያስጨንቃል።

ይህቺ «ፍኖተ መንግሥት» የተሰኘችው መጽሐፍ፣ ይዤንና ከዚህ ጋር የተያያዙ አያሌ ጉዳዮችን ያካተተች በመሆኑ፣ ዛሬውኑ የራስዎ ያድርጓት፣ እስከ ፍጻሜውም በትጋት ያንብቧት።

አነሆ ፍኖተ መንግሥት...
በመርዓዊ ንጉሤ
2004፡ ዓ.ም

5 መጻሕፍት፣ 28 ምዕራፎች፡ 464 ገጽ

አሳታሚ

መርዓዊ ሥላሴ ንጉሤ 2004

© መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው

ትዛ፣ ሌይአውትና ግራፊክስ - መርዓዊ ንጉሤ

አድራሻ

ፓስታ ሳጥን ቁጥር 952

ስልክ 251 911 215882

ኢሜል e-mail

selihom2002@yahoo.com,
merawinigussie03@gmail.com,
Facebook- merawi nigussie

መጽሐፍ ፩

መንግሥትህ ትምጣ

ከገጽ 19 እስከ ገጽ 72

መጽሐፍ ፪

ፍጥተ መንግሥት

ከገጽ 73 እስከ ገጽ 126

መጽሐፍ ፫

ጸንሒልና ሰባው ሱባኤ

ከገጽ 127 እስከ ገጽ 182

መጽሐፍ ፬

የሰሙኑና ጠዲፌት የሚሆነው

ከገጽ 183 እስከ ገጽ 334

መጽሐፍ ፭

ስስቴሊል፣ ስሙርፓና
መካከሰኛው ምሥጢቅ

ከገጽ 335 እስከ ገጽ 462

ዝርዝር ማውጫዎቹ ከየመጻሕፍቱ አንጻር ተዘርዝረዋል

ልዩ ምስጋና

አነሣስቶ ያስጀመረኝ፣ አስጀምሮም ያስፈጸመኝ ልዑል እግዚአብሔር ነው፤ ተነግሮ ስለማያልቅ ስጠታው፣ የተመሰገነ ይሁን::

አበርክቶት

ይኼን መጽሐፍ፣ ለእናቴ ቀለሚ ወልደሚካኤልና እና ለአባቴ ንጉሤ ኃይለማሪያም፣ ሳበረከት በታላቅ አክብሮት ነው::

የዘወትር ናፍቆቴና ጸሎቴ፣ እግዚአብሔር ያዘጋጀላችሁን ረጅምና ዘላለማዊ ሕይወት ትወርሱ ዘንድ ነው::

መጽሐፉን ቀድሜ በማንበቤ እጅግ አትርፈአለሁ፤ እንደሚኒጥር ኳስ፣ እዚህም እዚያም እየረገጥኩ እውቀው የመሰለኝን ብዙ ነገር፣ መስመርና ተዳባይ ታሪኮችን ተከትዬ እንዳውቃቸው ስላገዘከኝ ጌታ በፀጋ ይባርከህ:: ከዚህ በኋላም መሰሉን ድንቅ መጽሐፍ ከአንተ እጠብቃለሁ::

ስዩም ተፈራ /አርቲስት/

ይህ የመጋቢ መርዓዊ «ፍኖተ መንግሥት» በጣም ጥሩ መጽሐፍ ነው፤ በነገረ ፍጻሜ ላይ ሰፊ ዕውቀት ይሰጣል:: የዘመኑን ማለቅ ፍንትው አድርጎ ያሳያል:: ሰው ሁሉ ቢያነበው እወዳለሁ

በቀለ ወልደኪዳን /ፓስተር/

ከረጅም ጊዜ ጀምሮ፣ ከሙዚቃ በተጨማሪ በሌሎች መንፈሳዊ ርዕሰ ጉዳዮች ተገቢ ዕውቀት እንዲኖረኝ አፈልግ ነበር፤ ይኼ መጽሐፍ ለእያሌ ጥያቄዎቼ መልስ ያገኘሁበት ከመሆኑም በላይ ብዙ ዕውቀት አስጨብጦኛል:: መጽሐፉን በጥንቃቄ የሚያነብ ሰው፣ የተኛ መንፈሱ ይቀሰቀሳል:: ወገቡ የታጠቀ፣ መብራቱ የበራ ለመሆን የሚያስችለውን ዕውቀት እንደሚጨብጥም እርግጠኛ ነኝ:: ለሰው ሁሉ ያለኝ ምክር፣ በኋላ እንዳይቆጫችሁ ይህን መጽሐፍ አንብቡ የሚል ነው::

አዳነ አስናቀ፤ የሙዚቃ ባለሞያ ከኢ.ኦ.ፕ በሙዚቃ የመጀመሪያ ድግሪ፤

ፍኖተ መንግሥትን አንብቤ ስጨርስ «መንገዶች ሁሉ ወደ ሮም ይወስዳሉ» የሚለው የሮማውያን የዓለም ገዢነት መፈክር ትዝ አለኝ፤ እናም በልቤ እንዲህ አልኩ «መንገዶች ሁሉ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የከብር ፍጻሜ ያደርሳሉ::»
መጽሐፏ የትናንትና ፍኖት በተደራጀ መልኩ የቀረበባት ከመሆኗ አንጻር፣ ዛሬ እንደዋዛ ሰምቼ ወይም አንብቤ አልፋቸው የነበሩ ከሰተቶች፣ ከመንግሥቱ ፍኖት ጋር ያላቸውን ትስስር እንዳስተውልና ነገ፣ የመንግሥቱ የከብር ፍኖት ፍጻሜ ምን ሊሆን እንደሚችል በንቃት እንድጠብቅ አድርጋኛለች:: ስለዚህ ማንበብ የሚችሉ ሁሉ ሊያነቧት ይገባል እላለሁ::

ሳሙኤል ሙሉጌታ፤ የኢት. የሥነ መለኮት ድኅረ ምረቃ ተማሪ

የወደፊቱን ለመረዳት፣ ያለፈውንና የአሁኑን ማጤን ተገቢ ነው:: «ፍኖተ መንግሥትም» መጽሐፍ ቅዱስን መነጽሯ አድርጋ፣ በዘመናት የተከሰቱና የነላ ፋይዳ ያላቸው የዓለም ታሪኮችን በማስቃኘት፣ ዘመነ ፍጻሜን ለማስረዳት በትክክለኛው ወቅት መጥታለች:: መጋቢ መርዓዊ፣ አዕማድ ከሆኑት የከርስትና ትምህርቶች መካከል ትምህርተ-ፍጻሜን እንዲህ ባለ መልኩ በማቅረቡ በእውነት እግዚአብሔር ይባርከው:: መጽሐፏ ለመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶችና ለአብያተ ክርስቲያናት፣ እንዲሁም ስለመጪረሻው ዘመን ማወቅ ለሚፈልግ ሁሉ የምትሆን ናት::

ይመስገን ጌታ ተሾመ፡ የኢት. የሥነ መለኮት ድኅረ ምረቃ ምሩቅ

ውጥ አሳብ፣ የከርስቶስን መንግሥት ማዕከል ያደረገ፣ ታሪካዊ ማመሳከሪያን ያሟላ፣ ድንቅ መጽሐፍ ሲሆን፣ የመጨረሻውን ዘመን በማመላከት አማኞች ከልባቸው ማራናታ እንዲሉና ተዘጋጅተው እንዲኖሩ በአንከሮ የሚያሳስብ የሕይወት ደዉል ነው።

አሸብር በላይነህ፣ /ፓስተር/ Bሐ.D. የመጽሐፍ ቅዱስ
ሠራዊት ዓ.ኢ.ቤ.ክ. ሃይ ዌይ ቻፕል መጋቢ

ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ጉዳይ ዘለቅ ብሎ የተጻፈውና ይጋግማችሁ አንብቡኝ፣ አንብቡኝ የሚለው ይኼ የመጋቢ መርዓዊ መጽሐፍ እጅግ በጣም ገርሞኛል፣ አስደንቆኛል፣ አስተምሮኛል፣ አስጠንቅቆኛል። ጨዋዊ አጻጻፍ፣ አስተውሎ የተሞላ የነገረ ፍጻሜ አተያይ፣ ስለዚህ ሰዎች ሁሉ እንዲያነቡት ብቻ ሳይሆን፣ እንዲያጠኑት እመክራለሁ። ጸሐፊውን ከዓመታት በፊት ጀምሮ አውቀዋለሁ፣ የተሃድሶ እንቅስቃሴ ካፈራቸው ታላላቅ ሰዎች አንዱ እንደሆነም አሰባለሁ፣ በተባው ብዕሩ ብቻ ሳይሆን በሕይወቱና ኑሮው «ትስፋ መንግሥትከ፣ ትምጻ መንግሥትከ» የሚል ነው።

ቢንያም በፍቃዱ /ፓስተር/ ፤ Bሐ.D. ከኢትዮጵያ ተሃድሶ
አብያተ ቤተ ክርስቲያናት እና ማኅበራት ኅብረት

እጅግ የሚገርም ነው! አንብቤ ስጨርስ ልቤ በመምጣቱ ናፍቆት ተሞላ።

ታጋይ አበበ

መጽሐፍ ቅዱስ፣ እውነተኛ መጽሐፍ ነው። ደግሞም ከሺ ዓመታት በፊት የተነገሩና ሊፈጸሙ አይችሉም የምንላቸው ትንቢቶች በየዕለቱ ሲፈጸሙ ስናይ፣ ከእውነተኛው የእግዚአብሔር ቃል ጋር ይበልጥ አንድንጣበቅ ያደርገናል። በተለይም ሰዎች የመጽሐፍ ቅዱስን እውነተኝነት እንዲጠራጠሩ ሰይጣን በኃይል እየሠራ ባለበት በዚህ ከፋ ዘመን፣ እንደዚህ ዓይነት ወጥ ሥራ፣ ለሚያምኑም ሆነ ለማያምኑ፣ ዘመኑን ለማስተዋል የሚረዳ የማንቂያ ደዉል ነው።

ሰለሞን ግርማጽዮን

የዚህን መጽሐፍ ጸሐፊ ከዛሬ 14 ዓመት በፊት ጀምሮ አውቀዋለሁ፤ ድፍረቱ ጽናቱ፣ ተስፋ አለመቁረጡና የአእምሮው ስፋት እያስገረመኝ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፤ ይኼንን መጽሐፍ ለመጻፍ፣ ለማንበብና ለማጥናዘብ ሰፊ አእምሮ ይጠይቃል፤ ከርስቲያኖችን ብቻ ሳይሆን ሰዎችን ሁሉ ለንስሃ ያቻኩላል። ይኼ የመንግሥት ጉዳይ እንጂ፣ የአንድ ሃይማኖት ጉዳይ ብቻ አይደለም፤ አማርኛ ተናጋሪዎችን ብቻ ሳይሆን ዓለምን ሁሉ ይመለከታል። እግዚአብሔር አምላክ ለሁሉ የሚደርስበትን መንገድ ያመቻች ከማለት ሌላ ምን አላለሁ?

አሸናፊ ኢሳይያስ የምሥራች አገልግሎት ሥራ መሪ

ምስጋና

ካለሁበት ወደ ኋላ ዞሬ ስመለከት፣ ለዛሬው ማንነቴ፣ ይልቁኑም ለጸሐፊነቴ፣ አውቃችሁም ሆነ ሳታውቁ የየራሳችሁን አስተዋጽኦ ያደረጋችሁ ብዙ እንደሆናችሁ አስተዋልኩ። እናም ይኼ መጽሐፍ፣ ለእኔ ትልቅ ሥራ መስሎ በታየኝ ጊዜ እንዳንዶቻችሁን ነቅሼ ማመሰገን እንዳለብኝ ተሰማኝ።

መጽሐፉን ለመጻፍ ከመነሣቴ በፊት ባሉት ጥቂት ዓመታት በጉዳዩ ዙሪያ በየቤተ ክርስቲያኑ ሳስተምር ከገጠመኝ ልዩ፣ ልዩ ፈተና የተነሣ «ይኼ ትምህርት አንዳች የተሰየ ምስጢር አለው ለንዴ?» ብዬ እስከጠረጥር ድረስ ሆኜ ነበር። ሆኖም እነዚያ ጊዜአት እጅግ ወሳኝ ወቅቶች እንደነበሩ ተረድቻለሁና፣ እንዳስተምር ዕድሉን የሰጡኝን፣ ቁጭ ብለው የሰሙኝን፣ ሰምተው ያበረታቱኝንና የመከረሩኝን፣ ለምን በመጽሐፍ አታዘጋጀውም ብለው የሞገቱኝን ሁሉ እጅግ አመሰግናቸዋለሁ።

መቼም ለሚጽፍ ሰው፣ የትዳር አጋሩ ያላት ሚና ምን ያህል እንደሆነ ስለሚታወቅ ብዙ ማብራሪያ የሚያስፈልገው አይደለም፤ ከዚህ አንጻር እኔም በእነዚህ ዓመታት አጠገቤ ለነበረችው ባለቤቴ ጸጊ ያለኝ አክብሮት ብዙ ነው።

ለመጽሐፉ የሚሆነውን የዘር ገንዘብ በራሱ ተነሣሽነት ሰጥቶ እንድጽፍ ያነሳሳኝ ስለነገረ ፍጻሜ ለ16 ሳምንታት ያስተማርኩትን ሲዲ ያደመጠ አንድ ሰሙ እንዳይጠቀስ የሚፈልግ ወንድም ነው። ይህም ሰው እንደእግዚአብሔር መልአክ፣ ለእኔ በሰዓቱ የተላከ መልዕክተኛ በመሆኑ፣ መቼም ልረሳው አልችልም። እውነት ለመናገር እኔ ልጻፈው እንጂ ራእዩው የእርሱ ነው ማለት እችላለሁ። ዋጋውንም አምላኬ እንደባለጠግነቱ መጠን ይከፈለው።

ለዚህ መጽሐፍ በዚህ መልክ መቀናበር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረገ ሌላው ሰው፣ ወዳጄ ሰለሞን ግርማጽዮን ነው፤ እርሱ አስቀድሞ በቤተ ክርስቲያን መድረክ ለማስተምረው ትምህርት ብዙ መረጃዎችን ሲያጠናቅርልኝ የቆየ ከመሆኑም በላይ፣ በመጽሐፍ መልክ እንዳዘጋጀው ወትውቶኛል፤ መጻፍ ከጀመርኩ በኋላም የምፈልገውን ማንኛውንም ዓይነት መረጃ በፍጥነትና በጥራት ያቀርብልኝ ነበር። የእርሱ ከአጠገቤ መሆን፣ የመጽሐፏን አቅምና ውፍረት እጅግ አልቆታል ብል ምንም አላጋንንኩም። ሰሌ፣ አመሰግናለሁ።

እኔ እንዲህ አዋቀርኩት እንጂ፣ መጻፉ እንኳ የብዙ ሰዎች የዓመታት ምርምርና ድካም ውጤት ነው፤ ስለዚህ በዋቢነት የተጠቀምኩባቸውን መጻሕፍት የጸፉትን ሁሉ በብዙ አክብሮት ከአንባቢዎቼ ጋር ሆኜ ላመሰግን ይገባኛል።

ፍናተ መንግሥትን፣ ቀድማችሁ ተመልከታችሁ አስተያየታችሁን የሰጣችሁኝ እናንት የነገረ መለኮት ተማሪዎች ሆይ፣ በብዙ ስላነቃቃችሁኝና ስላደፋፈራችሁኝ አመሰግናችኋለሁ። የሥነ ጽሑፍ ባለሞያዎቹ ወዳጆቼም ብትሆኑ፣ አስተያየታችሁ ምን ያህል እንደጠቀመኝ እናንተ ራሳችሁ አይታችኋል፤ እኔም እግዜር ይስጥልኝ ብያለሁ።

የፊደል ዕርማቱን ተግተህ የሠራኸው የሥጋ ዘመዴ ታጋይ አበበ፣ «አይዞህ በርታ፣ መጻፍ ትችላለህ» እያከ ያበረታታኸኝ ገበየሁ ዘሩ፣ ላለፉት አስር ዓመታት ጽሑፎቼ እንደ ሀንፃዎችህ ውብ እንዲሆኑ ያገዘከኝ አርከቴክቱ ዘገየ ቸርነት፣ ለዓመታት ከጎኔ ሆነህ ወዳጅነትህን በፍቅር ያሳየኸኝ ጓደኛዬ ኤልያስ ወርቁ፣ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የነበራችሁ ድርሻ የላቀ እንደነበር ሳስታውቃችሁ በብዙ ፍቅር ነው።

ለማሳተሚያና ተያያዥ ለሆኑ ጉዳዮች የእናንተ ድጋፍ እጅግ በሚያስፈልገኝ ሰዓት፣ በገንዘብ ያገዛችሁኝ አቶ ጠና ከበደና ባለቤታቸው ወ/ሮ ተስፋነሽ አበራ፣ አምሳሉ አንባው፣ ወንድዬ አበራና አውነቱ ፈረደ፣ ጌታ አትረፍርፎ ይባርካችሁ እላለሁ። ታናሽ ወንድሜ ልየው ንጉሤ ግን በመጨረሻው ሰዓት የዋልከልኝ ውለታ መቼም የምረሳው አይደለም።

ላለፉት ዓመታት በሕትመት ሥራ ከጎኔ ለነበራችሁት ለአፍሪካ ማተሚያ ቤት ባለቤቶችና ሠራተኞች በጠቅላላ፣ በተለይም ለኤፍሬም፣ ለይልቃልና ለስንታየሁ ዳኜ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። የትየባ ኮምፒዩተሬ ቢታመመች ጊዜ ሁሉ እያከማችሁ በዚህ በኩል አከል እንዳይገጥመኝ በቅንነት ላገዛችሁኝ ለ«ፐሮፌናቹ» ኑኑና ፊሽ፣ አምላኬ ዕድሜ ይስጥልኝ። ከጉድለታችሁ ላይ አንሥታችሁ የላፕቶፕ ኮምፒተራችሁን የሸለማችሁኝ አዚና ዮኒም አግዚአብሔር ብድራታችሁን ይክፈላችሁ።

ባለፉት ሁለት ዓመታት ይኼንና ሌሎች መጻሕፍትን ለመጻፍ በቂ ጊዜ በሚያስፈልገኝ ሰዓት ጊዜውን እንዳገኝ መንገዱን የጠረጋችሁልኝ ስማችሁን ያልጠቀስኳችሁ አንዳንድ ሰዎች ናችሁ፤ በእርግጥ ያደረጋችሁልኝን የተረዳሁት ዘግይቼ ቢሆንም፤ ምን ያህል እንደጠቀማችሁኝ ስገነዘብ ከልቤ አመሰግናችኋለሁ።

በተረፈ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ አርዓያነታችሁንና ኢጋርነታችሁን ያሳያችሁኝን በጠቅላላ፣ አምላኬ በነገር ሁሉ አብዝቶ ይባርካችሁ።

መርዓዊ ንጉሤ

ከሁሉ በፊት

ባለፈው ክረምት አንድ እኅታችን አርፋ እኔና ጓደኞቼ በቀብሯ ላይ ተገኘን፤ በእርግጥ በወረቀት የአባልነት መስፈርት ከታየ፣ እኅታችን በእኛ ዘንድ አልነበረችም፤ ይሁን እንጂ የቀብር ሥርዓቱን የማስፈጸም ኃላፊነት የወደቀው እኛው ላይ ነበር፤ በዕለቱ አንደኛው ወንድማችን አጭርና ግልጥ በሆነ የወንጌል ቃል የዛሬ ቀባሪዎች ነገ በሰው ሽክም እንደምንመጣ ካስታወሰን በኋላ፣ ከዚያ በፊት ማድረግ የሚገባን ነገር እንዳለ አጽንቶ አሳሰበ፤ ሌላው ወንድማችን ደግሞ ለመጀመሪያ ጊዜ የቀብር ሥርዓት አስፈጻሚ በሆነበት በዚያ ቀን «*ሁላችንም አፈር ነንና ወደ አፈር እንመለሳለን*» ሲል ሦስት ጊዜ አፈሩን ወደመቃብሩ በተን፣ በተን እያደረገ የሟች ግብአተ መሬት መፈጸሙን አወጀ። ከቀብሩ በኋላ እንደተለመደው ሁላችንም ወደየሥራችን ተሰማራን። ሰባኪው እንደ ተናገረው፣ የዛሬዎቹ ቀባሪዎች ነገ ተራችን ሲደርስ ወደዚሁ ስፍራ መመለሳችን ግን አይቀርም።

በዕለቱ በቀብር ሥርዓቱ ላይ ከነበርነው አብዛኞቻችንን ከዓመታት በፊት በሌላኛው ጓደኛችን ቀብር ላይ መገኘታችንን አስታወስኩ፤ ቀናት ባለፉ ቁጥር፣ እጅግ እንወደው የነበረ ጓደኛችንን ምን ያህል እየረሳነው እንደሆነም አስተዋልኩ፤ ሌላው ቀርቶ ስለእሱ የምናወራው እንኳ አልፎ፣ አልፎ ብቻ ነው። ከመሞቱ በፊት የነበሩትን ጥቂት ወራት አብረን እንደማሳለፋችን፣ ፈጽሞ የሚሞት አይመስልም ነበር፤ ለዚህም ነው መሰል፣ ብዙዎቻችን መሞቱን እንኳ አምነን ለመቀበል ተቸግረን ሰነበትን። እኔም በበኩሌ ከጥቂት ወራት በፊት ስለነገ ተስፋና ዕቅዶቻችን ያወጋነው ሁሉ ትዝ እያለኝ፣ የሆነውን አሜን ብሎ ለመቀበል አቃተኝ። በወቅቱ ብዙ ያለቀስኩ አይመስለኝም፤ ግን ደረቅ እንባ ደረቴን ዘግቶት ለረጅም ቀናት በውስጤ ማንባቴን አስታውሳለሁ፤ ያንን ሁሉ ተስፋ ምን አድርጎት እንደ ሄደ እስከ አሁን ግልጥ አልሆነልኝም። ከሁሉም አሳዛኙ ነገር እንዴት፣ በማንና በምን፣ እንደሞተ አለመታወቁ ነው። ምንም እንኳ እንደማንኛውም

ሚች ስለአሚሚቱ *«አንዲሀና በዚህ ምክንያት»* የሚል ታሪክ ብንሰማም ማናችንንም አላሳመነንም፤ እሱም ቢሆን፣ ይኼን እንኳ ሳይነግረን ነው፣ ላይመለስ የሄደው::

ሰው ሁሉ የምድር ዘመኑ ሲጠናቀቅ መሞቱ አይቀርም፤ ስለዚህ ሁሉ ከዛሬ በኋላ ስለሚሆነው ነገር ቆም ብሎ ሊያስብ ይገባል:: የዛሬ «ሕያዋን» አንድ ቀን እነዚህ ወዳጆቼ ባዘገሙበት ጎዳና ተከትለን መንጎዳችን አይቀርም:: በእኛና በእነሱ መኻል ያለው መሠረታዊ ልዩነት እነርሱ ቀድመውን መሄዳቸው ብቻ ነው:: ምናልባት በምድር ሳሉ ካደረጉት የሚጎድላቸው ነገር ቢኖር እንደገና ለማረም ወይም ለማስተካከል አይችሉምና በአንድ በኩል እኛ በዚህ ዕድለኞች ነን:: ግን ለመሆኑ ላይመለሱ የሄዱበትን አገር ወደውት ይሆን? ለመመለስ ዕድል ቢያገኙ ይመለሱ ነበር፣ ወይስ ያሉበትን ይመርጡታል? እነዚህ ጥያቄዎች ወደ ሌሎች ታላላቅ ጥያቄዎች የሚወስዱ ናቸው::

የሰው ወደዚህ ምድር መምጣትና የመኖሩ ፋይዳ ምንድን ነው? ከሕይወትና ከሞት ለሰው የሚሻለውስ የትኛው ነው? ታላቁ የወንጌል ሰባኪ ጳውሎስ *«ከሕይወትና ከሞት የቱን እንደምመርጥ ተቸግሬአለሁ»*[1] ሲል፣ የብዙዎቻችን ምርጫ ግን አንድ ብቻ ነው፤ እሱም መኖር:: በጳውሎስ ዓይነት የምርጫ አጣብቂኝ ያልተያዝነው፣ ስለሕይወት ያልገባን ነገር ስላለ ወይስ ኑሮ ስለተመቸን? ኧረ ለመሆኑ ምቾት ምንድን ነው? የአሁን ኑሮአችን የወደፊቱን የሚወስነው እስከምን ድረስ ነው? ሰው ሁሉ በምድር እንዲኖር የተሰጠውን ጥቂት ዘመን ሲያጠናቅቅ መሞቱ እንደማይቀር በእኛ ባይደርስም በሌሎች እያየን ነው:: ግን ከሞት በኋላ ሕይወት አለ እንዴ? ዓለም የምትጓዘው አስቀድሞ በታወቀና በተተነበየ መስመር፣ ወይስ በደመ ነፍስና በነገሮች መገጣጠም? ይህን በምን ማወቅ እንችላለን? ከእኛ አልፎ ያለው ይኼ ዝብርቅርቅና ግራ የተጋባ ዓለም ወዴት እየተጓዘ ነው? ፍጻሜውስ መቼ ነው? የሰው ኑሮ መጨረሻስ የት ነው?

[1] ፊል1:23-24 በእነዚህም በሁለቱ እጨነቃለሁ፤ ልሄድ ከክርስቶስም ጋር ልኖር እናፍቃለሁ ከሁሉ ይልቅ እጅግ የሚሻል ነውና፤ ነገር ግን በሥጋ መኖሬ ስለ እናንተ እጅግ የሚያስፈልግ ነው።

ልብ በሉ!

ይኼ «ሰው» የሚባለው ፍጡር እኮ በአጋጣሚ ወይም በድንገት የተገኘ አይደለም:: ከማንኛውም ሌላ ዓይነት ፍጡር እርሱን ልዩ የሚያደርገውም በፈጣሪው መልክና ምሳሌ መፈጠሩ ነው:: እንዲያ ከሆነ ደግሞ ፈጣሪ፣ መልክና ምሳሌውን እንዴት በከንቱ ይተዋል? በእርግጥ ስለራሳችን አፈጣጠርና ኑሮ እንዲሁም ስለ ፈጣሪአችን የሚያስረዳ የሆነ መንገድ ማግኘት አለብን::

በመሠረቱ ለእነዚህ ጥያቄዎች አጥጋቢና ሙሉ መልስ ማግኘት የምንችለው መጽሐፍ ቅዱስን ከመሠረቱ፣ በጥንቃቄ የመረመርን እንደ ሆነ ብቻ ነው:: ትናንት፣ ዛሬም ሆነ ነገ ስለሚሆኑ ነገሮች ዝርዝር ታሪክ እዚህ መጽሐፍ ውስጥ ይገኛል:: ከሰው ፍጥረት እስከ ፍጻሜው፣ በዚህ መጽሐፍ ተተንትኗል:: ዓለምና በውስጡ የሚኖሩ ፍጥረታት ከየት እንደመጡና ወዴት እንደሚሄዱ በርብሮ ማወቅ የሚፈልግ ሰው፣ ይኼን መጽሐፍ ቢያጠና ለብዙ እንቆቅልሾቹ መልስ ያገኛል:: እርግጥ ነው፣ መጽሐፉ ተራ የሃይማኖት መጽሐፍ ሳይሆን፣ የፈጣሪ እስትንፋስ ያለበት በመሆኑ በተለየ ጥንቃቄ መጠናት የሚገባው ነው:: ደግሞም ከሰው አእምሮ በላይ የሆኑ እውነቶች የታጨቁበት እንደሆነ ለአፍታም እንኳ ችላ ማለት አይቻልም:: እውነቶቹም ነባራዊ እንጂ፣ አንጻራዊ ሆነው አያውቁም:: ሁሌም ከተጨባጭነት ያለፉና በራሳቸው የቆሙ ኗሪ እውነቶች ናቸው:: የሚደንቀው የሺ ዓመታት ታሪክ እንዲህ በአንድ መጽሐፍ ውስጥ በቀላሉ መገኘቱ ነው:: እጅግ የሚደንቀው ግን አያሌ ሰዎች በዚህ መጽሐፍ ለተገለጡ እውነቶች ዛሬም ድረስ ጀርባቸውን መስጠታቸው ነው:: ብዙ ሰዎች እስከ አሁን ድረስ በጥልቅ ግራ መጋባት ውስጥ የሆኑት ከመጽሐፉ እውነት ጋር ስለተጋጩ ወይም ስለተላለፉ ነው::

እነሆ የዘመናት ፍኖት . . .

ማኅቲት ስለመጽሐፉ

ይኼ «ፍኖተ መንግሥት» የተሰኘው መጽሐፍ፣ ቅዱሱን መጽሐፍ መሠረት አድርጎ የተጻፈ ሲሆን፣ ታሪካዊ፣ መለኮታዊና ትንቢታዊ ጉዳዮች የተካተቱበት ነው። መጽሐፉ፣ በዘመናት ውስጥ በኖሩ ታሪካዊና መንገዶች ላይ ምልክት በማድረግ፣ ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ለተመለከቱ ትንቢቶችና ክስተቶች ትኩረት እንዲያደርጉ የማነሳሳት ተልዕኮ ያለው ነው። እኔም ከርዕሰ ጉዳዩ አንጻር ከቅዱስ ቃሉ እንዲሁም ከነባራዊው ዓለም እውነት ከመሠረቱ የመረመርኩትን ቅደም ተከተሉን ጠብቄ፣ በጥንቃቄ ለመጻፍ ሞክሬአለሁ።[2] በመሆኑም ለዘመናት እግዚአብሔር ለመንግሥቱ መንገድ እንዲሆኑ የመረጣቸውን መስመሮች በመከተል የሺ ዓመታት ምናባዊ ጉዞ እናደርጋለን። በመጨረሻም ካለንበት ዘመን ሆነን ለወደፊት የተነገሩ ትንቢቶች በምን ዓይነት ሁኔታ እንደሚፈጸሙ በትንቢት መንፈስ እንመረምራለን። ከዚህ አንጻር እስራኤል፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ዋነኛ ማዕከል በመሆኗ በዚህ መጽሐፍ ልዩ ትኩረት ተሰጥቷታል።

መጽሐፉ አምስት መጻሕፍትን የያዘ ጥራዝ ነው። ምንም እንኳ እያንዳንዳቸው በየራሳቸውን መልዕክት አንጻር ቢዋቀሩም አንዱ ከሌላኛው ጋር ፍጹም የማይነጣጠል ወይም የተሳሰረ ነው። በዚሁ መሠረት መጽሐፍ ፩: መንግሥትህ ትምጣ፣ መጽሐፍ ፪: ፍኖተ መንግሥት፣ መጽሐፍ ፫: ዳንኤልና ሰባው ሱባኤ፣ መጽሐፍ ፬: የአሁኑና ወደፊት የሚሆነው፣ መጽሐፍ ፭: እስራኤል፣ አውሮፓና መካከለኛው ምሥራቅ፣ ይሰኛሉ።

[2] ሉቃ1:1-4። በእኛ መካከል ስለተፈጸሙት ነገሮች ብዙዎች የተቻሳቸውን ያህል ጽፈውት ይገኛል፣ ይህም ታሪክ ከመጀመሪያው አንስቶ የዓይን ምስክሮችና የቃሉ አገልጋዮች የነበሩት ያስተላለፉልን ነው። ከቡር ቴፍሉስ ሆይ፣ እኔም በበኩሌ ሁሉንም ከመሠረቱ በጥንቃቄ ከመረመርሁ በኋላ፣ ታሪኩን ቅደም ተከተሉን በመበቀ ሁኔታ ልጽፍልህ መልካም ሆኖ ታየኝ

በመጀመሪያው «መንግሥትህ ትምጣ» በሚለው መጽሐፍ፣ በራሴ ምናባዊ ዕይታ ከ2000 ዓመታት በፊት በመሲሁ ላይ የደረሰውን አሰቃቂ መከራና ስቃይ በተለየ ሁኔታ ከተረኩኝ በኋላ፣ ለምን ያ ሁሉ ሊሆንበት እንደቻለ አጭር ትንታኔ ለመስጠት ሞክሬአለሁ። ትንታኔው ከጌታ ትምህርትና ሕይወት በመነደርደር፣ የእርሱ የመንግሥት ሥርዓት ከዚህ ዓለም መንግሥታት ፍጹም ልዩ እንደ ሆነች ይጠቁማል፤ የመጣችውና የምትመጣው መንግሥት ልዩነት እና አንድነት ያስረዳል፤ በዚህ ምድር ፍጹም የሆነ የመንግሥት ሥርዓት ሊገኝ እንደማይችል በማስገንዘብ ዜጎች በመጣችው የጌታ መንግሥት እውነተኛ ሥርዓት እንዲኖሩ ይመክራል፤ የምትመጣዋ መንግሥት በርቀት በመጠቆም የዚህን ዓለም ሕዝብ፣ የኑሮ ፍልስፍናና የመንግሥት ሥርዓት በስሱ ይሞግታል።

ሁለተኛው መጽሐፍ «ፍኖተ መንግሥት» የተሰኘው ነው። ይኼም መጽሐፍ ከፍጥረት እስከ አዲስ ኪዳን መግቢያ የሚገኘው የሺ ዓመታት ታሪክ በአጭሩ የቀረበበት ነው። በዚሁ ክፍል ከአዳም ጀምሮ እስከ አብርሃም፣ የእስራኤል መንግሥት ምሥረታና ለሁለት መከፈል፣ እንዲሁም የሁለቱ አገሮች መማረክና ከምርኮ መመለስ፣ በአጭሩ ይዳሰሳሉ። በዚህም ከታሪክ አንጻር አስፈላጊታቸው ጎልቶ በታዩኝ ክፍሎች ላይ የበለጠ ትኩረት ያደረኩኝ ሲሆን፣ ብሉይ ኪዳን በአጭሩ የዳሰስኩበት ነው ማለት እችላለሁ፤ እንዲያውም የቀሩትን መጻሕፍት አሳብ ለመረዳት አስፈላጊ የሆኑ ቁልፍ ጉዳዮች ያሉት እዚህ መጽሐፍ ውስጥ ነው ብዬ አስባለሁ።

ሦስተኛው መጽሐፍ በሰባው ሱባኤና በዳንኤል ትንቢት ላይ ልዩ ትኩረት የሚያደርግ ነው፤ ርዕሱም «ዳንኤልና ሰባው ሱባኤ» ይሰኛል። በዚህ መጽሐፍ በተለይ የዳንኤል ትንቢትና በትንቢቱ የተጠቀሰው ሰባ ሱባኤ በጥልቀት ይዳሰሳሉ። ከዳንኤል ትንቢት አንጻር በአሁኑ ጊዜ የተፈጸሙና ያልተፈጸሙ ትንቢቶችንም እንቃኛለን። ምንም እንኳ ትንቢቱ ለአፈታት አስቸጋሪ መስሎ ቢታይም፣ እኔ ግን የዘመናት ፍጻሜን ለሚያጠና ሰው ያለውን ፋይዳ አስቤ፣ ልዩ ትኩረት አድርጌበታለሁ። አንድ ታዋቂ ሰው፣

«ትንቢተ ዳንኤል ባይኖር ኖሮ መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት አስቸጋሪ ይሆን ነበር» ማለቱ፣ የመጽሐፉን እጅግ አስፈላጊነት በሚገባ የሚገልጥ ነው።

በአዲስ ኪዳን ትንቢቶች ይልቁንም፣ በራእይ መጽሐፍ ላይ ተመርኩዞ የተጻፈው አራተኛው መጽሐፍ «የአሁኑና ወደፊት የሚሆነው» የሚል ርዕስ ተሰጥቶታል። የዚህ መጽሐፍ ትኩረት በተለይ ከቤተ ክርስቲያን መመሥረት በኋላ የተከናወኑና ወደፊት እንደሚሆኑ የሚጠበቁ አበይት ጉዳዮች ናቸው። ከእነዚህም ውስጥ የመጨረሻው ዘመን አበይት ምልክቶች፣ በራእይ መጽሐፍ ያሉት ሰባት አብያተ ክርስቲያናት፣ ንጥቀትና የጌታ ዳግም መምጣት፣ ዘንዶውና ታላቁ መከራ፣ የሰይጣን አሠራርና የወደፊት ዕድል ፋንታ፣ የመጨረሻው ዘመን የፍርድ ሥርዓትና የአማኞች ዕድል፣ 666 እና የሚመጣው ዓለም የንግድ ሥርዓት፣ ታላቂቱ ባቢሎንና የመሳሰሉት ሰፊ ሽፋን አግኝተዋል።

አምስተኛውና የመጨረሻው መጽሐፍ «እስራኤል፣ አውሮፓና መካከለኛው ምሥራቅ» የሚል ርዕስ አለው። ከመጨረሻው ዘመን አንጻር በመጽሐፉ በጥልቀት የተዳሰሱት በርዕሱ ላይ የተመለከቱት የዓለማችን ክፍሎች ቢሆኑም፣ ከዚህ ጋር የተያያዙ የወቅቱና የዘመናት ታሪኮች የተካተቱበት መጽሐፍ ነው። በዚሁ መሠረት ግሎባላይዜሽን፣ የአውሮፓ ኅብረትና የእስከ ዛሬ እንቅስቃሴ፣ ጎግ ማጎግ፣ እስልምናና አረቦች፣ ነዳጅ ዘይትና መካከለኛው ምሥራቅ፣ የእስራኤል ዳግም መመሥረትና ኢየሩሳሌም፣ ሁለተኛው የዓለም ጦርነትና የአይሁዳውያን አሰቃቂ መከራ፣ የአይሁዳውያን ወደ ፍልስጤም መፍለስና ፍልስጤማውያን፣ እንዲሁም ሦስተኛው ቤተ መቅደስ የሚሉት ርዕሰ ጉዳዮች በትኩረት የሚጠኑ ናቸው።

✡ 🕮 ✡

በመሠረቱ በዚህ መጽሐፍ የተነሡ በርካታ ጉዳዮች ወደ ፊት ገና እንደሚሆኑ የሚጠበቁ ከመሆናቸው አንጻር በመጨረሻው ዘመን መምህራን ዘንድ የአተረጓጎም ልዩነት የሚንጸባረቅባቸው መሆኑን እረዳለሁ። በመሆኑም አስፈላጊ ሆኖ እስካላገኘሁት ድረስ በተቻለ መጠን አከራሪ ባለመሆን፣ የሌሎችን እምነትና አቋም ላለመጻረር ጥረት አድርጌአለሁ፤ ደግሞም በተደጋጋሚ «እንዲህ ይመስለኛል» የሚል ሐረግ ለመጠቀም የተገደድኩበት ዋነኛ ምክንያት ይኼው ነው። ምናልባት አካሄዴ በአንዳንዶች ዘንድ ላይወደድ ወይም እንደ «አቋም የለሽነት» እንዳይቆጠር ስጋት ቢያድርብኝም የተሻለ አማራጭ ግን አላገኘሁም። በአንጻሩ አቋም መያዝ እንዳለብኝ ባመንኩባቸው ጉዳዮች የማምንበትን በግልጥ ከመናገር ወደኋላ አላልኩም፤ ይኼም አካሄዴ በእኔ አቋም የማይስማማ ሰው እንኳ፣ የማይስማማባቸውን ጭብጦች በተመለከተ በጥልቀት እንዲመረምር ያነሳሳዋል የሚል እምነት አሳድሮብኛል፤ በተጨማሪም በብዙ ሰዎች ዘንድ የእግዚአብሔርን መንግሥትና የመጨረሻው ዘመን በተመለከተ የሚታየውን ስሜት አልባነትና ቸልተኝነት በማስወገድ በኩል መጽሐፉ የራሱን አስተዋጽኦ ያደርጋል ብዬ አስባለሁ።

ይሁን እንጂ ዓላማዬ፣ ባነሣኋቸው ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ጥልቅ ሥነ መለኮታዊ መከራከሪያ ማንሣት፣ ወይም የታሪክ ምርምር ዘገባ ማቅረብ አይደለም። አንባቢዎቼም ቢሆኑ፣ መጽሐፉን እንደ አንድ ምስክር ጽሑፍ ቢያዩት የተሻለ ነው ብዬ አስባለሁ። በዚያ ላይ ከነገሩ ስፋት አንጻር በዚህ አነስተኛ መጽሐፍ የተዳሰሱት ጉዳዮች ውቂያኖስን በጭልፋ የመጨለፍ ያህል እንደሆኑ መዘንጋት አይገባም። የመጽሐፉ ርዕስ እንዲሆኑ የተዋቀሩት ሁለት ቃላት እንዲገልጡ የተፈለገውም ይኼንኑ ነው። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ፣ በተለየ ሁኔታ ሌላ ትርጉም እስካልተሰጠው ድረስ «ፍኖት» ማለት፣ መንገድ ማለት ሲሆን «መንግሥት» ደግሞ በእግዚአብሔር ዘንድ ያለችው ሉአላዊት ግዛትና የእርሱ የሚሆን ሕዝብ ነው።

✡ 🕮 ✡

መጽሐፍ ፩

መንግሥትህ ትምጣ!

የመጣችዋና የምትመጣዋ መንግሥት!

በመጽሐፉ የተጠቀሱት የቅዱሱ መጽሐፍ አሳቦች ከ1954/ቀ.ኃ.ሥ/ ትርጉም፣ ከ1980 ቀላል የአማርኛ ትርጉም እና «ኢንተርናሽናል ባይብል ሶሳይቲ» በ1993 ካሳተመው አዲሱ መደበኛ ትርጉም የተወሰዱ ናቸው። ምንም እንኳ አብዛኛዎቹ አሳቦች ከመጽሐፍ ቅዱስ በቀጥታ የተወሰዱ ቢሆኑም፣ በመጠኑ የራሴን የአጻጻፍ ዘይቤ የተከተልኩባቸው ስፍራዎች አሉ። ከሞላ ጎደል ጥቅሶቹን፣ በዚያው ገጽ ባለው የግርጌ ማስታወሻ አኑሬአቸዋለሁ። እንዲህ ያደረኩት በአንድ በኩል አንባቢን ከንባቡ ላለማደናቀፍ፣ በሌላ በኩል መረጃውን ላለማራቅ ስል ነው፤ ሆኖም አንዳንዴ በርከት ያሉ ጥቅሶች ሲጥሙኝ አንድ ላይ ሰንጌ አቅርቤአቸዋለሁ።

ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ ያሉት መረጃዎች ለዓመታት ከልዩ ልዩ ምንጮች የሰበሰብኳቸው ናቸው። እነርሱን በተመለከተ፣ ዕድለኛ ሆኜ ከየት እንዳገኘኋቸው ያስታወስኳቸውን፣ በግርጌ ማስታወሻ ለማመልከት ሞክሬአለሁ። ሆኖም አንዳዶቹን ከየት እንዳገኘኋቸው ባለማስታወሴ ወይም ደግሞ ከብዙ ምንጮች የተገኙ መስሎ ሲታዩኝ ያለ ግርጌ ማስታወሻ፣ አለያም በርከት ያለው አሳብ ከየት እንደተገኘ በመጠቆም አልፈዋለሁ። በዚያ ላይ «ዱላ» የተባለ ክፉ የኮምፒዩተር ቫይረስ ብዙ የመረጃ ምንጮቼን አጥፍቶብኛል። ከዚህ የተነሣ አንዳንድ መረጃዎች ሊሟሉልኝ አልቻሉም። ያም ሆኖ ግን ዋቢ መጽሐፍትን በዘረዘርኩ ጊዜ ብዙዎቹን ለማካተት ሞክሬአለሁ።

✡ 🕮 ✡

ማውጫ	ገጽ
መግቢያ	21
ምዕራፍ ፩	
መንግሥቴ ከዚህ አይደለችም	24
ምዕራፍ ፪	
የመንሥቱ ብርሃን	30
ምዕራፍ ፫	
የመንግሥቱ ሚስጥር	36
ምዕራፍ ፬	
የመጣችዋና የምትመጣዋ መንግሥት	49
ምዕራፍ ፭	
የመጣችዋ መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን	52
ምዕራፍ ፮	
መንግሥትህ ትምጣ	64
ኤሎሄ፣ ኤሎሄ መንግሥትህ ትም.....	69

መግቢያ

በቅርቡ፣ ከሃያ አምስት ዓመት በፊት የታተመ አንድ መዝገበ ቃላት አግኝቼ ስመለከት ነበር። በእርግጥ መጽሐፉ በወቅቱ ከዓለም ሕዝብ አንድ ሦስተኛ የሚሆነው ሕዝብ ከሚገዛበት ርዕዮትና ፍልስፍና አንጻር የተጻፈ ቢሆንም፣ እኔ ግን ስለመንግሥት ምንነት እያጠናሁ ስለነበር በትኩረት ነበር የመረመርኩት፣ በመጽሐፉ ስለመንግሥት ምንነት የተሰጠው ትንታኔ በከፊል ይኼን ይመስላል።[1]

«መንግሥት፣ ኢኮኖሚያዊ የበላይነት ያለው መደብ ፖለቲካዊ ድርጅት ሲሆን፣ ዓላማውና ተግባሩም በአንድ ጎብረተሰብ ውስጥ ያለውን ሥርዓት ለማስጠበቅና ለማጠናከር፣ የሌሎች መደቦች ተቃውሞና አሻፈረኝ ባይነት ለማፈን የሚያገለግል የመጨቆኛ መሣሪያ ነው። መንግሥት፣ ሥልጣኑን በኃይል ከሚያስከብርባቸው መሣሪያዎቹ ሌላ ርዕዮተ ዓለማዊ መሣሪያዎች አሉት። . . . መንግሥት፣ በቅድመ መደብ ጎብረተሰብ ውስጥ የነበረውን የአረጋውያን አስተዳደር በመተካት ከመደቦች መፈጠር ከማምረቻ መሣሪያዎች በግል መያዝ፣ ከማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል ማደግና መስፋፋት ጋር ተያይዞ የመጣ ፖለቲካዊ ድርጅት ነው። . . . በሶሻሊስት ሥርዓት የወዝ አደሩ መንግሥት፣ አድሃሪዎችንና ፀረ አብዮት እንቅስቃሴዎችን መደምሰሻ እንጂ፣ የመበዝበዣ መሣሪያ አይደለም። . . . ሰፊ ማኅበራዊ መሠረት ያለው የሽግግር መንግሥት በሰፈነበት በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ደረጃም ቢሆን መንግሥት የመበዝበዣ መሣሪያ ሳይሆን፣ እንደየ አገሩ ተጨባጭ ሁኔታ የተወሰኑ መደቦችንና የጎብረተሰብ ክፍሎችን ጥቅም የሚያራምድ ወገናዊ ድርጅት ነው። . . .መንግሥት፣ ከማይታረቅ የመደቦች ቅራኔ የመነጨ በመሆኑ ሁሌም የነበረና የሚኖር ሳይሆን፣ በጎብረተሰብ የዕድገት ሂደት ውስጥ የተከሰተና ከመደቦች መጥፋት ጋር አብሮ የሚከስም ነው። ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ፣ ጎሊናዊ የበላይነት ከከፍተኛ ደረጃ በሚደርስበት፣ በኮሚኒስት ሥርዓት ጎብረተሰቡ ራሱን በራሱ ለማስተዳደር ስለሚበቃ የመንግሥት ታሪካዊ ኃላፊነት ያበቃል።»

[1] ማርክሳዊ ሲኒናዊ መዝገበ ቃላት። ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት። አዲስ አበባ። 1978።

ይኼን የመንግሥት ምንነት ትርጉም ሳነብ ብዙ ነገሮች አስተዋልኩ፤ ምንም እንኳ «ለራስ ሲቆርሱ፣ አያሳንሱ» ከሚለው የቆየ ብሂል አንጻር ሲታይ ትርጉሙ የአንድ ወገን አከራሪ እምነት ብቻ ይምሰል እንጂ፣ በሌላኛው ጽንፍ ያለውም ቢሆን ከዚህ ብዙም ያልራቀ እንደሚሆን ጥርጥር የለውም:: ከሁሉም ያስደነቀኝ ግን የመንግሥት ጎልውና መቼ እንደሚከስም የተሰጠው ትንታኔ ነው:: ይሁን እንጂ እነርሱ እንዳሉት ሳይሆን የሥርዓቱ አራማጆችና ሥርዓታቸው ማንም ባልጠበቀው ጊዜ ስለተወገዱ ቢያንስ የዚህ ዘመን ሰው የተባለው ሁሉ ፈጽሞ እንደማይሆን የተረዳ ይመስለኛል::

እናንተ ግን ይኼን ልብ በሉ

እግዚአብሔርም ሰውን ፈጥሮ በምድር ላይ ያኖረበት ዋና ምክንያት በሰው በኩል መንግሥቱን በምድር ሊመሠርት ወዶ ነበር:: ሰው ግን በእግዚአብሔር ላይ ዐምጾ የመንግሥቱን ክብር ለሌላ አሳልፎ ሰጠ:: ሆኖም ከዘመናት በኋላ በፍጹም ሰውነት በተገለጠው አምላክ በኩል የእግዚአብሔር መንግሥት እንደ ገና ወደ ምድር መጥታለች:: ይሁን እንጂ ሰዎች ልባቸውን ከፍተው ሊቀበሏት አልፈለጉም:: ይህ አልበቃ ብሎ የመንግሥቱ መሥራችና መሪ የሆነውን መሲህ በግፍ ገደሉት::

እኛም በዚህ «መንግሥትህ ትምጣ» በተሰኘው አንደኛው መጽሐፍ፣ ስለመሲሁና መንግሥቱ መጠነኛ ቅኝት እናደርጋለን:: በቅድሚያ መሲሁ እንዴት ባለ ሁኔታ በግፍ እንደ ተገደለ በጥሞና እናያን:: ደግሞም እርሱ «መንግሥቴ ከዚህ አይደለችም» ብሎ የተናገረው ቃል የመጽሐፉ ዋና ማጠንጠኛ ከመሆኑም በላይ፣ ዓለም እሱን ለምን እንደጠላችው በመጠኑ ለመረዳት እንሞክራለን:: በተረፈ የመጣችዋና የምትመጣው የእግዚአብሔር መንግሥት ምን እንደምትመስል፣ እንዲሁም የመንግሥቱ ዜጋ ለመሆን የሚፈልግ ሰው ማድረግ ስለ ሚገባው ነገር በአጭሩ እንዳስሳለን:: ቀጥሎም ለእግዚአብሔር መንግሥት፣ የምድር እንደ ራሴ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ምን መምሰል እንደሚገባትና በፊቷ የሚጠብቃትን ተስፋ በትኩረት

እንመለከታለን:: በመጨረሻው ምዕራፍም ከጌታ ጸሎት ተነሥተን፣ የአንድ በጽኑ መቃተት ውስጥ ያለ ሰው ጸሎት እናነባለን::

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ «መንግሥት» የሚለው ቃል የመጣችውንና የምትመጣዋን የእግዚአብሔር መንግሥት የሚመለከት ቢሆንም ቃሉ ግን ለሚታየውና ለማይታየው አለያም ለምድራዊውና ለሰማያዊው መንግሥት መገለጫ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል:: ከዚሁ ጎን ለጎን፣ ጥሬ ቃሉ በተለያዩ ዘመናት የነበሩ መንግሥታትንና በማያምኑ ሰዎች ላይ ሠልጥኖ የቆየውን የሰይጣን አገዛዝ ሥርዓት ይመለከታል:: በመሆኑም እነዚህን ነገሮች ከግምት ውስጥ በማስገባት አንዳንድ መሠረታዊ ጉዳዮች በመጽሐፉ እንዲካተቱ ተደርጓል::

✡ 🕮 ✡

ይህንም ምሳሌ ስሕዝቡ ይሳቸው ጀመር። አንድ ሰው የወይን እትክልት ተክሰ ለገበሬዎችም አከራይቶ ብዙ ዘመን ወደ ሌላ አገር ሄደ። በጊዜውም ከወይኑ እትክልት ፍሬ እንዲሰጡት አንድ ባሪያ ወደ ገበሬዎች ላከ፤ ገበሬዎቹ ግን ደበደቡት ባዶውንም ሰደዱት። ጨምሮም ሌላውን ባሪያ ላከ፤ እነርሱም ያን ደግሞ ደበደቡት አዋርደውም ባዶውን ሰደዱት። ጨምሮም ሦስተኛውን ላከ፤ እነርሱም ይህን ደግሞ አቍሰለው አወጡት። የወይኑም እትክልት ጌታ። ምን ላድርግ? የምወደውን ልጄን እልካለሁ፤ ምናልባት እርሱን እይተው ያፍሩታል ስሰ። ገበሬዎች ግን እይተውት እርስ በርሳቸው ሲነጋገሩ። ወራሹ ይህ ነው፤ ርስቱ ስእኛ እንዲሆን ኑ እንገደለው ስሱ። ከወይኑም እትክልት ወደ ውጭ አውጥተው ገደሉት። እንግዲህ የወይኑ እትክልት ጌታ ምን ያደርጋቸዋል? ይመጣል እነዚህንም ገበሬዎች ያጠፋል፥ የወይኑንም እትክልት ስሌሎች ይሰጣል። ይህንም በሰሙ ጊዜ። ይህስ እይሁን ስሱ። እርሱ ግን ወደ እነርሱ ተመልከቶ። እንግዲህ ግንበኞች የናቁት ድንጋይ እርሱ የማዕዘን ራስ ሆነ ተብሎ የተጻፈው ይህ ምንድር ነው? በዚያም ድንጋይ ላይ የሚወድቅ ሁሉ ይቀጠቀጣል፤ የሚወድቅበትን ሁሉ ግን ይፈጨዋል ስሰ። የካህናት አለቆችና ጻፎችም ይህን ምሳሌ በእነርሱ ላይ እንደ ተናገረ አወቀው በዚያች ሰዓት እጃቸውን ሊጭኑበት ፈለጉ፤ ነገር ግን ሕዝቡን ፈሩ።[2]

[2] ሉቃ20:9-19

ምዕራፍ ፩

(1) ንግግሥላቴ
ከዚህ እንደሰማችሁት ፣

የሰማነውን ነገር ማን አመነ?[3]

ንጉሡ፣ ሳይነጋ በሌሊት ከእንቅልፉ መቀስቀሱ ለደግ እንዳልሆነ ቢያውቅም፣ ይኼን ያህል አሰቃቂ ይሆናል ብሎ ግን አልጠበቀም። ፊቱ የቆመው አይሁዳዊ በገዛ ወገኖቹ እንዲህ በጭካኔ የመደብደቡ ሚስጥርም ምክንያታዊ ሊሆንለት አልቻለም። ሚስኪኑ ሰው ከግንባሩ ጀምሮ በጉንጮቹ፣ ወደ ታች እስከ አንገቱ ድረስ የፈሰሰው ትኩስና የረጋ ደም ብዙ ሰዓት የፈጀ ድብደባ እንደተፈጸመበት ይመሰክራል። በደም የጨቀየ ልብሱ፣ ወይን ሲረግጥ የቆየ አስመስሎታል። ከአናቱ መኻል እንደ ምንጭ ውኃ ሳያቋርጥ የሚቡለቀለቀውን ደም ሲያይ፣ እስከ አሁን በሕይወት መቆየቱና ቆሞ መሄዱ እጅግ አስገረመው፤ ድንገትም ከላይ እስከ ታች የሆነ ነገር ውስጡን ሲነዝረው ተሰማው። *«ግን ምን አድርጓቸው ይሆን እንዲህ የጨከኑበት?»* ሲል አሰበ።

ሰውየው፣ የሚሰብ ውበት ወይም ግርማ የለውም፤ ማንም የሚወደው መልክም ሆነ ደም ግባት አልነበረውም፤ ሰው ሁሉ ንቆ ያገለለው፣ ከመከራና ከሕመም የማይለይ፣ የሐዘን ሰው፣ እግዚአብሔር ጭምር የጨከነበት ነበር የሚመስለው። ሰዎች ፊታቸውን እስኪያዞሩበት ድረስ የተናቀ ነበርና ማንም አላከበረውም። ተጨነቀ ተሰቃየ፤ እንደ ጠቦት ለዕርድ ተነዳ፤ ይሁን እንጂ በሸላቾቹ ፊት ዝም እንደሚል በግ አፉን አልከፈተም። *«ምን አድርጓቸው ነው እንዲህ የጨከኑበት?»*

ንጉሡ ደግሞ፣ ደጋግሞ አሰበ። ግና፣ መቼም መልስ ያላገኘለት ከባድ ነገር ነበር ከአእምሮው ጓዳ ውስጥ ያረገዘው።

[3] ኢሳ53፡ በጠቅሳሳ። ማቴ፡ምዕ27። ሉቃ23። ዮሐ፡ምዕ18እና፡ምዕ19።

ከሕዝቡ የሚበዙት በቁጣ ሲጮኹበት፣ በጭካኔ ሲረግሙት ሲያይ፣ የከፋ በደል እንደፈጸመባቸው እርግጠኛ ወደመሆን ተቃርቦ ነበር። ሆኖም ማለዳ በፍርድ ወንበሩ ላይ እንደተቀመጠ ሚስቱ መልዕክት ልካ *«ለእርሱ ምክንያት ዛሬ ሌሊት በሕልም ብዙ ተሰቃይቻለሁና በዚያ ንጹሕ ሰው ላይ አንዳች እንዳታደርግ»* ያለችውን ሲያስታውስ ደግሞ ግራ ተጋባ። ትንሽ ቆይቶም የገዛ ወገኖቹ በቅናት ተነሳስተው ይኼን ሁሉ እንዳደረጉበት እንጂ፣ ምንም በደል እንዳልነበረበት አወቀ። ዳሩ ምን ያደርጋል? የተረዳውን ደፍሮ ተናግሮ በጽድቅ እንዳይበይን ስሙና ሥልጣኑ አሳሳው።

ሰውየው ግን የደረሰበት መከራና ስቃይ ከበቂ በላይ ቢሆንም ማንም የሚራራለት የለም፤ እንዲህ መድቀቁና መሰቃየቱ በእግዚአብሔር ፈቃድ እንደ ሆነ አስቀድሞ ተናግሮ ነበር አሉ፤ ከነፍሱ ስቃይ በኋላም የሕይወትን ብርሃን ያልማል፤ ይኼን እያሰበም ደስ ይሰኛል። ዓለም ሁሉ በእርሱ ላይ እጅግ ጨከነ፤ «አስወግደው. . . አስወግደው . . .» ከቅርብም ከርቀትም የሚሰማው ጩኸት ይኼው ብቻ ነው።

መከራውን ለመቋቋም ነክሶ የያዛቸው ጥርሶቹ ያን በመሰለ ስቃይ ውስጥ እንኳ ሆኖ የተፈጥሮ ሕግን ጥሰው ፈገግ ያሉ ይመስላሉ። የተሸነፈ ሰው የሚደርስበት ሁሉ እየደረሰበት ቢሆንም ፈገግታው ግን አሸናፊነቱን የሚያውጅ ነው። በድብደባ ብዛት አብጠው፣ በረጋ ደም የተሸፈኑት ዓይኖቹን በሕመም ገለጥ ሲያደርጋቸው ፍቅር፣ ምህረትና ርሕራሔ ይረጩና አቅም አጥተው ተመልሰው ይከደናሉ። ግን ምን ያደርጋል? በዚያ የተሰበሰቡት ሁሉ በጭካኔ ስለተሞሉ ይኼን፣ ልብ ስፍስፍ የሚያደርግ ክስተት ማንም አልተመለከተም። የዚያን ቀን ከሕያዋን ምድር እስኪወገድ ድረስ ከትውልዱ ማንም አላስተዋለም።

ይገርማል! እርሱ ግን እኮ ማንንም በጥላቻ አይመለከትም፣ በዚያ ጽኑ መከራ ሆኖ እንኳ፣ የእርግማንም ሆነ የምሬት ቃል ከአንደበቱ የሰማ ሰው የለም። ብቸኝነቱን ለተመለከተ፣ በምድር በኖረባቸው ዓመታት ያለ ወዳጅ ዘመድ የነበረ ሊመስለው ይችላል። እውነቱ ግን እንዲያ አልነበረም፤ እንዲያውም ከዚያ በፊት ታይቶ እስከማይታወቅ ድረስ

በገባበትና በወጣበት በፈቃዳቸው የተከተሉት አያሌ ደቀ መዛሙርት ነበሩት፤ ዛሬ ግን ብቻውን ነው። እርግጥ ነው፣ እናቱና ከሩቅ እየተከተሉ የሚያለቅሱ ጥቂት ሴቶች በዕለቱ ከእሱ ጋር ታይተዋል። ዳሩ ግን ማናቸውም ከአሰቃቂው ስቃይና መከራ ሊካፈሉትም ሆነ ሊያድኑት አልቻሉም።

ንጉሡ፣ ወደ ሰውየው ቀርቦ ጠየቀው፣

«አንተ የአይሁድ ንጉሥ ነህ እንዴ?»

«ንጉሥ እንደሆንኩ አንተም አመንህ ወይስ ሰዎች ስለነገሩህ ብቻ ነው የምትጠይቀኝ?»

«እኔ አይሁዳዊ ነኝ? የገዛ ወገኖችህ ወደ እኔ አመጡህ፣ ለመሆኑ ምን አድርገሃቸው ነው?»

«የእኔ መንግሥት ከዚህ ዓለም አይደለችም፤ መንግሥቴ ከዚህ ዓለም ብትሆን ኖሮ ሎሌዎቼ በተዋጉልኝ ነበር፣»

«ታዲያ ንጉሥ ነህ?»

«አንተ እንዳልከው ነኝ፣ እኔ የተወለድኩትና ወደ ዓለም የመጣሁት ስለእውነት ልመሰክር ነው፣ ከእውነት የሆነ ሁሉ ድምፄን ይሰማል»

«እውነት ምንድን ነው?»

ከዚህ በኋላ አንዳች አልመለሰለትም።

ንጉሡ ግን ከሰውየው ጋር የተነጋገረው ነገር ቀኑን ሙሉ እየከነከነው እንደ እግር እሳት ሲፈጀው ዋለ፣ ሆኖም ለሥልጣኑ ሰግቷልና፣ ንጹሑን ሰው ከስቅላት ሊያድን የሚችልበት አቅም አጣ። በዚያን ቀን ማድረግ የቻለው አንድ ነገር ብቻ ሲሆን፣ እሱም በአደባባይ እጁን ታጥቦ፣ ከሰውየው ደም ንጹሕ መሆኑን ለሁሉም ካስረዳ በኋላ ያሰቡትን እንዲፈጽሙ ለገዛ ወገኖቹ አላልፎ መስጠት ብቻ ነበር።

አቤት ጥድፊያ! አይሁዳውያኑ፣ ያን ጻድቅ ሰው ከምድር ለማስወገድ እንዲህ የቸኮሉት ለምን ይሆን?

ጎልጎታ ከተባለው ቦታ ሲደርሱ ከሐሞት ጋር የተቀላቀለ ወይን ጠጅ እንዲጠጣ ሰጡት፤ እርሱ ግን ቀምሶ ሊጠጣ አልፈቀደም። ከሰቀሉት በኋላ ዕጣ ተጣጥለው ልብሱን ተከፋፈሉ፤ ወታደሮቹም በተጠንቀቅ ቆመው ይጠብቁት ነበር። ሁለት ነፍሰ ገዳይ ዐመጸኛ ወንበዴዎችንም አንዱን በቀኝ፣ ሌላውን በግራ ከእርሱ ጋር ሰቀሉ፤ እናም ከዐመጸኞች ጋር ተቆጠረ። ከእነሱ አንዱ በመስቀሉ ላይ ሆኖ ሊሳለቅበት ይሞክር ነበር፤ በመንገድ የሚያልፉ በኃይል እየተሳደቡና ራሳቸውን እየነቀነቁ *«ቤተ መቅደስን አፍርሰህ በሦስት ቀን ውስጥ የምትሠራው እስቲ ራስህን አድን የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ በል ከመስቀል ውረድ»* ይሉት ነበር፤ የካህናት አለቆች፣ የኦሪት ሕግ መምህራንና ሽማግሌዎችም እያሾፉ *«ሌሎችን አዳነ፤ ራሱን ግን ማዳን አልቻለም የእስራኤል ንጉሥ ከሆነ አሁን ከመስቀል ይውረድ፤ እኛም እናምንበታለን። በእርሱ ታምኖ፣ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ይል ስለነበር፣ እስቲ ከወደደው አሁን ያድነው»* ሲሉ፣ እርሱ ግን «አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው» እያለ፣ ለሁሉ ይማልድ ነበር። ምን ዓይነት ነገር ነው? ሰዎቹ መስቀል ላይ ሆኖ እንኳ ሊራሩለት አልቻሉም። ግን ለምን . . .?

ንጉሡ *«ከደሙ ንጹሕ ነኝ»* ብሎ፣ እጁን በውኃ ቢታጠብም፣ እንደ እጁ፣ ኅሊናው ከቶ ሊነጻለት አልቻለም፤ በንጹሕ ሰው ደም እንደ ጨቀየም ወዲያው ታወቀው። ምንም እንኳ የረከሰ ኅሊናውን ማንጻት ባይችልም፣ ባለቀ ሰዓትም ቢሆን አንድ ያመነበትን እውነት ሰውየው ከሚሰቀልበት መስቀል በላይ ሊያኖርለት ወደደ። ጽሑፉም *«የአይሁድ ንጉሥ፣ የናዝሬቱ ኢየሱስ»* የሚል ሲሆን፣ በላቲን፣ በዕብራይስጥና በግሪክ ቋንቋ ተጽፎ፣ በዚያ ለሚያልፉ ሁሉ በግልጥ ይነበብ ነበር።

የአይሁዳዊው ከሳሾችም የተጻፈውን ሲያዩ እጅግ ተቆጡ፤ ወደ ንጉሡ ዘንድ ተመልሰውም *«አንተ የአይሁድ ንጉሥ ብለህ አትጻፍ፤ ነገር ግን "ይኼ ሰው እኔ የአይሁድ ንጉሥ ነኝ፣ ብሏል" ብለህ ጻፍ»* አሉት። ንጉሡ ግን እነርሱን የሚሰማበት ጆሮም ሆነ፣ ባደረገው ነገር ተጸጽቶ ሌላ የሚያደርግበት አቅም አልነበረውም። ስለዚህም ሰዎቹን ፊት ነሥቶ *«የጻፍኩትን ጽፌአለሁ»* ብሎ አሰናበታቸው። ስፍራው ቅርብ ነበርና ብዙ ሰዎች የተጻፈውን አዩ።

ከዚህ በኋላ መሲሁ፣ ከፍ ባለ ድምፅ ጮኸ፤ ነፍሱን ሰጠ። በዚህ ጊዜ የቤተ መቅደስ መጋረጃ ከላይ እስከ ታች ለሁለት ተቀደደ፤ ምድር ተናወጠች፤ አለቶች ተሰነጣጠቁ፤ መቃብሮች ተከፈቱ፤ አንቀላፍተው ከነበሩት ብዙ ቅዱሳን ተነሡ፤ ከመቃብርም በመውጣት ወደ ቅድስት ከተማ ገብተው ለብዙዎች ታዩ። የመሬት መናወጡንና የሆነውን ነገር ሁሉ ባዩ ጊዜ ብዙ ሰዎችም እጅግ ፈሩ፤ አንዳንዶችም *«ይህ ሰው በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነበር!»* አሉ።

ከዚያም በስውር ደቀ መዝሙር የነበረ አንድ ባለጠጋ ሰው ሥጋውን ይሰጠው ዘንድ ንጉሡን ለምኖ ስለተፈቀደለት፣ በንጹሕ የበፍታ ጨርቅ ከፈነው፤ ለራሱ ከዐለት አስፈልፍሎ ባዘጋጀው መቃብር ውስጥም አኖረው፤ ትልቅ ድንጋይ አንከባሎ መቃብሩን ዘግቶ ሄደ።

ይገርማል! በአፉ ተንኰል ሳይገኝበትና ምንም ወንጀል ሳይሠራ በአሚሚቱ ከክፉዎች ጋር ተቆጠረ፤ መቃብሩም ከባለጠጎች ጋር ሆነ።

በሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን ማለዳ ገና ጎህ እንደ ቀደደ አንዳንድ ሴቶች መቃብሩን ሊያዩ ሄዱ፤ አሳባቸውም እንደ አይሁድ ልማድ አስክሬኑን ሽቱ ለመቀባት ነበር። ከሴቶቹ ብዙዎቹ ያኔ ወደ መቃብር ሳይወርድ በፊት አያሌ ውለታ አድርጎላቸው ነበርና ሞቱም እንኳ «ጌታዬ» እያሉ ነበር የሚጠሩት። ሴቶቹ በስፍራው እንደ ደረሱ በድንገት ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ፤ የጌታም መልአክ ከሰማይ ወርዶ ወደ መቃብሩ በመሄድ ድንጋዩን አንከባሎ በላዩ ተቀመጠበት፤ መልአኩም መልኩ እንደ መብረቅ ብሩህ፣ ልብሱም እንደ በረዶ ነጭ ነበር። ጠባቂዎቹም መልአኩን ከመፍራት የተነሣ ተንቀጠቀጡ፤ እንደ በድንም ሆኑ።

ይህ ከሆነም ሁለት ሺ ዓመታት አለፉ። ኢየሱስም ሞትን አሸንፎ፣ ከመቃብር ወጥቶ፣ ወደ ሰማይ አርጎ፣ አያሌ ሰዎችን በፍቅር መማረኩን ቀጥሏል። ግን ለመሆኑ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲህ አምርራ የጠላችው ለምን ይሆን?

በበኩሌ ቅዱሱን መጽሐፍ ሳጠና ከተረዳኋቸው አያሌ ነገሮች አንዱ፣ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ የብዙሐን ድምፅ ታላላቅ ስህተቶችን

እንዳስከተለ ነው። እኔ ራሴ በዚህ ዘመን እንዲህ ማለቴ በራሱ በብዙ ሰው ዘንድ ተቀባይነት እንደማያስገኝልኝ አውቃለሁ። እስቲ ይኼን ተመልከቱ፣ ከመጀመሪያው የምድር ሕዝብ ሁሉ *(አዳምና ሔዋንን ማለቴ ነው)* ተሰበሰበና የእግዚአብሔርን የአገዛዝ ቀንበር በድምፁ አሽቀንጥሮ ጣለ። የባቢሎን ሕዝቦች ተስማምተው ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ ግንብ ለመሥራት ተነሡ፤ *(በነገራችን ላይ በአሳባቸው እንጂ፣ በሥራቸው መቼም ሊደርሱበት እንደማይችሉ ግልጥ ነው)* የዮሴፍ ወንድሞች በሙሉ ድምፅ ተስማምተው ዮሴፍን ለእስማኤላውያን ሸጡት። የእስራኤል ሕዝብ በሙሉ ተስማምቶ *«ከግብጽ ምድር ከባርነት ነፃ ያወጣን ይኼ ጥጃ ነው»* ብሎ፣ ለራሱ ጣኦት አቆመ። እንደገና እስራኤላውያን በሙሉ ተስማምተው *«እንደ አሕዛብ ዓይነት ንጉሥ ያስፈልገናል»* አሉ። የሰሜን እስራኤል ሕዝብ በአብላጫ ድምፅ ከደቡቡ መገንጠልን መረጡ . . . ። እንግዲህ ይኼንን ከመሳሰሉ ትርኢቶች በኋላ ነው፣ የዓለም ሃይማኖትና የፖለቲካ መሪዎች መሲሁ ኢየሱስን ሰቅለው የገደሉት። ከሕዝቡም አብላጫው በጉዳዩ ስለተስማማ «አሜን» አለ። በእኛም ዘመን እየሆነ ያለውን እውነት አስተውለን ካየነው ዛሬም ድረስ ዓለም በአብላጫ ድምፅ ውሳኔ ክርስቶስን እያሳደደች እንደሆነ እንገነዘባለን። ግን ለምን ይሆን?

ምናልባት አንድ ሰው፣ አብዛኛው ሕዝብ የክርስትና እምነት ተከታይ በሆነበት ዓለም፣ እንዴት ዓለም ክርስቶስን እያሳደደች ነው ትላለህ? ብሎ ይሞግተኝ ይሆናል። ግን እስቲ ልብ ብላችሁ እዩ፣ በአሁኑ ጊዜ ዓለም እየተከተለች ያለችው ክርስቶስን ወይስ ሃይማኖትን? ክርስቶስ ለዓለም ያበረከተው ሃይማኖት ወይስ ሕይወት? ከክርስቶስ ትምህርት ውጪ በግድ ከተደረቱ የሃይማኖት መገለጫዎች ብዙዎቹ ክርስቶስን የሚሸፍኑ ብቻ ሳይሆን ክርስቶስን የሚቃወሙ የመሆናቸው ሚስጥርስ ምንድነው? ደግሞም ብዙ ሰዎች ከክርስቶስ ይልቅ ዋጋ የሚሰጡት ለሃይማኖታቸው አይደለም እንዴ? ታዲያ የሰው ልማድና ሥርዓት በገነነበት በዚህ ዘመን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ተመልሶ ቢመጣ፣ ይህቺ ሃይማኖተኛ ዓለም መልሳ እንደማትሰቅለው ምን ማረጋገጫ አለ?

ምዕራፍ ፪

የመንግሥቱ ብርሃን

ሰሰው ሁሉ የሚያበራው እውነተኛ ብርሃን ወደ ዓለም ይመጣ ነበር[4] ..

ምድር በተፈጠረችበት ቀን ታላላቅ ችግሮች ተሸክማ ነበር፤ ስለዚህ እግዚአብሔር ከሁሉ አስቀድሞ «ብርሃን ይሁን» አለ። እንደ እኔ እምነት ይኼ ብርሃን የተፈጠረ ሳይሆን፣ የሁሉ ነገር ምንጭና መገኛ የሆነ «ፈጣሪ ብርሃን» በመሆኑ፣ ለሰው የሕልውናና የመኖሩ መሠረት ነበር። ይሁን እንጂ የሰው ልጅ በእግዚአብሔር ላይ ባመፀ ቀን ብርሃኑ ከምድር ፈቀቅ አለ።[5] ሆኖም ዓይኖቻቸው ከተከፈቱላቸው ጥቂት ሰዎች በቀር ብዙ ሰዎች በጨለማ መሆናቸውን አልተረዱም ነበር። እነዚህ በጨለማ መሆናቸውን የተገነዘቡ ጥቂቶች ግን ስለ ብርሃኑ ተመልሶ በሙላት መገለጥ በጭንቅ ሲያምጡ ቆዩ። ምክንያቱም ያ ብርሃን የሰው ሁሉ የሕይወትና የሕልውናው ምንጭ የነበረ በመሆኑ ነው። በዚህ መሻል ነብዩ ዳዊት «በጎውን ማን ያሳየናል? የፊትህ ብርሃን በላያችን ታወቀ፤ አባክህ ብርሃንህንና አውነትህን ሳክ፤ አነርሱም ይምሩኝ፣ ወደ ቅድስናህ ተራራና ወደ ማደሪያህ ይውሰዱኝ። የሕይወት ምንጭ ከአንተ ዘንድ ነውና፤ በብርሃንህም ብርሃንን አናያለን» ሲል፣ ከክርስቶስ ልደት ሰባት መቶ ዓመታት በፊት የተከሰተው ነብዩ ኢሳይያስ ደግሞ በጨለማ ውስጥ የሚጓዘው ሕዝብ ታላቅ ብርሃን እንደሚያይና በሞት ጥላ ለተቀመጡ ሁሉ ብርሃን እንደሚወጣላቸው አስቀድሞ ተነበየ።[6]

ቆይቶም የእስራኤል ምድር በሮማውያን በሚተዳደርበት ዘመን አንድ የተለየ ህፃን በዓለም ተወለደ፤ ህፃኑም ኢሳይያስ «ህፃን ተወልዶልናልና፣ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፤ አስቀነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ መካር፣ ኃያል አምላክ፣ የዘላለም አባት፣ የሰላም አስታ ተብሎ ይጠራል። ከዛሬ

[4] ዮሐ1:10
[5] የተሪሪው ትምህርት ገጽ 86ን ከነማብሪሪያው ይመለከቷል።
[6] መዝ 4:6፤ 36:9፤ 43:3። ኢሳ9:2።።9:6።።

ይምሮ አስከ ዘላለም ድረስ በፍርድና በጽድቅ ያጸናውና ይደግፈው ዘንድ በዳዊት ዙፋንና በመንግሥቱ ላይ አስቅነቱ ይበዛል፤ ስሰላሙም ፍጻሜ የለውም። የአግዚአብሔር ቅናት ይኼን ያደርጋል» **ያለለት ሲሆን፣ መጥምቁ ዮሐንስ ለእሱ መንገድ ለመጥረግ የተላከ ጽኑ ድምፅ ነበር። ሰዎችም ወደ ዮሐንስ እየመጡ «አንተ መሲሁ ነህ?» እያሉ ጠየቁት።** እርሱም «አነ መሲሁ አይደለሁም፤ አናንተ የማታውቁት ግን በመካከላችሁ ቆሟል፤ አኔ የጫማውን ጠፍር አንኳ ልፈታ የማይገባኝ ስሆን፣ አርሱ ከአነ በኋላ አየመጣ ነው፤ መንሹ በአጁ ነው። ስንዴውንም ከአንከርዳዱ ይለየዋል» ይል ነበር።

ዮሐንስ ቀድሞ እንደመሰከረው ለሰው ሁሉ የሚሆን እውነተኛ ብርሃን በዓለም ሁሉ ይበራ ጀመር። ዓለም ግን አላወቀውም፤ ሁሉ የሆነው በእርሱ ነው፤ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለእርሱ አልሆነም። በእርሱ ሕይወት ነበረች፤ ይህቺ ሕይወትም የሰው ብርሃን ነበረች፤ ብርሃኑም በጨለማ ይበራ ነበር፤ ጨለማም አላሸነፈውም። ወደ ራሱ ወገኖች መጣ፤ **የገዛ ወገኖቹ ግን አልተቀበሉትም። ዮሐንስ ግን** «ከአነ በኋላ የሚመጣው ከአነ በፊት ስለነበረ ከአነ ይልቃል ብዬ የመሰከርኩለት አሱ ነው» **በማለት ጮኾ ተናገረ።**

ብርሃንስ ወደ ዓለም መጣ፤ ሰዎች ግን ሥራቸው ክፉ ነበርና ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ወደዱ። ብዙዎቹ በውሸትና በግብዝነት የሚመላለሱ ስለነበሩ ወደብርሃኑ መምጣት አልፈለጉም፤ ይባስ ብሎ እውነተኛውን ብርሃን ከምድር ሊያስወግዱት ተጣደፉ። በዚህ መሻል አንዳንዶች ወደ ዮሐንስ መልዕክተኛ ልከው «ይኼ መሲሁ ነውን?» ብለው ጠየቁ። ለነገሩ ብርሃኑ እንኳ በግልጥ የሚታይ በመሆኑ የሰው ምስክርነት የሚያስፈልገው አልነበረም። በእርግጥ ዮሐንስ፣ እየነደደ ብርሃን የሚሰጥ መብራት ነበር እንጂ፣ ራሱ ብርሃን አልነበረም፤ ጥቂት ሰዎችም ለትንሽ ጊዜ በብርሃኑ ደስ ተሰኙ።[7]

> እርሱ የሚነድና የሚያበራ መብራት ነበረ፥ አናንተም ጥቂት ዘመን በብርሃኑ ደስ ሊላችሁ ወደዳችሁ።[8]

[7] ማቴ3:1-12፤ 14:1። ዮሐ1:20-26፤ ዮሐ3:19፤
[8] ዮሐ 5:33-35።

አንድ ጠዋት፣ የአሪት ሕግ መምህራንና ፈሪሳውያን በምንዝር የተያዘች ሴት ኢየሱስ ዘንድ አቀረቡ፤ ሴቲቱንም በሕዝብ ፊት አቁመው «መምህር ሆይ፣ ይህቺ ሴት ስታመነዝር ተያዘች፤ ሙሴም አንዲህ ያሉ ሴቶች በድንጋይ አንዲወገሩ በሕጉ አዞናል፤ አንተስ ምን ትላለህ?» ሲሉ ጠየቁት። ወንጌላዊው ዮሐንስ ስለዚሁ ጉዳይ ሲጽፍ ሰዎቹ፣ ይኼን ጥያቄ ያቀረቡለት እሱን የሚከሱበት ምክንያት ለማግኘትና ሊፈትኑት እንደሆነ ይነግረናል። ኢየሱስ ግን የልባቸውን ስላወቀ ምንም ሳይመልስላቸው ዝም አላቸው፤ በውትወታ ሲያስቸግሩት ግን ጎንበስ ብሎ በምድር ላይ ከጻፈ በኋላ «ከአናንተ ኃጢአት የሌለበት ቀድሞ ይውገራት» አለና ተመልሶ በምድር ላይ መጻፍ ጀመረ። በዚያን ቀን ኢየሱስ በምድር ላይ ምን እንደጻፈ ዮሐንስ አልነገረንም። የሴቲቱ ከሳሾች ግን ኢየሱስ የተናገረውን ሲሰሙ ከሽማግሌዎች ጀምሮ አንድ በአንድ ከዚያ ሄዱ፤ በሴቲቱም ላይ ማንም የፈረደባት አልነበረም። ኢየሱስም «አኔም አስፈርድብሽም፤ ደግመሽ ግን ኃጢአት አትሥሪ» ሲል በነፃ አሰናበታት።

የሴቲቱ ከሳሾች ፍላጎትና ጥማት እውነተኛ ጽድቅ ወይም ፍትህ ማግኘት አይመስልም፤ ሴቲቱን ወደ ኢየሱስ ያመጧት ምናልባትም፣ በሮማውያኑና በአይሁዳውያኑ ሕግ መኻል መፈናፈኛ ካሳጡት በኋላ የሚከሱበት አንዳች ምክንያት ማግኘት ብቻ ሊሆን ይችላል። ይኼም ማለት፣ ለምሳሌ ኢየሱስ ጉዳዩን በሙሴ ሕግ በኩል ተመልክቶ በድንጋይ እንድትወገር ቢበይን፣ በጊዜው ከነበረው የሮም መንግሥት ሕግ ጋር ስለሚጋጭ እርሱን የሮማውያን ተቃዋሚ አድርጎ ለማቅረብ ያመቻቸው ነበር፤ የጠቀሱለትን ሕግ ቸል ብሎ ሴቲቱን በነፃ ቢያሰናብታት ደግሞ ከአይሁዳውያን ጋር ለማጋጨት በቂ ምክንያት ያገኙ ነበር። በዚህም ሆነ በዚያ፣ የሰዎቹ ድርጊት ልባቸው ምን ያህል በክፋት እንደተሞላ የሚያሳይ ነው።

በመሠረቱ ሮማውያንም ሆኑ አይሁዳውያን በሕጉ ያኖሯቸው ድንጋጌዎች በራሳቸው መጥፎ ባይሆኑም፣ ሰዎቹ በክፉ ልብ ሆነው እስከተረጓሚቸው ድረስ በአፈጻጸም ችግር ማስከተላቸው አይቀርም። ይኼ ችግር የአይሁዳውያንና የሮማውያን ብቻ ግን አይደለም። ደግሞም ለዘመናት በዓለም ተንሰራፍቶ ከኖረው የጨለማ አሠራር

የሚመነጭ በመሆኑ መፍትሔው ኢየሱስ የዚያን ቀን ለሰዎቹ የነገራቸው ብቻ ነው።[9]

> «አኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፤ የሚከተለኝም የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ ከቶ በጨለማ አይመላለስም»

ከዚህ ቀጥሎ በሆነ ሌላ ታምር ኢየሱስ ዕድሜውን ሙሉ ዓይነ ስውር የነበረ ሰው ከፈወሰ በኋላ «በዓለም ሳለሁ የዓለም ብርሃን ነኝ» ሲል መናገሩን ያስታውሷል። በዕለቱ ሰውየው የበሩለት ሁለቱ የግንባር ዓይኖቹ ብቻ ሳይሆኑ ልቡ ጭምር ነበር። ፈሪሳውያን ግን ሰውየው በሰንበት መፈወሱን ምክንያት አድርገው ኢየሱስን ለመክሰስ ማስረጃ እንዲሆናቸው በጥብቅ ይወተውቱት ነበር። ሰውየው ደግሞ ከሥጋዊ ዓይኑ አልፎ ለልብ ዓይኑ ፈውስ ሆኖለት ስለነበር፣ አንዳቸውም እርሱን ሊቋቋሙ አልቻሉም፤ ስለዚህ ከምኩራብ አስወጡት። ኢየሱስ ይኼን በሰማ ጊዜ «ዕውሮች አንዲያዩ የሚያዩም አንዲታወሩ አኔ ወደዚህ ዓለም መጥቻለሁ» አለ። ፈሪሳውያንም ንግግሩን ሰምተው «ምን ማለትህ ነው? ታዲያ አኛም ዕውሮች መሆናችን ነው?» አሉ። እሱም «ዕውሮችስ ብትሆኑ ኃጢአት ባልሆነባችሁ ነበር፤ አሁን ግን አናያለን ስለምትሉ ኃጢአታችሁ አንዳስ ይኖራል» አለ።

ዛሬም ድረስ የብዙ ሰዎች ችግር ዕውሮች ሆነው ሳለ እንደሚያዩ አድርገው ማሰባቸው ነው። ይኼ ዓይነቱ ዕውርነት ግን ሥጋዊ ሳይሆን መንፈሳዊ ነው። ሆኖም ብዙ ሰዎች መለኮታዊ ፈውስ ለማግኘት ወደ እግዚአብሔር መቅረብ አይፈልጉም። እግዚአብሔር እስራኤላውያን ሰንበትን እንዲያከብሩ ያዘዛቸው ፍጹም የሆነችውን የመንግሥቱን እረፍት እንዲለማመዱ ሆኖ እያለ፣ እነሱ ግን ስለሰንበት የነበራቸው ትርጉም ሌላ ነበር። ስለዚህ አንድ ምስኪን ሰው ዕድሜውን ሙሉ ሲያስጨንቀው ከኖረ ዕውርነት ተፈውሶ እፎይ ማለቱ ምንም ትርጉም ሊሰጣቸው አልቻለም። ምናልባት የዚያን ቀን ከእነርሱ የአንዳቸው በግ ወይም ፍየል በጉድጓድ ወድቆ ቢሆን ኖሮ፣ *«ዛሬ ሰንበት ነውና ሳላወጣው ይደር»* ይሉ ነበር? የዚያን ቀን ኢየሱስ አይሁዳውያኑን የጠየቃቸው ይኼንኑ ነበር።

[9] ዮሐ8:11-12።

በሌላም በኩል ኢየሱስ አልአዛር የተባለ ወዳጁን ከሞት ካስነሣ በኋላ እነዚሁ ሰዎች ኢየሱስንና አልአዛርን ሊገድሉ የማሰባቸው ምስጢር ግራ ያጋባል። ኢየሱስ ግን ድምፁን ከፍ አድርጎ «ማንም በእኔ ቢያምን በእኔ ብቻ ሳይሆን በሳከኝ ማመኑ ነው፤ እኔን የሚያይ የሳከኝን ያያል። በእኔ የሚያምን በጨለማ እንዳይኖር ብርሃን ሆኜ ወደ ዓለም መጥቻለሁ» አለ።

ከእነዚህ ክስተቶች አንጻር ዓለም መሲሁን የጠላችበት ምስጢር ግራ ያጋባል። ሆኖም በእሱ የተገለጠው ብርሃን ለአያሌ ዘመናት በምድር ተንሰራፍቶ የነበረውን የጨለማ አሠራር እንደተጻረረው ግልጥ ነው። ክርስቶስ የእውነት፣ የፍትህና የጽድቅ ምሳሌ ነበር፤ በእርሱ ዘንድ ጨለማ የለም። በእርሱ ዓይን የትኛውም ሕግ፣ ሰውን ለማረቅና ወደ ፍጹምነት ለማምጣት እንጂ፣ ሌላውን ለመጉዳት ወይም ለማሳጣት የሚተረጎም አልነበረም። ክርስቶስ የተጋፈጣቸው መሪዎች ዘወትር የሚጨነቁት ለሥልጣንና ለሕልውናቸው ብቻ ነበር። ብዙ ጊዜም በአፋቸው የሚናገሩት፣ ከተግባራቸው ርቆ ከመታየቱም በላይ የገዛ ሕዝባቸውን እጅግ የሚጨቁኑና የሚያስመርሩ ነበሩ። ይኼም በእርሱ የጽድቅ መነጽር ሲታይ ልዩነቱ የትየለሌ ነው። ስለዚህ ዓለም የነበራት አማራጭ ሁለት ብቻ ሆነ፤ ወይ ከዚህ የጽድቅ ብርሃን ጋር ተስማምታ መኖር፤ አልያም ብርሃኑን ማጥፋት። የሚያሳዝነው ግን የመረጠችው ሁለተኛውን መንገድ መሆኑ ነው።

በሌላ በኩል፣ ክርስቶስ ራሱ ብርሃን ሆኖ በዓለም ያበራው ብርሃን የእግዚአብሔርን ማንነት የሚገልጥ ነበር፤ መቼም ቢሆን ያለክርስቶስ እግዚአብሔርን ማወቅ አይቻልም፤ በእርሱ በኩል ካልሆነ በቀር ጽድቅ፣ እውነትና ፍትህ የሚባሉትን ነገሮች ለመረዳት የማይታሰብ ነው። በአጭሩ ማንም ሰው ክርስቶስን የማያውቅ ከሆነ የሚኖረው በጨለማ ነው። «የዚህ ዓለም ገዢ» የተባለው የዲያቢሎስ ዋና ዓላማ፣ ሰዎች በክርስቶስ በኩል የተገለጠውን የወንጌል ብርሃን እንዳያዩ ልቦናቸውን ማሳወር ነው።[10] አሳዛኙ ነገር በዘመናት አያሌ ሰዎች በዚህ ጨለማ ውስጥ፣ ወደውና ፈቅደው መኖራቸው ነው። በዚህ

[10] 2ኛቆሮ4:1-6።

ጨለማ ውስጥ ደግሞ ሞት፣ አለማወቅና ዕውርነት ጸንቶ ይኖራል። መሪም ተመሪም ዕውራን በሆኑበት ዓለም፣ የሁለቱም ፍጻሜ ገደል መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነው።[11]

ዕውሮችን የሚመሩ ዕውሮች ናቸው፤ ዕውርም ዕውርን
ቢመራው ሁለቱም ወደ ጉድጓድ ይወድቃሉ።

[11] ማቴ15:14:

ምዕራፍ ፫

የመንግሥቱ ምስጢር

ምስጢር መግለጥ የሚችል የለም፣ ነገር ግን
ምስጢርን የሚገልጥ አምላክ በሰማይ አለ.[12]

ሰው የተፈጠረው፣ ምድርንና በውስጧ የሚኖሩትን ሁሉ በሥልጣኑ ስር እንዲገዛ ነበር። ይኼም በሰው በኩል የእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ የሚገለጥበት ዓይነተኛ መንገድ ነው። ሰው ግን በኃጢአት በመውደቁ ሥልጣኑ ተገፎ ሊኖር ተገደደ። ምክንያቱም የሰይጣንን ምክር ሰምቶ በአምላኩ ላይ ባመጸ ቀን፣ በፈቃዱ ሥልጣኑን ለሰይጣን አሳልፎ ሰጥቶት ነበርና ነው። እናም ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን፣ ሰይጣን የዚህ ዓለም ገዢ ተሰኝቶ ይኖራል።[13] እንዲያም ሆኖ እግዚአብሔር በዘመናት ለራሱና ለክብሩ የለያቸው ትሩፋን አጥቶ አያውቅም።

ከብዙ ዘመን በፊት እግዚአብሔር በአብርሃም በኩል ለክብሩ የለየውን «እስራኤል» የተባለ ዘር በአሕዛብ መኻል የተመረጠ ርስቱ አድርጎት ነበር። ሙሴም ለዚህ ሕዝብ በዓይነቱ ልዩ የሆነ ሕግና ሥርዓት ከእግዚአብሔር ተቀብሎ ሰጠው። ስለዚህም ሕዝቡ በዕለታዊ ኑሮው የአምላኩን ክብር በሙላት እየተረከ የተመረጠ ሕዝብነቱን ለሌላው ሕዝብ ወይም ለአሕዛብ መግለጥ ይጠበቅበት ነበር። ሕዝቡ ግን አምላኩ የሚጠበቅበትን ያህል ሊኖር አልቻለም። ከዚያም ቀጥሎ በመጀመሪያ የእስራኤል መንግሥት ለሁለት ተከፈለ፣ ቀጥሎም በተለያዩ ዘመናት በተነሡ የአሕዛብ መንግሥታት ተማረከ። ሕዝቡም እግዚአብሔር ምሎ ከሰጠው ርስቱ ተፈናቅሎ በባዕድ ምድር ሊኖር ተገደደ። ከምርኮ ከተመለሰ በኋላም በቅኝ ገዢዎቹ ተጽዕኖ ስር ቆየ።

[12] ዳን2:27፣28
[13] የሐ14:30።16:11።

ከእነዚያ ዘመናት በኋላ እስራኤላውያን ነፃ የሆኑት በጣት ለሚቆጠሩ ዓመታት ብቻ ነው። በመሆኑም ኢየሱስ ወደ ምድር ሲመጣ፣ ከዘመናት በፊት እንደነበሩት የዳዊትና የሰለሞን መንግሥት ዓይነት በተስፋ ይጠባበቁ ነበር። ሆኖም እርሱ የመጣበት መንገድ እነርሱ እንደሚያስቡት ስላልነበር በመንገድ ተላለፉ። በእርግጥ ጉዳዩ ኢሳይያስ ከተናገረው ትንቢት ጋር በቀጥታ የተያያዘ ነው።

ነቢዩ ኢሳይያስ በዘመኑ የእግዚአብሔርን አስደናቂ ክብር ከተመለከተ በኋላ «ማንን አልካከሁ? ማንስ ይሄድልኛል?»[14] የሚል ድምፅ ሲሰማ ፈጥኖ «አነሆ አነ አሄዳለሁ፣ አኔን ሳከኝ» ቢልም የተቀበለው አገልግሎት ግን ማንም የሚወደው ዓይነት አልነበረም። ምክንያቱም እግዚአብሔር «ወደዚህ ሕዝብ ሂድና መስማትን ትሰማላችሁ፣ ነገር ግን አታስተውሉም፤ ማየትን ታያላችሁ፣ ነገር ግን ልብ አታደርጉም በላቸው» ነበር ያለው። ስለዚህም ኢሳይያስ እስራኤል ሁሉ እንዳያይ ዓይኑን የመጨፈን፣ አንዳይሰማ ጆሮውን የማደንቆር፣ እንዳያስተውል ልቡን የማደንደን፣ አስቸጋሪ የሚባል አገልግሎት ማገልገል ነበረበት። ይኼም አገልግሎት እግዚአብሔር ለአገልጋዮቹ ከሰጣቸው አስቸጋሪ ተልዕኮዎች አንዱ እንደሆነ እገምታለሁ። ዳሩ ግን እርሱ እንዲህ እንዲሆን የወደደው እስራኤላውያን በዘመናት የተሰጣቸውን በርካታ ዕድሎች ሳይጠቀሙ በመቅረታቸው የተነሣ ነበር።

ከብዙ መቶ ዓመታት በኋላ እስራኤላውያን የመሲሁን የመወለድ ዜና በጆሮአቸው ሰሙ። ሥራውንም በዓይናቸው አዩ። ሆኖም ኢሳይያስ ቀድሞ እንደተናገረው በልባቸው ድንዳኔ ምክንያት ለመቀበል እንቢ አሉ። ይኼ ሳይበቃቸው ሮማውያን እንዲገድሉት አሳልፈው ሰጡት።

መላእክቱ የመወለዱን ዜና ያበሰሩት በሌሊት መንጋቸውን ሲጠብቁ ለነበሩ እረኞች ነው።[15] የምሥራቅ ኮከብ ቆጣሪዎችም የሚወለድበትን ዘመን አስልተው ኢየሩሳሌም ሲደርሱ፣ ህፃኑ ሊገኝ የሚችለው በቤተ መንግሥት ውስጥ እንደ ሆነ አስበው ነበር። ስለዚህ ንጉሡ ዘንድ

[14] ኢሳ 6፤9-11። እርሱም እንዲህ አለኝ፣ «ወደዚህ ሕዝብ ሂድ፣ «መስማትን ትሰማላችሁ...
[15] ሉቃ2:8-20

ቀርበው «የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው? ኮከቡን ከምሥራቅ ተመልክተን ልንሰግድለት መጥተናል» አሉ። ሄሮድስም ነገሩን ሲሰማ እጅግ ታወከ፤ የካህናት አለቆችንና የሕዝቡን የሕግ መምሕራን አስጠርቶ «መሲህ የሚወለደው የት ነው? ሲል ጠየቃቸው» እነርሱም «በይሁዳ ክፍለ ሐገር በቤተልሔም ከተማ ነው» በማለት ከትንቢታዊ ማብራሪያ ጋር ቢመልሱለትም ሀሣኑን ለመፈለግ ካሉበት ንቅንቅ አላሉም። ሰብአ ሰገል ግን ሀሣኑን ከእናቱ ጋር በበረት በግርግም ተኝቶ አገኙት። ሳጥናቸውን ከፍተው፣ የወርቅ፣ የዕጣንና የከርቤ ስጦታ አቀረቡለት።

ከኢየሱስ መወለድ ስድስት ወራት ቀደም ብሎ የተወለደው ዮሐንስ መጥምቁም ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ቀዳሚ አብሳሪ ነበር። ዮሐንስ፣ ራስ ወዳድነትንና ግፍን የሚቃወም፣ ፍትህን እውነትን የሚሰብክ፣ ትሁት፣ ጽድቅን የሚወድ፣ ማንንም የማይፈራ ደፋርና ታማኝ መልዕክተኛ መሆኑ በሁሉ ዘንድ ተመስክሮለታል። እስከ ሞቱ ድረስም በዚህ እውነት ጸንቶ ነፍሱን ዋጋ አድርጎ ከፍሏል።

በእርግጥ በነብዩ ኢሳይያስ እንደተነገረው ዮሐንስ፣ በበረሀ የሚጮህ ድምፅ ነበር፤ «የጌታን መንገድ አዘጋጁ፣ ጎዳናውን አቅኑ፤ ሸለቆው ሁሉ ይሞላል፤ ተራራውና ኮረብታው ሁሉ ዝቅ ይላል፤ ጠማማው መንገድ ቀና፣ ሸካራውም ጎዳና ትከከል ይሆናል፤ የሰውም ዘር ሁሉ የእግዚአብሔርን ማዳን ያያል» የሚል ድምፅ። ብዙዎች ሊጠመቁ መጡ፤ እሱም እንዲህ አላቸው «አናንተ የእፉኝት ልጆች፣ ከሚመጣው ቁጣ አንድትሸሹ ማን መከራችሁ? አንግዲህ ሰንስሳ የሚገባ ፍሬ አፍሩ፤ በልባችሁ "አብርሃም አባት አለን" ማለት አትጀምሩ፤ እግዚአብሔር ከአነዚህ ድንጋዮች ለአብርሃም ልጆች ማስነሣት እንደሚችል እነግራችኋለሁና። አሁን እንኳ ምሳር በዛፎች ስር ተቀምጧል፤ መልካም ፍሬ የማያፈራም ዛፍ ሁሉ ተቆርጦ ወደ እሳት ይጣላል።»

ከሕዝቡም መኻል ልባቸው የተነኩት «ምን እናድርግ?» ሲሉት «ሁለት ልብስ ያለው ለሌለው ያካፍል፤ ምግብም ያለው እንዲሁ ያድርግ» ሲል፣ ራስ ወዳድነትን እንዲጠየፉ አስተምሯል። ሁሉም በየተሰማሩበት ሥራ፣ ፍትህን እንዲያሰፍኑና መልካም የሆነውን ነገር ብቻ እንዲያደርጉ አሳስቧቸዋል፤ በዚሁ መሠረት ቀረጥ ሰብሳቢዎችን «ከተገቢው በላይ አትቅረጡ» ሲላቸው፣ በሮም መንግሥት ውስጥ ቁልፍ ቦታ የነበራቸው ጭፍሮችን ደግሞ «በማንም ላይ ግፍ አትስሩ፣ ማንንም በሐሰት አትክሰሱ፣

[መማሰጃ ጉቦ አትቀበሉ] ደመወዛችሁ ብቻ ይብቃችሁ» በማለት ያስጠነቅቃቸው ነበር። ሕዝቡ ሁሉ በዮሐንስ ስብከት ከመደነቃቸውም በላይ በምድር ላይ የተለየ የመንግሥት ሥርዓት እየመጣ እንደሆነ ስለጠረጠሩ «ክርስቶስ ይሆንን» ይባባሉ ነበር። ዮሐንስ ግን «አነስ በውኃ አጠምቃችኋላሁ፤ ነገር ግን የጫማውን ጠፍር መፍታት የማይገባኝ ከአኔ የሚበረታ ይመጣል፤ እርሱ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃችኋል። መንሹም እጁ ነው፤ አውድማውንም ፈጽሞ ያጠራል፤ ስንዴውን በጎተራው ይከታል፤ ገለባውን ግን በማይጠፋ እሳት ያቃጥለዋል» ይላቸው ነበር። ደግሞም በብዙ ሌላ ቃል እየመከረ የመሲሁን መንግሥት እንዲጠባበቁ ቀሰቅሷል።[16]

ዮሐንስ መጥምቁ በፍልስጥኤም ምድር «መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንሰሀ ግቡ» በማለት መስበክ ከጀመረ ከጥቂት ወራት በኋላ ኢየሱስ ከእርሱ ጋር ፍጹም አንድ ዓይነት ትምህርት እያስተማረ መጣ። በወቅቱ የሁለቱ ትምህርት አንድነት ብዙዎችን ቢያስደንቅም፣ የኢየሱስ ትምህርት በሥልጣንና ኃይል የተሞላ መሆኑ ሮማውያኑንም ሆነ አይሁዳውያኑን ክፉኛ ያስደነገጠ ነበር። ኢየሱስ ስለዮሐንስ በተናገረ ጊዜ ከሴት ከተወለዱ ነብያት መኻል እሱን የሚስተካከለው እንደሌለ ሲመሰክር፣ በመንግሥተ ሰማያት ግን ከሁሉ የሚያንሰው እንደሚበልጠው መናገሩ እጅግ የሚገርም ነው። በእርግጥ ዮሐንስ በሞቱ ዋዜማ ኢየሱስ፣ እርሱ ክርስቶስ ስለመሆኑ መጠነኛ ጥርጣሬ ገብቶት የተፈተነ ቢሆንም፣ ከጌታ ዘንድ የተላከለት መልዕክት ግን ልቡን እንጸባረፈው ይታመናል። በዚያን ቀን ኢየሱስ፣ ለዮሐንስ የላከለት መልዕክት «ሂዳችሁ ያያችሁትንና የሰማችሁትንም አውሩለት፤ ዕውሮች ያያሉ፤ አንካሶችም ይሄዳሉ፤ ለምጻሞች ይነጻሉ፤ ደንቆሮዎች ይሰማሉ፤ ሙታን ይነሣሉ። ለድሆችም ወንጌል ይሰበካል፤ በእኔም የማይሰናከለው ሁሉ ብጹዕ ነው» የሚል ሲሆን እነዚህ ነገሮች ደግሞ የመሲሁ መንግሥት ወደ ምድር መቅረብ ወይም መምጣት ዋነኛ ምልክቶች ነበሩ።[17]

[16] ሉቃ3:12-18።
[17]ማቴ11:5።

እርግጥ ነው፣ በዚያ ዘመን የነበሩ የአይሁድ ልሂቃንም ሆኑ ተራው ሕዝብ የእግዚአብሔር መንግሥት አንድ ቀን በብዙ ታምራት ታጅባ በኢየሩሳሌም እንደምትመሠረት ተስፋ በማድረግ ይጠባበቋት ነበር፤ በተጨማሪ መንግሥቱን ሊመሠርት መሲሁ ቀድሞ መምጣት እንደሚገባው ተረድተዋል። ይሁን እንጂ እርሱ ሲመጣ የወቅቱ ልዕለ ኃያል መንግሥት የነበረውን የሮም ስርወ መንግሥትን ገርስሶ ጥሎ፣ እነርሱን በ«አሕዛብ» ሁሉ ላይ የበላይ ገዢ አድርጎ እንደሚሾማቸው በመጠበቃቸው ኢየሱስ፣ እርሱ የናፈቁት መሲህ ወይም ክርስቶስ መሆኑን ለማመን ተቸግረዋል። ክርስቶስን ግን ወደ ምድር የመጣው እንደዳዊትና ሰለሞን ዓይነት ምድራዊ መንግሥት ሊመሠርት ወይም ለሰው ልጅ ተጨማሪ ሃይማኖት ሊፈጥር አልነበረም። በእርግጥ ክርስቶስ በእሱ ለሚያምኑ የተለየ መንግሥት እንደሚሰጥ ቃል ገብቷል። ለዚህም በአንድ ወቅት «አንተ ታናሽ መንጋ፣ መንግሥትን ሊሰጣችሁ የአባታችሁ በጎ ፈቃድ ሆኗል» ማለቱን መጥቀስ ይበቃል። ይሁን እንጂ፣ ይህቺ መንግሥት ማንም እንዲህ በቀላሉ የሚገነዘባት አልነበረችም።

ኢየሱስ በተወለደበት ዘመን የነበረው ንጉሥ ሄሮድስ ከሰብአ ሰገል በሰማው ነገር ስለታወከ ሊገድለው አስቦ ነበር፤ እግዚአብሔር ደግሞ ለዮሴፍ ተገልጦ እንዲሸሽ ስለነገረው፣ ህፃኑንና እናቱን ይዞ ወደ ግብጽ ተሰደደ። ሄሮድስም ዕድሜአቸው ሁለት ዓመትና ከዚያ በታች የሆኑ፣ በቤተልሔምና በአካባቢው የተወለዱ ወንድ ህፃናትን ሁሉ በጭካኔ አስገደለ። ከተወሰነ ዓመት በኋላ ሄሮድስ ራሱ ስለሞተ፣ የጌታ መልአክ ለዮሴፍ እንደገና ተገልጦ *«ህፃኑን የሚያሳድዱት ሁሉ ሞተዋልና ወደእስራኤል ተመለስ»* አለው።

ኢየሱስ አገልግሎት የጀመረው በገሊላ ሲሆን፣ ይኼም በምድረ በዳ ውስጥ የአርባ ቀን ጾምና ጸሎት አድርጎ በዲያቢሎስ ከተፈተነ በኋላ የሆነ ነው። ከዚያ በኋላ በቀጥታ ወዳደገበት ናዝሬት ሄደ፣ እንደ ልማዱም በሰንበት ቀን ምኩራብ ገባ፣ ሊያነብም ተነሣ።[18] የዕለቱ የምንባብ ክፍልም ከነቢዩ የኢሳይያስ መጽሐፍ በተለይ ስለመሲሁ

[18] 4:1-11። ማር 1:12:13፣ ሉቃስ 4:1-13

መምጣትና ተግባር የሚያወሳው ክፍል ነበር።[19] ሁሉም ነገር ግን በአጋጣሚ ሳይሆን ከዘመናት በፊት በተወሰነው መሠረት የሆነ ነው።

> የጌታ የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ላይ ነው፣ ስድኾች የምሥራች እንድሰብክ፣ እግዚአብሔር ቀብቶኛል። ልባቸው የተሰበረውን እንድጠግን፣ ለምርኮኞች ነጻነት፣ ለእስረኞች መፈታትን እንዳውጅ ልኮኛል፣

ክፍሉን ካነበበ በኋላ መጽሐፉን ለአስተናባሪው ሰጠና በስፍራው ሄዶ ተቀመጠ፤ በምኩራብ የነበሩት ሕዝብ ግን ትኩር ብለው ይመለከቱት ጀመር፤ ስላነበበውም ክፍል አንዳች እንዲናገር ፈልገው እንደነበር ግልጥ ነው። ምናልባትም ከዚያ በፊት በሌሎች ምኩራቦች ያስተማረው ትምህርት ዝና በዚያም አገር ቀድሞ ተሰምቶ ይሆናል። እርሱም «አነሆ አሁን ሲነበብ የሰማችሁት የመጽሐፍ ቃል ዛሬ ተፈጸመ» በማለት ያልጠበቁትን የምስራች አበሰራቸው። ምንም እንኳ ከዚያ በፊት ካዩዋቸው መምህራን ሁሉ ኢየሱስ የተለየ እንደ ሆነ ቢረዱም፣ አይሁዳውያኑ ግን አስተዳደጉን፣ ቤተሰቡንና ሙያውን ስለሚያውቁ ብቻ፣ ለዘመናት ሲናፍቁት የነበረው የትንቢት ቃል በእርሱ በኩል ፍጻሜ እንዳገኘ አምነው ለመቀበል ከበዳቸው። ኢየሱስ ግን የልብ አሳባቸውን አውቆ «አንተ ሐኪም፣ አስቲ ራስህን አድን፣ የሚሰሙን ምሳሌ እንደምትጠቅሱብኝ እርግጠኛ ነኝ፣ አንዲሁም፣ በቅፍርናሆም አድርገህል ሲሉ የሰማነውን ሁሉ እዚህም በገዛ አገርህ አድርግ፣ ትሉናላችሁ። በእውነት አሳችኋለሁ፣ ነቢይ በገዛ አገሩ ሰዎች ዘንድ አይከበርም» አላቸው። አይሁድ ግን ይኼን በማለቱ እጅግ ተቆጥተው እየጎተቱ ወደ ገደል አፋፍ ወሰዱት፤ ገፍትረውም ሊጥሉት ፈልገው ነበር፤ ሆኖም ጊዜው ገና አልደረሰም ነበርና በመኻላቸው አልፎ ሄደ። ይኼም ከሰተት ኢየሱስ ካደገ በኋላ ዓለም እሱን ያሳደደችበት የመጀመሪያው ቀን ሆኖ ተቆጠረ።

በትምህርቱና ዕለት፣ ዕለት በሚያደርገው ታምራት ዓለም ተደነቀ። በልዩ ልዩ ደዌና በአጋንንት እስራት የተያዙ ሰዎች እርሱ ወዳለበት ሲመጡ እየራራ በፍቅርና በነፃ ፈውሶ ይልካቸው ነበር። ለምጻሞችን

[19] ሉቃ414-19

አነፃ፣ ሽባዎችን ተረተረ፣ ልምሾዎችን ፈታ፤ ዕውራንን አበራ፣ ጎባጣ አቀና፤ ለአያሌ ዓመታት የአልጋ ቁራኛ የደዌ ዳኛ የነበሩ ሰዎችን አልጋ አሸክሞ ላከ፣ ብዙ ሰዎችም የልብሱን ጫፍ ለመዳሰስ ይለምኑት ነበር፤ የዳሰሱትም ሁሉ ዳኑ። በየትኛውም ዘመን ከነበሩ «አዋቂ» ወይም «ባለመድሃኒቶች» ሁሉ ይልቅ እርሱ ብቻውን የብዙ ሰዎችን እንቆቅልሽ ፈታ። ስለዚህ በአንዳንድ ከተሞች የሚኖሩ ሰዎች ከእነርሱ ጋር ለሁልጊዜ እንዲኖር ወደው «አትሂድብን» ይሉት ነበር።

አያሌ ሰዎች በትምህርቱ እየተደነቁ በየዕለቱ ይሰሙት የነበረ ቢሆንም፣ ስለማንነቱና ሥልጣኑ ቀድመው የተረዱት ግን አጋንንቶች መሆናቸው እጅግ ይገርማል። አነሱም «የናዝሬቱ ኢየሱስ ሀይ ከእንተ ጋር ምን አስን? ልታጠፋን መጣህን? አንተ ማን እንደሆንክ እኛ እናውቃለን፤ አንተ አኮ የእግዚአብሔር ቅዱስ ነህ» እያሉ ሲጮኹ፣ ዝም እንዲሉ እያዘዘ ገስጾ ያወጣቸው ነበር። መናፍስቱን በሥልጣን ሲያስወጣ ያዩትም «ይህ ምን ዓይነት ነገር ነው?» ተባባሉ። በአጭር ጊዜ ዝናው ምድርን ሞላ፤ ሕዝቡም ከአንደበቱ በሚወጣው የጸጋ ቃል እየተገረሙ ስለእርሱ በጎ ነገር ይነጋገሩ ነበር።[20] ግን ደግሞ መልሰው «ይህ የዮሴፍ ልጅ አይደለምን? እናቱና ወንድሞቹን የምናውቃቸው አይደሉምን?» ይሉት ነበር። ይህ እንዴት ግራ የሚያጋባ ነገር ነው?

በበረት የተወለደ፣ ሄሮድስን ፈርቶ ወደ ግብጽ የተሰደደ፣ በሰዎች እጅግ የተናቀውን የአናጢነት ሥራ እየሠራ በድህነት የኖረ *«ደግ ነገር የማይበቅልባት»* በተባለችው በናዝሬት ከተማ እንደ ተራ ልጅ ያደገ፣ ከማንም ያልተለየ ልብስ ለብሶ ከሕዝቡ ጋር እንደማንኛውም ሰው በእግሩ የተጓዘ፣ ሌላው ሰው የሚበላውን እየበላና እየጠጣ አብሮ የኖረ፣ የሰው ጀልባና አህያ ተውሶ የመለሰ፣ ማንም እንደፈለገ ሲሰድበውና ሲዘብትበት ሰምቶ እንዳልሰማ ዝም ያለ. . . *«በእርግጥ፣ ይህ ሰው የእስራኤል ሁሉ የልብ ናፍቆት የሆነው መሲህ ነው»* ብለው እንዴት ይቀበሉት?! ግና፣ ኢየሱስን ባልተቀበሉ ሰዎች ላይ መፍረድ ምንኛ ከባድ ነገር ነው! በእኛ ዘመን እንኳ የክርስቶስን ድንቅ

[20] ሉቃ4:34-35። ማር1:21-28። ሉቃ4:22-27። ሉቃ4:28-30።

አገላለጥ ብቻውን መቀበል የቸገራቸው፣ አንዳንድ «መምህራን» በሚተርኳቸው አያሌ አፈ ታሪኮችና በደረሷቸው ድርሳናት፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰው ቢሆንም፣ በአስተዳደጉና በአኗኗሩ ግን የተለየ የመለኮት ተጽዕኖ እንደነበረው ለማስረዳት በብዙ ሲደክሙ ይታያሉ። ከእነዚህ መካል . . .

በልጅነቱ ለእናቱ እንጨት ሲለቅም፣ በንፋሳት አስሮ በደመናት በመጫን ያመጣላት እንደነበር፣ ከልጆች ጋር ሲጫወት በብርሃን ጨረር ላይ ይንጠለጠል እንደነበር፣ ለእናቱም በወንፊት አሳት ከጎረቤት ይጭርላት እንደ ነበር፣ እንደ ልጅ ጭቃ እያበላ ሲጫወትም የእርሱን ጭቃ እፍ ብሎ የሕይወት እስትንፋስ እየሰጣት ያበራት እንደነበር፣ ይሼን ያዩ የልጅነት ጓደኞቹ እንደ እርሱ ለማድረግ ሲሞክሩ የአየር ቧንቧቸው እየፈነዳ ይሞቱ እንደነበር፣ በዚህ የተቆጡ ወላጆችም በንዴት ደረቱን ቢደቁት ጊዜ፣ ቀሰር እንደገደላቸው፣ . . . [21]

እየተባለ የሚነገረውን መጥቀስ ይበቃል። እነዚህ ሁሉ ታሪኮች ደግሞ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካለው አሳብ ጋር ፍጹም የሚቃረኑ ናቸው። እንዲያውም የኢየሱስ ክርስቶስን እንደማንኛውም ህፃን ማደግና መኖር የሚያስተባብሉ በመሆናቸው በብዙዎቻችን ዘንድ ተቀባይነት የላቸውም። ዳሩ ግን እነዚህ የሃይማኖት «መምህራን» ይሼን ያህል መድከማቸው የኢየሱስን ፍጹም አምላክነት ወይም ከሰው የላቀ መሆን ለሌሎች በማስረዳት እጅግ ሊያከብሩት ፈልገው ነው። ታዲያ በዚህ ዘመን ያለን ሰዎች እንኳ የእርሱ በሰው ምሳሌና ግብር መገለጥ እንዳለ ለመቀበል እንዲህ የሚያስጨንቀን ከሆነ፣ በዚያ ዘመን በዓይነ ሥጋ የተመለከቱት አይሁዳውያን ቢጠራጠሩት ወይም ጨርሶ ባያምኑበት ምን ያስገርማል?

ሮማዊው ንጉሥ ጲላጦስ፣ በመረመረው ጊዜ ከወዴት እንደሆነ እንዲነግረው ጠይቆት ነበር፤ እርሱ ግን አንድ ስንኳ አልመለሰለትም፤ ስለዚህ «ልሰቅልህ ወይም ልፈታህ ሥልጣን አንዳለኝ አታውቅምን?» በማለት

[21] ተአምረ ኢየሱስ፡ ገጽ 48፣ 55፣ 66፣ 67 እና 73። ወይም 145፣ 175፣ 205፣ 215 እና 245 ታመር።

ሊያስፈራራው ሞከረ። በዚህ ጊዜ «ከሳይ ካልተሰጠህ በቀር በእኔ ሳይ ምንም ሥልጣን ባልነበረህ፤ ስለንተ አሳልፎ የሰጠኝ ግን ኃጢአቱ የባሰ ነው» ከማለት በቀር ምንም ቃል ሳይናገር ዝም አለ። እንዲያም ሆኖ ንጉሡ ሊፈታው ፈልጎ ነበር፤ ሕዝቡ ግን «ብትፈታውስ የቄሳር ወዳጅ አይደለህም፤ ራሱን ንጉሥ የሚያደርግ ሁሉ የቄሳር ተቃዋሚ ነው» እያለ ስለጮኸ፣ ፍርሃት አደረበት። ሆኖም በክርስቶስ ላይ የሞት ፍርድ መፍረድ ስላልወደደ ተጨማሪ ዕድል መስጠት ፈለገ። ኢየሱስን ወደ ውጪ አውጥቶ «እነሆ ንጉሣችሁ» አሳቸው። አይሁድ ግን «ከቄሳር በቀር ንጉሥ የለንም አሱን ግን አስወግደው፤ አስወግደው» እያሉ አብዝተው ጮኹ። ኃጢአቱ የከፋውን በርባን በፊታቸው ሲያቆመው ከበርባንስ ይልቅ ኢየሱስን ፍታልን እንደሚሉ ተስፋ አድርጎ ነበር። ሕዝቡ ግን *«በርባን ቢፈታ ይሻለናል»* በማለት አጽንተው ጮኹ። እንግዲህ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ነበር እንደሚታረድ በግ ጌታ ወደ መስቀል ሞት የተጓዘው። *ታዲያ «ጲላጦስ ቢሆን ከዚህ የተሻለ ምን ሊያደርግለት ይችላል?»* ብለን መጠየቃችን አግባብ ይሆን?

ደቀ መዛሙርቱም ብዙ ጊዜ ስለ መንግሥቱ ጠይቀውታል፤ ያዕቆብና ዮሐንስ በእናታቸው አማላጅነት መንግሥቱን በመሠረተ ጊዜ በቀኝና በግራ ያስቀምጣቸው ዘንድ ተማጥነውታል፤ እርሱ ግን «የምትለምኑትን አታውቁም፤ በቀኝና በግራ መቀመጥ ስተሰጣቸው ነውና» የሚል የተሟሳጽ መልስ ከመስጠቱ በቀር በልባቸው ውሸጥ ይንገዋለል ለነበረው ጥያቄ የሚፈልጉትን ያህል መልስ ሰጥቶአቸዋል ለማለት አይቻልም። ሌላው ቀርቶ ከሞት ተነሥቶ ወደ ላይ ከማረጉ ጥቂት ሰዓት በፊት አስራ ሁለቱ ወደ እርሱ ቀርበው «ለአስራኤል መንግሥትን የምትመልሰው መቼ ነው?» የሚል ወሳኝ ጥያቄ አቅርበውለት ነበር። አሁንም «አብ በገዛ ሥልጣኑ የወሰነውን ጊዜና ዘመን አናንተ ልታውቁት አትችሱም፤ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በአናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበሳላችሁ፤ በዚያን ጊዜ በኢየሩሳሌም በይሁዳ፣ በሰማርያ፣ አስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ» ሲል፣ ከጥያቄው ጋር የማይገናኝ የሚመስል ተስፋ ነበር የሰጣቸው።

ኢየሱስ መንግሥቱን በተለያየ ምሳሌ መስሏታል፤ በምሳሌዎቹም ስለ ባህርይዋ፣ ለሰዎች ስላላት ፋይዳ፣ እንዲሁም ከእርሷ አንጻር የሚገለጠው የክፉው ተጽዕኖና ማንም ሰው እሷን ለማግኘት ሊከፍል

ስለሚገባው ዋጋ ተንትኖ አስተምሮአል። የኢየሱስ ምሳሌዎች እጅግ አስገራሚ ከመሆናቸውም በላይ ለየትኛውም ዕድሜና ጾታ፣ ኑሮና የሙያ ሁኔታ የተመጠኑ ሆነው መቅረባቸው በእሱ ዘንድ ምን ያህል ዋጋ እንደተሰጣቸው የሚያስገነዝብ ነው።[22] እንዲያም ሆኖ ግን ምሳሌዎቹን ማንም በቀላሉ ሊረዳቸው የሚችሉ አልነበሩም። ደቀ መዛሙርቱም ስለምሳሌው ምንነት ቀርበው በጠየቁት ጊዜ «ስአናንተ የመንግሥተ ሰማያት ምስጢር ማወቅ ተሰጥቷችኋል» ብሏቸዋል።

ከእነዚህ ምሳሌዎች አንዱ «የዘሪው ምሳሌ» በመባል የሚታወቀው ነው፤ ኢየሱስ በዚሁ ምሳሌው በእግዚአብሔር መንግሥት የተዘራው ሁሉ እንደማይበቅልና እንደማይጸና ነው የተናገረው። በዚሁ መሠረት የመንግሥቱን ቃል ለአንዳንድ ሰዎች በጎዳና ላይ እንደ ወደቀ ዘር ነው የሚሆንባቸው። እነዚህ ሰዎች ቃሉን ሰምተው እንዳያስተውሉ ወይም እንዳይቀበሉት በወፍ የተመሰለው ክፉ ወይም ሰይጣን ከልባቸው የተዘራውን ወዲያው ለቅሞ ይወስደዋል። አንዳንድ ሰዎች ደግሞ የመንግሥቱን ቃል ሲሰሙ ለጊዜው በደስታ ይቀበላሉ፤ ሆኖም ልባቸው እንደ ጭንጫ መሬት ጥልቀት ስለሌለው በቃሉ ምክንያት ስደት ወይም መከራ ሲመጣባቸው ፈጥነው ይሰናከላሉ። አንዳንድ ሰዎችም በልባቸው የተዘራው ቃል የተወሰነ ያህል ቢያድግም፣ ለዚህ ዓለም ኑሮና ባለጠግነት ከሚሰጡት ግምት የተነሣ ከእሾህ ጋር እንዳደገ ዘር ፍሬ እንዳያፈራ ታንቆ ይቀራል። ከእነዚህ ሁሉ መኻል ያልሆነውና ጸንቶ የተገኘው ዘር ግን ብዙ ፍሬ አፍርቶ ይታያል።

በኢሳይያስ የተነገረው «መስማትን ትሰማላችሁ፣ አታስተውሱም፤ ማየትንም ታያላችሁ፣ አትመለከቱም» የሚለው ትንቢት በተለይ የሚመለከተው አይሁዳውያንን ቢሆንም፣ ሌላውን ሕዝብ ጨርሶ አይጠቅስም ማለት ግን አይቻልም። በዚያ ላይ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ «ስአናንተ ግን የመንግሥተ ሰማያትን ሚስጥር ማወቅ ተሰጥቶአችኋል» ካለ በኋላ ከሌሎች መሰወሩን ለመግለጥ የጠቀሰው ይኼንኑ የትንቢት ክፍል መሆኑ ጉዳዩ የትናንት ብቻ ሳይሆን፣ የዛሬም ጭምር እንደሆነ

[22] እነዚህ ምሳሌዎች በማቴ13: ላይ ይገኛሉ።

የሚያስገነዝብ ነው። በመሆኑም ከዚህ የኢየሱስ ገለጣ ተነሥተን ዓለምን ሁሉ *«የመንግሥቱን ምስጢር ማወቅ የተሰጠው ያልተሰጠው እንዲሁም ተሰጥቶት ያልተጠቀመበት»* በማለት መፈረጅ እንችላለን።[23]

እግዚአብሔር የመንግሥቱን ሚስጥር የገለጠው በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ብቻ ነው። ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ሆኖ ሳለ፣ ራሱን ባዶ አድርጎ በፍጹም ሰውነት በምድር የተገለጠበት ምክንያት የእግዚአብሔርን መንግሥት በሰው ዘንድ እንደ ገና ሊመሠርት ስለወደደ ነው። በእርግጥ ፍጹም መልኩንና ባሕርይውን በእቅፉ ያለው ልጁ እስኪተርከው ድረስ እግዚአብሔርን ማንም ያየው አልነበረም፤ ምንም እንኳ በቀድሞ ዘመናት ለአባቶች፣ በተለያየ ጊዜ በነብያት በኩል እየተገለጠ የተናገረ ቢሆንም፣ በዚህ የዘመን መጨረሻ የሁሉ ነገር ወራሽ ባደረገው በልጁ አስኪናገር ድረስ ብዙ ነገሮች ምስጢር ነበሩ። ኢየሱስ የእግዚአብሔር ክብር ነጸብራቅና በባሕርይውም ከአባቱ ጋር ፍጹም ትክክል ነው። ከጥንት እስከ ዛሬ ዓለምን ሁሉ ሥልጣን ባለው ቃሉ ደግፎ የያዘውም እርሱ ነው፤ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር እንዳይቀርቡ ይከለክላቸው የነበረውን የዕዳ ጽሕፈትና ኃጢአት ሁሉ በደሙ ከደመሰሰ በኋላ፣ በአሁኑ ጊዜ ዓለም ሳይፈጠር በነበረው ክብር ከአባቱ ቀኝ ተቀምጧል። ወደፊት እንዲሆን በተቀጠረ አንድ ቀንም የወጉት አያዩት በዓለም ላይ ሊፈርድ ተመልሶ ይመጣል።[24]

አንድ ሌሊት ከፈሪሳውያን ወገን የአይሁድ አለቃ የሆነ ኒቆዲሞስ የሚባል ሰው ወደ ኢየሱስ ዘንድ መጥቶ ነበር። ኢየሱስም ለዚህ ሰው ስለእግዚአብሔር መንግሥት መሠረታዊ እውነት ነገረው። ኢየሱስና ኒቆዲሞስ ካደረጉት ንግግር የምንረዳው ሁነኛ ምስጢር፣ ማንም ሰው የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጋ ለመሆን የሚፈልግ ከሆነ የግድ ዳግመኛ መወለድ እንዳለበት ነው። ካለዚያ ግን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ ቀርቶ እርሷን ማየት እንኳ አይችልም። ይሁን እንጂ «ዳግም መወለድ» የሚባለው ነገር በመንፈስ ቅዱስ በኩል

[23] ማር 4:11-12 እና ማር 8:17-18። ያነጻጽሯል።
[24] ዕብ1:1-3። ራዕ1:7። ዮሐ19:37።

የሚከናወን ሚስጥራዊ ውልደት እንጂ፣ በሥጋና በደም የሚሆን ወይም ከወንድና ከሴት ፈቃድ የሚፈጸም አይደለም። በእርግጥ ስለነገሩ ሚስጥር ኢየሱስ ሲያስረዳው ኒቆዲሞስ ራሱ በመጀመሪያ ኣጅግ ግራ ተጋብቶ ነበር። ጥቂት ቆይቶ ግን ጉዳዩ ምን ማለት እንደ ሆነ የገባው ይመስላል። ለዚህም በአንድ ወቅት ፈሪሳውያን በክርስቶስ ላይ ፍርደ ገምድል ውሳኔ ሊያሳልፉ በነበረበት ጊዜ የመለሰላቸውን መጥቀስ ይበቃል። ከዚህ በተረፈ ከአርማቲያሱ ዮሴፍ ጋር ሆኖ የኢየሱስን ሥጋ ከተሰቀለበት አውርዶ በክብር ማሳረፉ በራሱ ስለ ዳግም መወለድና የእግዚአብሔር መንግሥት ጉዳይ አንዳች የተረዳው ነገር እንዳለ የሚያመለክት ነው።

እርግጥ ነው፣ ይኼ «እንደገና ተወለዱ» የሚለው የክርስቶስ አዲስ ትምህርት ከአይሁዳውያኑ ይልቅ ለአሕዛብ ጥቅመ- የበለጠ ነው። ተስፋው በተለይ ቀድሞ «አሕዛብ» ለተባልነው ለእኛ የላቀ ክብር የሚያቀዳጅ እንዲሁም አሕዛብንም ሆነ አስራኤልን በእኩል የሚያይ በመሆኑ ለዘመናት የኖረውን የአይሁዳዊት ትምክህት ከመሠረቱ የሚያናጋ ሆኗል። እንደሚታወቀው አስራኤላውያን የእግዚአብሔር ምርጥና ቅዱስ ሕዝብ ነበሩ። ዳሩ ግን አሕዛብ በክርስቶስ በኩል፣ ከምሥራቅና ከምዕራብ መጥተው ከአብርሃም፣ ከይስሐቅ፣ ከያዕቆብና ልጆቻቸው ጋር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የመግባት ዕድል አግኝተዋል። በጽድቃቸው ከሚታመኑት ከእነዚያ ከተመረጡ ሕዝቦች ይልቅ በሩቅ የነበሩ ኃጢአተኞች ወደ መንግሥቱ ቀድመው መግባታቸው እንዴት ድንቅ ነው?!

ይህ ሲባል ግን ወደ መንግሥቱ የገባ ሰው ሥርዓት የሌለው ይሆናል ማለት ግን አይደለም። በመሠረቱ የእግዚአብሔር መንግሥት የራሱ የሆነ ሕግና ሥርዓት ያለው ነው። ቃሉ «እርሱ ከጨለማ ሥልጣን አድነን፣ በዛነቱንም አርሱንም የኃጢአትን ስርየት ወዳገኘንበት ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግሥት አፈሰሰን» ነው የሚለው። ከዚህ አንጻር በዚህች መንግሥት ውስጥ ፍቅር ትልቅ ስፍራ አላት። በተለይም «አምላክህ አግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹም አሳብህ፣ በፍጹም ኃይልህ ውደድ። ባልጀራህንም እንደ ራስህ ውደድ» የሚሉት ሁለት ትዕዛዛት፣ ሕግና ነብያት ሁሉ

የተሰቀሉባቸው ናቸውና በአዲሱ ሰው ዘንድ የተለየ ትኩረት የሚደረግባቸው ናቸው::

ወደዚህች መንግሥት ገብቶ ለዘላለም ሊኖር የሚሻ ሰው፣ ከውሳኔው ጀምሮ በሁሉ ነገር ታማኝ ሆኖ መገኘት ይጠበቅበታል:: አስፈላጊም ከሆነ ስለመንግሥቱ ክብር ያለውን በሙሉ ለመተው ፈቃደኛ መሆን ይኖርበታል:: ደግሞም ቤቱን ወይም ወላጆቹን ወይም ወንድሞቹንና እኅቶቹን ወይም ሚስቱና ልጆቹን ለተወ፣ በሰማይም ሆነ በምድር ታላቅ ብድራት እንዳለው በጌታ ትምህርት ተመልክቷል:: ስለጽድቅ መሰደድ፣ ከፈሪሳውያንና ከጻፎች በላቀ የሕይወት ልክ መገኘት፣ በመንፈስ ድሀ መሆን፣ እንደ ህፃን ንጹሕ መሆን፣ ከመንግሥቱ ዜጎች የሚጠበቅ የሕይወት ሥርዓት ነው::[25]

[25] ማቴ5- 12::ዮሐ3:1-13::

ምዕራፍ ፩

የመጣችሁ
የምትመጣዋ መንግሥት

አይሁዳውያን ከብዙ ጊዜ በፊት ጀምሮ የእግዚአብሔርን መንግሥት መገለጥ በተስፋ እየናፈቁ ይጠባበቁ እንደነበር ከዚህ በፊት በስፋት የተመለከትነው ጉዳይ ነው:: መጥምቁ ዮሐንስና ጌታ ኢየሱስ ተከታትለው ወደ ምድር በመጡ ጊዜ ስለዚሁ ጉዳይ አብዝተው መናገራቸውም አይተናል:: በዕለተ ሆሳዕና፣ በኢየሩሳሌም በሚኖሩ አይሁዳውያን ዘንድ የነበረው የፈንጠዝያ በዓል ሰበብም ለዘመናት የናፈቋት የእግዚአብሔር መንግሥት በመኻላቸው እንደሆነች አስበው እንደነበር ግልጥ ነው:: የዚያን ቀን ሕዝቡ ሁሉ «በጌታ ስም የምትመጣ የአባታችን የዳዊት መንግሥት የተባረከች ናት» እያሉ ይጮኹ ነበር:: በቀናት ልዩነት ያው ሕዝብ እንደገና ጲላጦስ ዘንድ ቀርቦ ኢየሱስን «ስቀለው፣ ስቀለው» ማለቱም በእርሱ መሲህነት ተስፋ ስለቆረጠ ይመስላል:: ሆኖም ግን በመስቀል ሳለ እንኳ በመንግሥቱ በመጣ ጊዜ እንዲያስበው አብሮት ከተሰቀሉት ወንበዴዎች አንደኛው ይለምነው ነበር:: እርሱም «ጌታ ሆይ በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ» ነበር ያለው:: ደግሞም በሴራቸው ያልተባበረና የጌታን ሥጋ ወስዶ ለራሱ ባሠራው የመቃብር ስፍራ ያኖረው የአርማትያሱ ዮሴፍ የእግዚአብሔርን መንግሥት ይጠባበቅ የነበረ ሰው እንደነበር መጠቀሱ፣ በአሁድ ግንባረሰብ ዘንድ ስለጉዳዩ የቱን ያህል ናፍቆትና መጓጓት እንደነበር ያሚያስረዳ ነው::

ኢየሱስ የመንግሥቱን ወንጌል ከመስበኩ ጎን ለጎን በሕዝቡ ያለውን ደዌና ሕመም ሁሉ እየፈወሰ በከተማና በመንደሮች ሁሉ ይዞር ነበር:: እርሱም ከሰዎች እርኩሳን መናፍስት ሲያወጣ «የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለች» በማለት ይነግራቸው ነበር:: ከሕዝቡ አንዳንዶች ግን እንደሆነ አውቀው ሲከተሉት፣ የአይሁድ የሃይማኖት መምህራን

ግን «አጋንንት አስበት፤ ጋኔሎችንም የሚያወጣው በአጋንንት አሰቃ ነው» እያሉ እርሱንም ሆነ በእርሱ የተገለጠውን ታምር ለመቀበል አልወደዱም:: ኢየሱስም «አኔ በአግዚአብሔር መንፈስ አጋንንትን ማውጣቴ የአግዚብሔር መንግሥት ወደ አናንተ መቅረብ ምልክት ነው» ሲላቸው፣ ከመጥምቁ ዮሐንስ ዘመን ጀምሮ መንግሥተ ሰማያት እየተገፋች እንደሆነች፣ ነገር ግን ግፈኞች እንደሚናጠቋትም አበክሮ ይነግራቸው ነበር::

ደቀ መዛሙርቱን ለአገልግሎት ሲልካቸውም «በየደረሳችሁበት ያሉ ድውዮችን ፈውሱ፤ በዚያም የአግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለች፤ ብላችሁ ስበኩ» ከማለቱ በተጨማሪ፣ በሰጣቸው የተለየ ፀጋና ኃይል አጋንንት እንዲያወጡና በሽተኞችን እንዲፈውሱ አግዟቸዋል:: ምናልባት ፈጽሞ የማይቀበላቸው ሰው ቢገጥማቸው፣ የእግራቸውን ትቢያ አራግፈው ከከተማው እንዲወጡ አሳስቧቸዋል:: እነርሱም ተመልሰው «አጋንንት አንኳ በሰምህ ተገዙልን» ቢሉት «ስማችሁ በሰማይ ስለተጻፈ አንጂ አጋንንት ስለተገዙላችሁ ደስ አይበላችሁ» ነበር ያላቸው::[26]

ኢየሱስ ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት በእግሩ ተተክተው እንዲያገለግሉ የሾማቸው ሐዋርያት የአገልግሎታቸው ዋና ማዕከል የአግዚአብሔር መንግሥት ጉዳይ እንደነበር ከመልዕክቶቻቸው መረዳት ይቻላል:: ምንም እንኳ እነዚህ ሰዎች በስፍራው ሁሉ ስለስሙ ጽኑ መከራ ቢደርስባቸውም «ወደ አግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ አንገባ ዘንድ ያስፈልገናል» እያሉ እርስ በርስ ከመጽናናት በቀር ወደ ኋላ ሲሉ አልታዩም:: ደግሞም በስብከታቸውም ሆነ በትምህርታቸው ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደ ሆነ አጽንኦት ሰጥተው ይናገሩ ነበር::

እንደው ለመሆኑ የእግዚአብሔር መንግሥት የመጣችው እንዴት ነው? የምትመጣውስ በምን ሁኔታ ነው? የዚህ መጽሐፍ ትኩረት ይኼ ጉዳይ እንደ መሆኑ ከዚህ ቀጥሎ ባሉት ክፍሎች አስቀድሞ የመጣችዋን ለጥቆም የምትመጣዋን በስፋት እንቃኛለን::

[26] ሉቃ 8:1:: 10:20::

በእነዚያ ዓመታት «ፈሪሳውያን» የሚባሉት የሃይማኖት መሪዎች ወደ ኢየሱስ ቀርበው «የአግዚአብሔር መንግሥት መቼ ትመጣለች» ሲሉ ጠየቁት፤[27] እርሱም «የአግዚአብሔር መንግሥት ሰዎች በሚጠባበቁበት መንገድ አትመጣም፤ ደግሞም አነኋት በዚህ፣ ወይም አነኋት በዚያ፣ የምትባል አይደለችም፤ አነሆ የአግዚአብሔር መንግሥት በመካከላችሁ ናትና» በማለት መለሰላቸው:: ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ «ከሰው ልጅ ቀኖች አንዱን ለማየት የምትመኙበት ወራት ይመጣል፤ አታዩትምም:: አነርሱም አነሆ በዚያ ወይም በዚህ ይሏችኋል፤ አትሂዱ አትከተሏቸውም:: መብረቅ በርቆ ከሰማይ በታች ካለ ከአንድ አገር፣ ከሰማይ በታች ወዳለው ሌላ አገር አንደሚያበራ፣ የሰው ልጅ በቀኑ አንዲህ ይሆናል:: አስቀድሞ ግን ብዙ መከራ አንዲቀበል፣ ከዚህም ትውልድ አንዲጣል ይገባዋል» አላቸው:: የኖኅንና የሎጥን ዘመን በዋቢነት ጠቅሶ ወደፊት ምን እንደሚሆን ተናግሯል:: ይህን ክፍል በአንክሮ የሚያስተውል ማንም ሰው ኢየሱስ ስለመጣችውና ስለምትመጣዋ መንግሥት እየተናገረ እንደነበር ለመረዳት አይቸገርም::

በአጭሩ፣ የመጣችዋ መንግሥት ኢየሱስ በተወለደ ጊዜ ወደ ምድር የመጣች ስትሆን፣ እስከ አሁንም በቤተ ክርስቲያን በኩል ሕያው ሆና የምትኖር ናት፤ ጌታም «ገና ወደፊት የምትጠባበቋት ሳትሆን በመኻላችሁ ናት» ማለቱ የሚያስረግጠው ይኼንኑ ነው:: ቤተ ክርስቲያንም እስከጊዜው ድረስ ከዚህ ዓለም መንግሥታት ጋር ጎን ለጎን የምትጓዝ ናት እንጂ እንደ እስራኤል መንግሥት በምድራዊ ቤተ መንግሥት የምትወሰን አይደለችም:: ተጽዕኖዋም መንፈሳዊ እንጂ፣ በመልክአ ምድር ቅርጽ የሚለካ ሆኖ አያውቅም:: በአንጻሩ የምትመጣዋ የእግዚአብሔር መንግሥት፣ በኢየሱስ ዳግም ምጽአት ጊዜ ገና የምትገለጥ ስትሆን ዘላለማዊትና ፍጹም ናት::[28] ከሁሉም አስደሳቹ ነገር ደግሞ እርሷ በምድር ላይ በሙላት በምትገለጥበት ወራት የምድር መንግሥታት ጎልውና ለዘላለም የሚያከትም መሆኑ ነው::

[27] ሉቃ 17:20-25
[28] ዳን 2:44

ምዕራፍ ፭

፭ መጠንቀቂያዋ መንግሥትና እና ቤተ ክርስቲያን

ፈሪ፣ ችኩል፣ ከሃዲ፣ ወላዋይ፣ ሽንበቆ . . . ሌላም፣ ሌላም፣ ለቀደመው ሕይወቱ ከስሙ በፊት ቅጥያ የሆኑለት ምስኪን ሰው ነበር። ምክንያቱ ግልጥ ባይሆንም አባቱ ያወጣለት ስም ትርጉም በራሱ ሽምበቆ መሆኑ ሰውየው ጽኑ ያይደለ ወይም የሚዋልል ባህርይ እንደ ነበረው ነው የሚናገረው። አንድ ማለዳ ግን ኢየሱስ ተከተለኝ ሲለው ሳያንገራግር ከተከተለው በኋላ ስሙ ተለውጦ «ዐለቱ» ለመባል በቃ። ይህ ሰው «የዮና ልጅ ስምአን» ወይም «ጴጥሮስ» የሚባለው ነው። መቼም ስምአን ጴጥሮስ በመቸኮሉ፣ በመጣደፉና በተደጋጋሚ በመሳቱ ነበር የሚታወቀው። በተለይ አንድ ቀን የሠራው ስህተት አይረሳም። ባደረገው ነገር ተጸጽቶ መራራ እንባ አስኪያነባ ድረስ፣ መምህሩንና ጌታውን በአደባባይ ካደ። ነገር ግን ከእርሱ ድካም ያለፈ አስደናቂ ጸጋና ምህረት ከፊቱ ስለጠበቀው በሕይወት ተርፎ በርትቶ ታየ። መንፈስ ቅዱስ በወረደ ቀን ኢየሱስ፣ እርሱ ክርስቶስ መሆኑን ደፍሮ በአደባባይ[29] «አናንተ የሰቀላችሁት ኢየሱስን አግዚአብሔር ጌታና መሲህ አንዳደረገው የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ አሁን ይወቅ» ሲል ሰበከ። በዚህ ሰው ሕይወት ውስጥ ይኼን የመሰለ ዓይነተኛ ለውጥ ያመጣው ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ነበር።

መንፈስ ቅዱስ የወረደበት ቀን በቤተ ክርስቲያን ዘንድ በልዩ ሁኔታ የሚታሰብ ነው። ምንም እንኳ መሠረቷ የተጣለው በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ቢሆንም፣ ሥራዋን በይፋ የጀመረችው ግን በበዓለ አምሳ፣ ማለትም መንፈስ ቅዱስ በወረደበት ቀን ነው። በዚያ ላይ ቤተ ክርስቲያን አንድ የሃይማኖት ተቋም ብቻ ሳትሆን ወደ ምድር

[29] የሐ1፡42::ማቴ16:18::26:69-75::ማር 14:66-72::ሉቃ 22:55-62::የሐ 18:16-18:25-27::ሐዋ2:1-42::

ቀድማ ለመጣችው የእግዚአብሔር መንግሥት ፍጹም መገለጫ እንደ ሆነች መርሳት አይገባም። ይህ ሲባል ግን እያንዳንዱ አማኝ በግሉ የመንግሥቱ እንደራሴ መሆኑን መዘንጋት የለብንም። በክርስቶስም ሆነ በሐዋርያት ትምህርት «ቤተ ክርስቲያን» የተባለው ህንፃውና ድርጅታዊ ተቋሙ ሳይሆን የአማኞች ጎብረት ነው። እያንዳንዱ አማኝ ግን የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነው። የእነዚህ ሁሉ ቤተ መቅደሶች ጎብረት የወል መጠሪያ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ክብሯና ልዕልናዋ እንዴት ታላቅ ነው!

ጌታ ኢየሱስ በትምህርቱ ስለመንግሥቱ የተለየ ትኩረት ይሰጥ እንደ ነበር ባለፉት ክፍሎች ተመልክተናል። የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ጸሐፊያንም ስለጉዳዩ ደጋግመው ጽፈዋል። ለዚህም ከሃያ ሰባቱ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ከአንድ መቶ አምሳ ጊዜ በላይ የመንግሥቱ ጉዳይ በአንድ ወይም በሌላ መንገድ መነሣቱን መጥቀስ ይበቃል። በነዚህ ክፍሎች የተዘረዘሩት አሳቦች በጥቅሉ ሲታዩ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጎች በምድር ላይ ምን ዓይነት የሕይወት ሥርዓት መከተል እንደሚገባቸውና የሚያጋጥሟቸውን ተግዳሮቶች የሚተነትኑ ሲሆኑ፣ ዜጎች ዘላለማዊ ለሆነችው ሰማያዊት መንግሥት እንዴት መዘጋጀት እንደሚገባቸው በዝርዝር ያስረዳሉ።

አማኞች ወይም ክርስቲያኖች የመንግሥቱን እውነቶች በሕይወታቸው እስከገለጡ ድረስ፣ የመጣችዋን መንግሥት ለዓለም አውን ማድረግ ከመቻላቸውም በላይ ለምትመጣዋ መንግሥት ተስፋ እንዳለ ሕያው ምስክር ለመሆን ይችላሉ። በአንጻሩ ትምህርቶቹን ቸል ብለው፣ ከተሰመረላቸው ሥርዓት ፈቀቅ ያሉ እንደሆን፣ ሲኦልን ወይም ገሃነመ እሳትን በምድር ማየት ለማንም ቀላል ይሆናል። ምንም እንኳ አሁን በዓለም ላይ በስፋት የሚታየው ኃጢአት፣ ክፋት፣ ግፍ፣ በደል. . .የመሳሰሉት አስከፊ ነገሮች ተወግደው፣ ጽድቅ፣ እውነት፣ ፍቅር፣ ፍትህ፣ ሰላም. . . የሚባሉት መልካም ነገሮች ሊሰፍኑ የሚችሉት ወደፊት ፍጹም የሆነችው የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር ስትመሠረት ቢሆንም፣ እነዚህ ነገሮች እስከዚያው ድረስ አውን የሚሆኑት ግን የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ለዓለምና ለምድር

ማበርከት ወይም መሆን የቻሉትን ያህል ብቻ ነው። ከዚህ በተረፈ በዓለም ላይ ምንም ዓይነት ደንብና ሥርዓት ቢደነግግ ወይም ምንም ዓይነት ስም ያለው የአመራር ዘይቤ ቢዘረጋ፣ ፍጹም ሰላም፣ ፍቅርና ፍትህ የሰፈነበት መንግሥት በምድር ሊመሠረት አይችልም።

በበኩሌ አንዳንድ አማኞች ለምድር መንግሥታት አክራሪ ደጋፊ ወይም ተቃዋሚ መሆናቸው እጅግ ያሳስበኛል። በውሳጣቸው ባለው ጭፍን ጥላቻና ፍቅር ምክንያት በጎውን ለማየት ከፋውንም ለመጠየፍ የማይችሉ «አማኞች» ነገረ ሥራም አይገባኝም። እርግጥ በምድር ካሉ ባለሥልጣናት መኻል አንዱ እንኳ ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ ወደሥልጣን የወጣ የለም። እያንዳንዱ በዘመኑ በሠራው ሥራ ተመዝኖ ይኼ፣ ከዚያኛው ይሻላል ቢባል እንኳ የሁሉም መሠረትና ፍጻሜ ግን አንድ ነው። እንዲያውም እንደ ትንቢተ ዳንኤል ያሉ መጻሕፍት ከእያንዳንዱ የምድር መንግሥታት ጀርባ የሚሠራ አለቃ መንፈስ እንዳለ ፍንጭ ይሰጠናል።[30] ከዚህ አንጻር ለጊዜው ብቻ ከሚከሰቱ ምድራዊ መንግሥታት ጋር በጽኑ ፍቅርም ሆነ ጥላቻ መውደቅ፣ ፍጻሜን ከማክፋት ባለፈ የሚፈይደው ነገር የለም።

ክርስቲያኖች ከምድራዊ መንግሥታት ጋር ላላቸው ግንኙነት አንድ ዓይነት ሚዛን ሊኖራቸው ይገባል። ይኼም ሚዛን በየትኛውም ዘመን በሁሉም ዓይነት የመንግሥት ሥርዓት እንዲሠራ ከተፈለገ ከክርስቶስ ባሕርይ አንጻር መቃኘት አለበት። የክርስቶስ መንግሥት የቅንነት በትር ያለው ነው። ኢየሱስም እንደ ፍጹም ሰውነቱ ከምድር ሰዎች ሁሉ ልቆ የተገኘው ጽድቅን በመውደዱ፣ ዐመጻን በመጥላቱ ነው።

> ዙፋንህ እስከ ዘላለም ድረስ ይኖራል፤ የመንግሥትህ በትር የቅንነት በትር ነው። ጽድቅን ወደድህ ዓመፅንም ጠላህ፤ ስለዚህ አግዚአብሔር አምላክህ ከጓደኞችህ ይልቅ በደስታ ዘይት ቀባህ። [31]

ሆኖም ክርስቲያኖች በእነርሱ ዘመን በሥልጣን ላይ ላሉ የምድር ባለሥልጣናት ከልብ እንዲገዙና እንዲታዘዙ የእግዚአብሔር ቃል

[30] ዳን10:13። የፋርስ መንግሥት አስቃ ግን. . .
[31] ዕብ.1:8-9

አበክሮ ያዛል። ለዚህም ከሁሉ አስቀድሞ ባለሥልጣናት ሁሉ የተሾሙት በእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ እንደሆነ ማወቅ በራሱ ትልቅ ብልህነት ነው። ደግሞም ማንም ይሁን ማን የምድር ባለሥልጣናትን የሚቃወም ሰው፣ የሚቃወመው የእግዚአብሔርን ሥርዓት ነው። ይሁን እንጂ ክርስቲያኖች ለመንግሥት የሚታዘዙትና የሚገዙት ትጣትንና ቁጣን በመፍራት ሳይሆን፣ ከጌታ ዘንድ ስለተሰጣቸው ኃጢአ ሕሊና ጭምር ነው። ለመንግሥታት የሚገባውን ግብርም ሆነ ቀረጥ መክፈል፣ መከበር የሚገባውን ማክበር፣ መፈራት የሚገባውን መፍራት፣ ፍጹም መንፈሳዊነት ነው።

አማኞች ግን በምድራዊውና በሰማያዊው መንግሥታት መኻል እንዴት ባለ ሥርዓት መኖር እንዳለባቸው በጥንቃቄ ሊያጤኑት ይገባል። ደግሞም አይሁዳውያን፣ ጌታ ኢየሱስን በዚሁ ነገር ሊያጠምዱት ፈልገው ከሄሮድስ ወገን የሆኑ ሰዎች ልከውበት እንደ ነበር አትርሱ። ሰዎቹም መልካም በሚመስሉ የሽንገላ ቃላት ካወደሱት በኋላ አንድ መሰሪ ጥያቄ ጠይቀውት ነበር።

> እንግዲህ ምን ይመስልሃል? ንገረን አስቲ፣ ሰቄሳር ግብር መስጠት ተፈቅዷልን ወይስ አልተፈቀደም? አሉት። ኢየሱስ ግን ክፋታቸውን አውቆ አናንተ ግብዞች ስለምን ትፈታተኑኛላችሁ? የግብሩን ብር አሳዩኝ አሳቸው፤ እነርሱም አንድ ዲናር አመጡለት። እርሱም፣ ይህች መልክ ጽሕፈቱስ የማን ናት? አሳቸው፤ የቄሳር ነው አሉት። በዚያን ጊዜ እንኪያስ የቄሳርን ለቄሳር የእግዚአብሔርንም ለእግዚአብሔር አስረክቡ አሳቸው[32]

ከዚህ አንጻር፣ ለመንግሥትና ለእግዚአብሔር በሚሆነው መኻል በጥራት መለየት ይጠበቅብናል። በእርግጥ ቤተ ክርስቲያንም ሆነች አማኞች በክርስቶስ ላይ ባላቸው እምነት ምክንያት አንዳንድ የምድር መንግሥታት ሥርዓቶችን ፊት ለፊት በመቃወማቸው እስከ ዛሬ ድረስ ብዙ ዋጋ ሲከፍሉ እንደ ኖሩ ታሪክ ምስክር ነው። የአዲስ ኪዳን መጽሐፍት የመጀመሪያ ተደራሲያን የሆኑት አማኞችም በሮም

[32] ሮሜ13:1-6።።ማቴ22:17-22

ጽኑ የጭቆና አገዛዝ ቀንበር ስር የነበሩ ከመሆኑ አንጻር የመልዕክቱ ትርጉም ለእነርሱ የተለየ እንደሚሆን አያከራክርም። በዚያ ላይ ኢየሱስ ክርስቶስና ሐዋርያቱን ጨምሮ፣ አያሌ ደቀ መዛሙርት የተገደሉት በዚሁ መንግሥት በኩል በቀጥታ በተላለፈ ጭካኔ የተሞላ ትዕዛዝ መሆኑን መዘንጋት የለብንም። ዳሩ ግን እስከ መጨረሻው ድረስ ከዚህ እውነት ማናቸውም ፈቀቅ አላሉም። ለነገሩ እነዳንኤል በባቢሎንና በሌሎች መንግሥታት ስር ያን ሁሉ መከራ እየተቀበሉ በነበረባቸው ዘመናት እንኳ ለነገሥታቱና መንግሥታቸው የነበራቸው አክብሮት ምን ያህል ታላቅ እንደነበር ስናስተውል በእኛ ዘመን ለመንግሥታት መገዛት እጅግ ቀላል ሆኖ እናገኘዋለን። ምንም እንኳ መጽሐፉ ደጋግሞ አማኞች ለሚታየው የሰዎች መንግሥት መገዛት እንዳለባቸው ቢናገርም በያዙት እውነት እንዲደራደሩ ግን ምንም ዕድል አልተወም። በቤተ ክርስቲያንና በዓለም መንግሥታት መኻል ያለውን የልዩነት ገደብ መርሳት ወይም ቸል ማለት አይገባም።[33]

ቤተ ክርስቲያን ወደ ምድር ከመጣች በኋላ ባሉት ሦስት መቶ ዓመታት በራስዋ መንግሥት የአገዛዝ ጥላ ስር ሆና በቀረው ዓለም ላይ መሠረታዊ የሚባል ተጽዕኖ ስትፈጥር እንደኖረች ይወሳል። ደግሞም በየዕለቱ ብዙ ሰዎች በክርስቶስ እያመኑ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይጨመሩ ነበር። ዳሩ ግን በእነዚያ ዘመናት ከነበሩ የሮም ቄሳሮች አብዛኛዎቹ የክርስትና ተቃዋሚዎች የነበሩ በመሆናቸው ክርስቲያኖች ስለእምነታቸው ምክንያት ከተራቡ አውሬዎች ጋር እንዲታገሉ፣ በሕይወት እያሉ ወደ እሳት እንዲጣሉና የመላሰሉት የጭካኔ ድርጊቶች እንዲፈጸምባቸው ይደረግ ነበር። ሆኖም የአማኞቹ ጽናት አስገራሚ ከመሆኑ በላይ ብዙዎቹ ታማኝነታቸውን በሞታቸው ጭምር አረጋግጠዋል። ከነዚህ ውስጥ ለምሳሌ በ156 ዓ.ም በሰምርኔስ ከተማ ከግንድ ጋር ታስሮ የተቃጠለው ፖሊካርፕ የተባለው የሰማኒያ ስድስት ዓመት አዛውንት መጥቀስ ይቻላል።ፖሊካርፕ ከመገደሉ አስቀድሞ ጌታ ኢየሱስን እንዲክድ የቀረበለትን ዕድል አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ ብሎ እንደ ነበር በታሪክ ይወሳል።

[33] የተሪሬው ትምህርት ገጽ141።

"ይሼን ሁሉ ዘመን ክርስቶስን ሳገለግለው አንድም ቀን በድሉኝ አያውቅም፣ ታዲያ በዚህ ዕድሜዬ አዳኜንና ንጉሤን ምን አደረገኝ ብዬ እክደዋለሁ?"[34]

ቤተ ክርስቲያንን በስደትና በመከራ ብዛት ሊያሸንፋት እንዳልቻለ የተረዳው ሰይጣን ከተወሰኑ መቶ ዓመታት በኋላ ክፉ ሴራና ተንኮል ስላደረገባት ከዚያ በፊት በነበራት ጉልበትና ንጽሕና እንዳትቀጥል ቸጽዕኖ አድርጎባታል። በተለይም ከ306 እስከ 337 ዓ.ም ድረስ በሥልጣን ላይ በቆየው በቆስጠንጢኖስ ዘመን ክርስትና በመንግሥት የሚደገፍ ሃይማኖት መሆኑን ተከትሎ ቤተ ክርስቲያን በስደትና በመከራው ጊዜ የነበራትን አያሌ እንጡራ እሴቶች እንድታጣ ሆናለች። ምንም እንኳ ቄሳር ቆስጠንጢኖስን በተመለከተ በታሪክ ጸሐፊዎች ዘንድ እርስ በርሳቸው የሚጋጩ ታሪኮች ያሉ ቢሆንም፣ እኔ ግን ቄሳሩ፣ ለክርስትና ከፈየደው በጎ ነገር ይልቅ በተቃራኒው ያለው ነው ጎልቶ የሚታየኝ፣ እንዲያው አንዳንድ የታሪክ ጸሐፊዎች እንደሚሉት ከሆነ እስኪሞት ድረስ በክርስቶስ የማያምን ከመሆኑም በላይ በአረማዊ እምነቱ ነበር የሚታወቀው።[35] እስከ ዛሬም ድረስ ቁጥራቸው ቀላል የማይባል አብያተ ክርስቲያናት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥርዓቶች እንደ ሆኑ በመቁጠር ከሚገለገሉባቸው ሥርዓቶች አብዛኛዎቹ ከአረማውያን እምነት ተቀድተው በእርሱ በኩል ለቤተ ክርስቲያን የተበረከቱና የግድ ክርስቲያናዊ ትርጉም እንዲኖራቸው የተደረጉ መሆናቸው በግልጥ ይታያል። ለዚህም፣ ልዩ ልዩ በዓላትን፣ የካህናት አለባበስ፣ የእናትና የልጅ ክብርና አምልኮ፣ ቅርጻ ቅርጽና ልዩ ልዩ ስዕሎች. . . የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል።

ይሁን እንጂ በብዙ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ የተለየ ስፍራ ከሚሰጣቸው ጉባኤዎች አንዱ የሆነውና በ325 የተደረገው የኒቂያ ጉባኤ በራሱ በቆስጠንጢኖስ የተጠራና የተመራ መሆኑ ደግሞ እጅግ ግራ የሚያጋባ ነው። እንደሚታወቀው ጉባኤው አርዮስ የተወገዘበት ሲሆን፣ ከ288 እስከ 365 የኖረው የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ

[34] ይሼፉ ክርስቲያን ታሪክ። ክሐዋርያው የፊንስ እስከ የፊንስ ሱስ። ጽሁፉ ብክክቢ ተጻፈ። አሳታሚ፡ አ.አ.ይ.አም ሥነ ጽሑፍ ክፍል።

[35] አንዳንዶች ቀስጠንጢኖስ የፀሐይ አምላክን ያመልክ ነበር ይላሉ። ሆኖም ስለሰውየው ተጨማሪ ማብራሪያ ስማግኘት በሕይወት ታሪኩ ዙሪያ የተጻፉ ጽሑፎችን አንዲመረምሩ አመክራለሁ።

አትናቴዎስ አፈ ጉባኤ ሆኖ ያገለገለበት ነው። ይኼ፣ ይኼ ሲታይ እግዚአብሔር ምናልባት ሰውየውን እንደ ቂሮስ ለጊዜው ተጠቅሞበት ይሆን? ያሰኛል። እንዲያም ሆኖ ግን ክርስትና ለሮም የመንግሥት ይፋዊ ሃይማኖት ሆኖ የታወጀው ግን 378 እስከ 395 በሥልጣን ላይ በነበረው «ቴኦዶሲዮስ» በተባለው ቄሳር ዘመን ነው።

ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን ቤተ ክርስቲያን ከዓለማዊው መንግሥት ጋር የፈጸመችው ጋብቻ በምንም ዓይነት መስፈርት ተቀባይነት የሌለው ሕገ ወጥ ጋብቻ ነው የሚል እምነት አለኝ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በብዙ የዓለም ክፍሎች ስሟ እንጂ ኃይሏ እንደ ቀድሞ ያለመሆኑ ሚስጥር ምናልባት ከዚሁ ጋር የተገናኘ ይሆን? በአንጻሩ ከእነዚያ ዘመናት በኋላ ባሉት ዓመታት ቤተ ክርስቲያን የነገሥታቱ ቀኝ እጅ ሆና የታየችባቸው ነበሩ።

ባለንበት በሃያ አንደኛው መቶ ክፍለ ዘመንም ምንም እንኳ በቀድሞ ዘመናት በመንግሥት ዘንድ የነበራትን ኃይልና ጉልበት የተገፈፈች መስላ ትታይ እንጂ በአንዳንድ አገሮች የሚደረግባት ስውርና ግልጥ ጫና ባለፉት ሺ ዓመታት ከፈጸመችው ጽኑ ጋብቻ ቀጥሎ ያለ መሆኑ እሙን ነው። እንዲያውም ከማናቸውም ጊዜ ይልቅ ያለንበት ዘመን ለቤተ ክርስቲያን የፈተና ጊዜ ነው ማለት ይቻላል። ለዚህም በአንዳንድ የአውሮፓና የአሜሪካ አገራት እየሆነ ያለውን መጥቀስ ይቻላል። በእነዚህ አገሮች በሰብአዊ መብት፣ በዴሞክራሲና በግለሰብ ነፃነት ስም ከሚደረግባት ልዩ ልዩ ተጽዕኖ ምክንያት ዛሬ፣ ዛሬ ለማንም ሰው ኃጢአተኛ እንደ ሆነ መንገርም ሆነ የንስሃ ስብከት መስበክ የማትችልበት ደረጃ እየደረሰች ነው። በአንዳንድ አገሮችም አጋንንትን ገስጾ ከሰው ውስጥ ማውጣት እንደ ከባድ ሰብአዊ መብት መጣስ ተደርጎ ስለሚወሰድ ጽኑ ቅጣት ያስከትላል። በዚያ ላይ በባልና በሚስት፣ በልጅና በወላጅ፣ በአሠሪና ሠራተኛ. . . መኻል ያሉትን ግንኙነቶች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ለማድረግ ማሰብ ጨርሶ የማይታሰብ እየሆነ ነው። በማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ ቤተ ክርስቲያን ያላት ልዩነትና ተጽዕኖ ቀስ በቀስ እየተሸራረፈ ነው። ሌላው ቀርቶ በውስጧ «አለን» ለሚሉ አማኞች እንኳ እውነትና ጽድቅን መስበክ እንዳትችል በየቀኑ አዳዲስ እቀባዎች እየተደረጉባት ነው። ለዚህም

በቅርቡ በስዊድን አገር ስለ ግብረ ሰዶም ኃጢአትነት በመስበኩ ምክንያት ተከሶ በፍርድ ቤት ሲከራከር የነበረው መጋቢና የእንግሊዝ መንግሥት፣ ቤተ ክርስቲያን ግብረ ሰዶማውያንን በይፋ እንድታጋባ ያወጣውን ሕግ ለአብነት ያህል መጥቀስ ይበቃል። ለነገሩ ሰይጣን በዘመናት ሁሉ ራሱን በተለያየ ሁኔታ እየለዋወጠ የሚሠራ በመሆኑ ይኼም ጉዳይ ድንቅ ነገር አይደለም። ዳሩ ግን ቤተ ክርስቲያንን «ቤተ ክርስቲያን» የሚያሰኛት በላይዋ ላይ የተጠራው ስም ሳይሆን ተግባሯ ነውና ለቅዱሱ ቃል እውነት ስፍራ መስጠት እስከቻለች ድረስ በየትኛውም ዘመን የሚገጥማትን ተግዳሮት በአሸናፊነት እንደምታልፍ አያጠራጥርም።

በሌላኛው ገጽታዋ፣ ቤተ ክርስቲያን ለገጠርው መንግሥት መገበር እንቢ እንዳለች ዐመጸኛ መንግሥት ሆና ትታያለች፤ ሆኖም ከሰይጣን ሉውርና ግልጥ ጥቃት ራሷን ጠብቃ፣ አሸናፊ የምትሆንበት አቅም ተሰጥቷታል። ይህ ሲባል ግን ዐመጸኝነቷ ወይም አልታዘዝ ባይነቷ፣ ለዘመናት በምድር ሠልጥኖ በኖረው የሰይጣን መንግሥትና ሥርዓት ላይ እንጂ በሚታየው የሰዎች መንግሥት ወይም ሥርዓት ላይ እንዳይደለ መረዳት ያሻል። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም ከሁሉ በፊት ለዚህ ወሳኝ ፍልሚያ ብቁ እንድትሆን የሚያስችላትን ኃይል እንደሚሰጣት ቃል ገብቶላታል። ስለዚሁ ጉዳይ ሲናገርም፣ የገሐነም ደጆች እንኳ አይችሏትም ነው ያለው። በዚያው ክፍል እንደ ተመለከተው፣ ጌታ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያኑን የሚሠራው እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ በፍጹም ልባቸው አምነው በተቀበሉ ሰዎች ላይ እንጂ በ«ሃይማኖት» ስም «ክርስቲያን» በተሰኙ ሰዎች ላይ እንዳልሆነ እንገነዘባለን። ከዚህም በላይ ልዩ ልዩ የእግዚአብሔር ጥበቦች ለምድር ነገሥታት እንዲሁም በሰማያዊ ስፍራ ላሉ አለቆችና ሥልጣናት እንድትገልጥ የሚያስችላትን ልዩ ኃይል ሰጥቷታል።[36]

በሌላም በኩል ቤተ ክርስቲያንን በሌላ አገር እንዳለ ኤምባሲ ልናያት እንችላለን፣ በኤምባሲው ያሉ ዲፕሎማቶች በተለይም አምባሳደሩ

[36] ማቴ16:18። ኤፌ3:10

ከአገሩ ውጪ የሚኖሩበት ምክንያት፣ በማናቸውም ጉዳይ የአገሩን መንግሥትና ሕዝብ በመወከል ሲሆን፣ በተወከለበት አገር ሆኖ እንኳ የሚገዛው በላከው አገር ሕግ ነው። እንዲህ ሲባል ግን ለጊዜው የሚኖርበት አገር ሕግ በእርሱ ላይ ምንም ዓይነት ተጽዕኖ የለውም ማለት ግን አይደለም። ምናልባት ከኤምባሲው ቅጥር ውጪ ያሉ አንዳንድ በጎ ወይም ክፉ ሕጎችና ሥርዓቶች የተወሰነ ተጽዕኖ ሊያስከትሉበት ይችላሉ። ሆኖም በኤምባሲው ቅጥር ግቢ ውስጥ ሲገባ እነዚህ ሕጎች ምንም ዓይነት ተጽእኖ እንደሌላቸው ያውቀዋል።

ልክ እንዲሁ አማኞች ወይም የአማኞች ጎብረት የወል መጠሪያ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን፣ በዚህ ዓለም ለጊዜው ያለችው ከላይ የሆነውን የእግዚአብሔር አሳብ በምድር ለመከወን ነው። «አባታችን ሆይ» በሚለው ጸሎት «መንግሥትህ ትምጣና ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን» የሚሉት ሁለት ዓረፍተ ነገሮች ተከታትለው መከሰታቸውም የሚያስገነዝበን ይኼንኑ ነው፣ የሚል እምነት አለኝ። ደግሞም እያንዳንዱ አማኝ እስከአሁን በዓለም የሚኖርበት ምክንያት የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመፈጸም መንግሥቱን በምድር ለማስፋት እንደ ሆነ የታወቀ ነው። እርሱ ቤዛነቱንና የኃጢአት ስርየቱን አግኝቶ ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግሥት እንደፈለሰ፣ ሌሎችን የማፍለስ ታሪካዊ አደራ በላዩ ላይ ወድቆበታል።

ሆኖም በምድር ላይ ሲኖር ከዚህ ዓለም ሥርዓትና እምነት ጋር በየዕለቱ መጋጨቱ ግን አይቀርም። እርሱ ለዓለም እንደማይመች፣ ዓለምም ለእርሱ የተመቸች ስላልሆነች፣ የምድር ሕይወቱ በግጭት የተሞላ እንደሚሆን የተጠበቀ ነው። ጌታ ኢየሱስም «ዓለም ቢጠላችሁ ከአናንተ በፊት አኔን እንደጠላኝ አወቁ። ከዓለምስ ብትሆኑ ዓለም የራሱ የሆነውን ይወድ ነበር፣ ነገር ግን አኔ ከዓለም መረጥኳችሁ አንጂ ከዓለም ስላይደላችሁ ስለዚህ ዓለም ይጠላችኋል»[37] ሲል፣ ደቀ መዛሙርቱ በዓለም በሚመላለሱበት ጊዜ ስለሚገጥማቸው ጽኑ ተግዳሮት ተናግሯል። ይሁን እንጂ የዚህ ዓለም ገዢ የተባለው ዲያቢሉስ በአማኞች ላይ ሊያደርስ የሚችለው

[37] የሐ15:18-19።

ነገር ያን ያህል ሊጋነን የሚገባው አይደለም። አቅሙም ግፋ ቢል ሥጋን እስከ መግደል ድረስ ብቻ ነው። ኢየሱስ ከአብ ወጥቶ ወደ ዓለም እንደመጣ፣ ደግሞም ዓለምን ትቶ ወደ አብ እንደ ሄደ፣[38] አማኞችም ለዘላለም ከእርሱ ጋር ለመኖር አንድ ቀን ወደ እርሱ የመሄድ ተስፋ ተሰጥቷቸዋል። እስከዚያው ድረስ ግን በሌላ አገር እንዳለ እንደራሴ፣ በምድር ከብራቸው ተጠብቆ እንዲኖሩ ተወስኗል። በዚህ ዓለም ባለ ሥርዓት እንኳ ዲፕሎማቶች በምንም ጉዳይ ቢሆን ያለመከሰስ መብታቸው ተጠብቆ ነው የሚኖሩት። እንደራሴ ሆነው የተወከሉበት አገር መንግሥት ምናልባት ሊያደርግ የሚችለው፣ አገራቱን ጥለው እንዲወጡ ማባረር ብቻ ነው። በእርግጥ ይኼን ማድረግ ግን ለማንኛውም አገር መንግሥት ቀላል ነገር አይደለም።

ኢየሱስ የገለጣት የእግዚአብሔር መንግሥት ልክ እንደ ሰናፍጭ ቅንጣት ናት፤ የሰናፍጭ ቅንጣት ከዘር ሁሉ የምታንስ ብትሆንም፣ ባደገች ጊዜ ግን ትልቅ ዛፍ ሆና፣ ለብዙዎች መጠለያና ማረፊያ ትሆናለች። ልክ እንደዚሁ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደ ራሴ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን፣ ለሰዎች ሁሉ ሁነኛ መጠጊያ እንድትሆን በራሱ በእግዚአብሔር የተዘጋጀች ማረፊያ ጥላ ናት። የእውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን ክብር ባለበት ስፍራ ሰዎች በዚህ ምድር ካለው ፍርሃትና ስጋት አርፈው ከመኖራቸውም በላይ በምትመጣዋና ዘላለማዊት በሆነችው መንግሥት ተስፋ እንዳላቸው ስለሚገነዘቡ እነሱም ለሌሎች ማረፍ ምክንያት ይሆናሉ።

የእግዚአብሔር መንግሥት በየትኛውም ጊዜና ዘመን ሁሉ ተጽዕኖ ፈጣሪ ናት። እርስዋም ሴት በጥቂት መስፈሪያ ወስዳ በብዙ ሊጥ ውስጥ የሸሸገችውን እርሾ ትመስላለች። እርሾው ከሊጡ አንጻር ጥቂት ቢሆንም፣ ብዙውን ሊጥ ኩፍ በማድረግ ቅርጽንና መልኩን ይለውጠዋል። የመንግሥቱም ዜጎች በዚህ ዓለም ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊና ፖለቲካዊ ትውፊትና እሴት ሥርዓት ላይ የሚያስከትሉት ተጽዕኖ ጥቂቱ እርሾ፣ በብዙው ሊጥ ላይ ከሚያስከትለው ተጽዕኖ

[38] የሐ16:28።

ጋር የሚተካከል ነው። ቤተ ክርስቲያንም የእግዚአብሔር መንግሥት እንደራሴዎች ጎብረት እንደመሆኗ በእርሷ ዘንድ የሚመከር ምክርና የሚጸለይ ጸሎት፣ በቀረው ዓለም ላይ ዓይነተኛ ተጽዕኖ መፍጠር የሚችል ነው። «አናንተ የምድር ጨው፣ የዓለምም ብርሃን ናችሁ»[39]

የእግዚአብሔር መንግሥት በመንፈስ ቅዱስ የሆነ ደስታና ሰላም ናት እንጂ፣ በዚህ ዓለም በሚሆን መብልና መጠጥ ወይም የኑሮ መጠን የምትለካ አይደለችም። በመሠረቱ ሰው ወደዚህ ዓለም ሲመጣ ምንም ይዞ እንዳልመጣ ሁሉ ከዓለም ተለይቶ ወደመጣበት አፈር ሲሄድም ከዚህ ይዞ የሚሄደው ነገር የለም። ስለዚሁ ጉዳይ ሐዋርያው ጳውሎስ ሲናገር «ሰዕሰት የሚሆን ምግብና ዕብስ ካሰን አርሱ ይበቃናል» ነው የሚለው። በተረፈ «ኑርዩ ይበቃናል» ማለት ለለመደ፣ እግዚአብሔርን ከመምሰል ጋር ማትረፊያ እንደሚሆንለት ጨምሮ ያስረዳል። የዚያኑ ያህል ባለጠጋ ለመሆን አልመው የሚንቀሳቀሱ ሰዎች፣ ብዙ ጊዜ በጥፋትና በመፍረስ፣ ሰዎችን በሚያሰጥምና በሚያሰንፍ፣ በሚጎዳም በልዩ ልዩ ምኞትና ፈተና በወጥመድም ሲወድቁ ይታያሉ። ከዚሁ ጋር የሚከሰተው ገንዘብን መውደድ የኃጢአት ሁሉ ሥር በመሆኑ ዜጎች በጉዳዩ ካልተጠነቀቁ ከእግዚአብሔር መንግሥት አሳብ ርቀው ሊወድቁ ይችላሉ። አንዳንዶች ይኼን ሲመኙ ከሃይማኖት ተሳስተው በብዙ ስቃይ ራሳቸውን ወግተዋል።[40] ጳውሎስም በምድር ባፈሩት ሀብትና ባላቸው ቁሳዊ ነገር በዚህ ዓለም የብልጥግና መሰፈርት ተለክተው ባለጠጋ የተባሉትን አማኞች ሲመክር፣ ከሁሉ በፊት የትዕቢትን ነገር እንዳያስቡ ካስጠነቀቃቸው በኋላ፣ ደስ እንዲለን ሁሉን አትርፎ በሚሰጠን በሕያው እግዚአብሔር እንጂ በሚያልፍ ባለጠግነት ተስፋ እንዳያደርጉ ያዛቸዋል፣ እውነተኛውን ሕይወት ይይዙ ዘንድ ለሚመጣውም ዘመን ለራሳቸው መልካም መሠረት የሚሆንላቸውን መዝገብ እየሰበሰቡ መልካምን እንዲያደርጉ፣ በበጎ ሥራ ባለጠጎች እንዲሆኑ፣ ሊረዱና ሊያካፍሉም የተዘጋጁ እንዲሆኑ ያሳስባቸዋል።

[39] ማቴ5:13-16
[40] ፫ጢሞ6:1።

ሆኖም ለዚህ ዓለም ባለጠጎች ጉዳዩ ቀላል አይሆንም፣ ጌታ ኢየሱስም የእግዚአብሔር መንግሥት፣ በገንዘብ ፍቅር ለተነደፉ ወይም በዚህ ዓለም የባለጠግነት አሳብ ለሰጠሙ፣ የምትሆን ስፍራ እንዳልሆነች አስታውቆናል። ደግሞም ገንዘብ ላላቸውና በገንዘባቸው ለሚታመኑ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት እንዴት ጭንቅ እንደ ሆነና ባለጠጋ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከሚገባ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢሾልክ እንደሚቀለው አስረግጠ መናገሩ፣ ነገሩ ምን ያህል አሳሳቢ እንደሆነ የሚያሳይ ነው። በወቅቱ ደቀ መዛሙርቱም ይኼን ሲሰሙ እጅግ ደንግጠው «ታዲያ ማን ሊገባ ይችላል?» እስከ ማለት ደርሰው ነበር። እርሱም «ሰሰው የማይቻል ለእግዚአብሔር ይቻላል» በማለት ነበር የመለሰላቸው። ከዚህ አንጻር አማኞች በምድር በሚኖሩበት ዘመን፣ ለስለኑሮአቸው ብዙ መጨነቅ የለባቸውም። ኢየሱስም ማንም ሰው በሕይወቱ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባውን ነገር ሲናገር «አስቀድማችሁ ጽድቁንና መንግሥቱን ፈልጉ፣ ሌላው ሁሉ ይጨመርላችኋል» ነው ያለው።[41]

ስለዚህም የቱንም ያህል ከባድና አስቸጋሪ መስሎ ቢታይ እንኳ አማኞች ስለእግዚአብሔር መንግሥት ተገቢ ዋጋ ሊከፍሉ ይገባል። በእርግጥ ኢየሱስ ለጉዳዩ አጽንኦት ለመስጠት ወደ ለደቀ መዛሙርቱ የነገራቸው ሁለት ምሳሌዎችም የሚያስገነዝቡት ይኼንኑ ነው።[42] ከዕለታት አንድ ቀን፣ አንድ ገበሬ በውስጡ የተሸሸገ ብዙ ሀብት ያለበትን የእርሻ መሬት አገኘ፤ ወዲያው ዘመኑን ሁሉ ያፈራውን ሀብት በሙሉ ሽጦ መሬቱን ገዛ። አንድ ነጋዴ ደግሞ በገበያ መኻል ውድና ንጹሕ የሆነች ዕንቁ አገኘ፤ እርሱም ዕንቁዋን ለመግዛት አስቦ ሀብቱን በሙሉ ሸጠ፤ ገዝቶም የራሱ አደረጋት። ልክ እንዲሁ ማንም ሰው መንግሥተ ሰማይን ከፈለገ፣ አለኝ ከሚለው ሁሉ አብልጦ ይፈልጋት። እርሷንም የራሱ ለማድረግ ምንም ነገር መክፈል ካለበት ይክፈል። ልብ በሉ፣ ይህን ያለው ኢየሱስ ነው።

[41] ማቴ6:33።
[42] ማቴ13:44-46።

ምዕራፍ ፮

(፲፱) ማማሥግት ትምጣ!

ስምህ ይቀደስ፣ መንግሥትህ ትምጣ፣ ፈቃድህ
በሰማይ እንደሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን

ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ያስተማረውና «አባታችን ሆይ» የተሰኘው ጸሎት፣ ፍጹም የተለየ ጸሎት ነው። በአንድ በኩል በማንም አማኝ ጸሎት ውስጥ ሊካተቱ የሚገባቸው መሠረታዊ አሳቦች የታጨቁበት በመሆኑ፣ እንደ ጸሎት ርዕስ ሊታይ የሚችል ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ የጸሎተኛው ሕይወት ምን መምሰል እንዳለበት የሚያመለክት ነውና የአማኝ ሕይወትና ኑሮ መቃኛ ነው ለማለት ያስደፍራል። ከዚህ በተረፈ ጸሎቱ፣ በአራት ዋና፣ ዋና ክፍሎች የተከፈለ ሆኖ፣ አያንዳንዳቸው የየራሳቸው መልዕክት እንዲኖራቸው ሆነው እንደ ተዋቀሩ ይታያል። በዚሁ መሠረት በጸሎቱ የመጀመሪያ ክፍል፣ ጸሎት ወደማንና ለማን መጸለይ እንደሚገባ ሲያመለክት ጸላዩ ሰው፣ ጸሎቱ የሚደርስበትን ስፍራና ጸሎቱን የሚቀበለው ለእርሱ ማን እንደሆነ በአንክሮ እንዲያስተውል የሚያደርግ ነው። በሁለተኛው የጸሎቱ ክፍል መቼም ጊዜ ጸሎት ከእግዚአብሔር ፍላጎት አንጻር እንዴት መቅረብና ምን መምሰል እንዳለበት የሚያስረዱ ጠንካራ አሳቦች የተካተቱበት ነው። ሦስተኛው የጸሎቱ ምዕራፍ፣ ጸሎት ከሰው መሠረታዊ ፍላጎት አንጻር እንዴት ባለ ሁኔታ መቅረብ እንዳለበት የሚያሳስቡ አሳቦችን አቅፎ ይዟል። በዚህ ድንቅ ጸሎት መደምደሚያም ማንም ሰው፣ ለጸሎት በሚንበረከክበት ጊዜ ሁሉ ሊያስታውሳቸውና እንደ የእምነት አቋም መግለጫ ረገጥና ጫን ብሎ ሊያውጃቸው የሚገቡ ጉዳዮች ይገኛሉ።

ከዚህ መጽሐፍ ዓላማ አንጻር የእኛ ትኩረት የሚሆነው፣ በጸሎቱ ሁለተኛ ክፍል ውስጥ የተዘረዘሩት ጉዳዮች ናቸው። በተለይም «መንግሥትህ ትምጣ» የሚለውን አሳብ የመጽሐፉ ዋና መንደርደሪያ

በመሆኑ ከሌሎቹ ይልቅ በመጠኑ ይዳሰሳል። ይሁን እንጂ ከዚህ ጸሎት ጋር ተያይዘው ያሉት ማለትም «ስምህ ይቀደስ አና ፈቃድህ በሰማይ አንደ ሆነች፣ አንዲሁም በምድር ትሁን» የሚሉት የጸሎቱ ክፍሎች «መንግሥትህ ትምጣ» ከሚለው ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ያላቸው ግንኙነት ጥብቅ በመሆኑ እነርሱን በተለይ ነጥለን ማየት አንችልም።

እስቀድሞ «ስምህ ይቀደስ» የሚለውን የጸሎቱን ክፍል እንኳ ብንመለከት አሳቡ *«በእኔ ሕይወት ንጽሕና ወይም ቅድስና የአንተ ሰም በዓለም ተቀድሶ /ተለይቶ ይታይ»* ማለት፣ ወይም «ስሰአርሱ መከራ ዕትቀበሱ አንጂ በአርሱ ዕታምኑ ብቻ አደደለም. . . *እንደሚል ስለስምህ መከራ በምቀበል ጊዜ ከአንተ ምንም ነገር ሊነጥለኝ እንደማይችል ዓለም ሁሉ ይወቅ»* ማለት ሊሆን ይችላል። ወይም ደግሞ *«በእኔና በሌሎች በኩል በስምህ የሚደረግ ማንኛውም ዓይነት ታምር በዚህ ዓለም "አማልክት" ተብላሉት ሁሉ አንተ ልዩ አምላክ መሆንህ ይታወቅ»* የሚል ትርጉም ሊኖረው ይችላል። ይኼ ዓይነቱ ጸሎትም በመጣችው የእግዚአብሔር መንግሥት ማለትም በቤተ ክርስቲያን በኩል ዕውን እንደሚሆን ለሚጠበቀው የሕይወት ልክ የተገባ በመሆኑ «ስምህ ይቀደስና መንግሥትህ ትምጣ» የሚሉት ክፍሎች ምን ያህል የተሳሰሩ እንደሆኑ ያሳየናል።

«ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች፣ አንዲሁ በምድር ትሁን» የሚለው የጸሎቱ ክፍልም በመጣችው መንግሥቱ በኩል በምድር ላይ ስለሚሆነው አግዛዝ የሚመለከት እንደ መሆኑ «መንግሥትህ ትምጣ» ከሚለው አሳብ ተነጥሎ የሚታይ አይሆንም። እንዲያውም ጸላዩ ሰው እዚህ ክፍል ላይ ሲደርስ፣ እግዚአብሔር በማን በኩል ፈቃዱን ሊፈጽም እንደ ወደደ ቆም ብሎ እንዲያጤን ያደርገዋል። ከዚህ ቀደም በመጠኑ እንደተመለከትነው እያንዳንዱ አማኝ ወይም ቤተ ክርስቲያን አሁን በምድር ያሉት በሰማይ ያለውን የእግዚአብሔር ፈቃድ ለመፈጸም የሚያስችላቸው የእንደራሴነት ሥልጣን ከክርስቶስ ስለተቀበሉ ወይም ስለተሾሙ ነው። ይኼም የጸሎት አሳብ ከዚህ መሠረታዊ ጉዳይ ጋር በቀጥታ የተያያዘ ነው። ኢየሱስም በአንድ ወቅት «አብ አንደላከኝ እኔ ደግሞ አልካችኋለሁ» ማለቱን እናስታውሳለን። በእርግጥ ኢየሱስ ራሱ ከአብ ተልኮ እንደመጣ በተደጋጋሚ መናገሩ የአማኞች ኃላፊት ምን

ያህል ታላቅ እንደሆነ የሚያሳይ ነው። ስለዚሁ ጉዳይ፣ 21 ምዕራፎች ባሉት የዮሐንስ ወንጌል ላይ ብቻ፣ ከ25 ጊዜ በላይ ተጽፎ ይገኛል።

በዚህ ምክንያት ማንም «አባታችን ሆይ» የሚለውን ጸሎት የሚጸልይ ሰው፣ በተለይ «መንግሥትህ ትምጣ» በሚለው ቁ.ሎቱ ክፍል ላይ ሲደርስ በናፍቆት የሚቃትት መንፈስ እንደሚያስፈልገው መስሎ ይታያል። በክፍሉ እንደተመለከተው ይኼ ዓይነት መቃተት የሚገኘው ግን ጸላዩ ሰው፣ በልቡ መንግሥት አልባነት ወይም አሁን ባሉትም ሆነ በዘመናት መኻል ባለፉት የምድር መንግሥታት ያልረካ ወይም ሌላ የተሻለ መንግሥት ተስፋ የሚያደርግ እንደሆነ ብቻ ነው። በመሆኑም ይኼ ዓይነቱ ጸሎት፣ ከእውነተኛ የልብ መቃተትና ናፍቆት እንጂ ከሃይማኖተኝነት መንፈስ ብቻ የሚመነጭ ሊሆን አይችልም። ከዚህ አንጻር ኢየሱስ «መንግሥትህ ትምጣ» ብላችሁ ጸልዩ ሲል፣ በአንድ በኩል በእርሱ መወለድ ወደምድር የደረሰችው መንግሥቱ በየስፍራው እንድትስፋፋ፣ ብርቱ ተጽዕኖ እንድትፈጥርና ተግባሯን በአግባቡ እንድትፈጽም እንድንግልድ ሊያሳስበን፣ በሌላ በኩል ደግሞ በዳግም ምጽአቱ የምትመጣዋ መንግሥት ፈጥና ዕውን እንድትሆን ያለንን ናፍቆት እንድንገልጥ ወዶ ይመስለኛል። በእርግጥ የመንግሥቱ ጉዳይ እግዚአብሔር ለሰው ከሰጠው ተስፋ ሁሉ እጅግ የሚያጓጓ ነው። በተለይ እኛ ባለንበት በዚህ ዘመን ስለዚያች መንግሥት ማሰብ በራሱ ምንኛ የሚያጽናና ነው።[43]

እግዚአብሔር በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ለሚያምኑ ብቻ የማይናወጥ ዘላለማዊ መንግሥት እንደሚያወርሳቸው ተስፋ ሰጥቷል። ይህቺም መንግሥት ምድራዊ ሳትሆን ሰማያዊት ናት። በምድር በኖሩበት ዘመን እርሱን ያከበሩ ሁሉ አንድ ቀን በምትመጣዋ መንግሥት ካህናት ሆነው ያገለግሉታል። ከክርስቶስም ጋር ለዘላለም ይነግሣሉ። ምድራዊ መንግሥታት ሁሉ ካለፉ በኋላ የእግዚአብሔር መንግሥት በዓለም ላይ ትመሠረታለች። ደግሞም የዚህ ዓለም መንግሥታትና

[43] ማቴ6:9-13። ሉቃ11-13።

ሕዝቦች አንዱ በአንዱ ላይ መነሣቱም የእግዚአብሔር መንግሥት መቅረብ ዋነኛ ምልክት ሆኖ ተጠቅሷል።

ልብ በሉ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ ባሕር የተጣለ መረብን ነው የምትመስለው፣ ይህቺም መረብ በባሕር ውስጥ ካገኘችው ዓሣ በየዓይነቱ የምትሰበስብ ናት፣ በሞላች ጊዜም አሣ አጥማጆቹ መረቡን ወደ ዳር ጎትተው ያወጡታል፣ ጥሩ፣ ጥሩውንም መርጠው ባዘጋጁት ዕቃ ያስቀምጣሉ፣ የማይጠቅመውን ግን መልሰው ይጥሉታል። በዚህ ዓለም መጨረሻ የሚሆነው እንዲሁ ነው። የእግዚአብሔር መላዕክት መጥተው ጻድቃንን ከኃጢአተኞች ይለይዋቸዋል። ጻድቃኑን ወደ ዘላለም ሕይወት፣ ኃጥአኑንም ወደ ዘላለም የእቶን እሳት ይጥላሉ። በዚያም አሰቃቂ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል። በዚህ ዓይነት በመጨረሻው ዘመን እግዚአብሔር ራሱ በመንግሥቱ ልጆችና በዚህ ዓለም ልጆች መኻል አስደናቂ መለየትን ያደርጋል።[44]

ከዘሪው የመጀመሪያ ምሳሌ ቀጥሎ ባለው ሌላኛው ምሳሌው ኢየሱስ በመንግሥቱ ውስጥ ሰይጣን አሾልኮ ስለሚያስገባቸው ክፉ ዘሮች ተናግሯል። እነዚህ ክፉ ዘሮች በባሕሪያቸው ልክ እንደ እንክርዳድ ናቸው። ለመብል ያማይሆኑ፣ ደግሞም የሚጎዱ። ምንም እንኳ እንክርዳድ እስከ ጊዜው ድረስ እውነተኛ ዘር መስሎ ቢታይም፣ ፍሬ በያዘ ጊዜ በአቋሙ ተለይቶ መታወቁ አይቀርም። እነዚህም ሰዎች እስከ ጊዜው ድረስ መልካም ፍሬ የያዙ መስለው ይታያሉ። እንዲያውም እነርሱን ከእውነተኛዎቹ ለመለየት እስከማይቻል ድረስ ራሳቸውን ይሰውራሉ። ሆኖም ለእውነተኝነታቸው ማረጋገጫ የሚሆን ፍሬ ማፍራት አይችሉም። ስለዚህም ለጊዜው ነው እንጂ ማንና ምን እንደ ሆኑ መታወቃቸው አይቀርም። ይሁን እንጂ ቢታወቁም እንኳ እስከ መከር ጊዜ፣ ማለትም ክርስቶስ ዳግመኛ እስኪመጣ ድረስ ማንም እንዲነቅላቸው አልተፈቀደለትም። መጨረሻው ሲሆን ግን፣ የመኸሩ ባለቤት ራሱ አጫጆች ልኮ ስንዴን ከእንክርዳድ እንደሚለይ እንዲሁ እውነተኞቹን ከሐሰተኞቹ ይለያቸዋል።

[44] ማቴ24:7። ማቴ13:47-50።

በሁለቱ የዘረው ምሳሌዎች እንደተመለከተው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት ዕድል ከተሰጣቸው ሰዎች መኻል አንዳንዶቹ ዕድሉን ሊያጡ የሚችሉበት አጋጣሚ ሊኖር እንደሚችል ነው።[45] ሰዎች ዕድሉን እንዲያጡ ከሚያደርጓቸው ነገሮች ውስጥ፣ ዓለምን መውደድ፣ የሥጋ ምኞት ዋናዎቹ ሲሆኑ፣ በዚህ ሁሉ ደግሞ የክፋው የሰይጣን ተጽዕኖ መኖሩ አይታበልም። እንደሚታወቀው ሰይጣን ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ሰዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት ተስፋ በማቃለል በዚህ ዓለም አሳብ እንዲዋጡ ሲያደርግ ነው የኖረው። ይኼ ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ዘመናት ልዩ፣ ልዩ የስህተት አሠራሮች ወደ መንግሥቱ ልጆች አሹልኮ እያስገባ በእግዚአብሔር የሚያምኑ ሰዎችን ለማሳት ሲተጋ እንደነበር የተገለጠ ነው።[46]

በመሠረቱ ገና ወደ ፊት የምትመጣው የእግዚአብሔር መንግሥት፣ በምንም ዓይነት ከመጣችው ተለይታ የምትታይ አይደለችም። ጌታ ኢየሱስም ስለመጣችው መንግሥት ባስተማረ ጊዜ ሁሉ እርሷን ቸል ብሏት አያውቅም። እንዲያውም ከጌታ ትምህርት አንጻር የመጣችው ለምትመጣው መሠረት እንደሆነች ነው የምንገነዘበው። የምትመጣው የእግዚአብሔር መንግሥት በክርስቶስ ዳግም ምፅአት ጊዜ ወደ ፊት የምትገለጥ ናት። በእርግጥ እርሷ በምትገለጥበት ወራት በምድር አዲስ ሥርዓት ይዘረጋል። የዚያች መንግሥት መሪ መሲሁ ኢየሱስ በመሆኑ እውነት፣ ፍቅር፣ ሰላምና ፍትህ የመሳሰሉ ውድ ነገሮች በምድር ይሰፍናሉ። እስከዚያው፣ በመጣችዋ እየኖርን፣ የምትመጣዋን እንናፍቃለን። «መንግሥትህ ትምጣ» እያልን እንቃትታለን።

[45] ዕብ6:4-8። 10:26-39።1ኛ ቆሮ6:9። ወደስ በመጸፃፉ የእግዚአብሔርን መንግሥት አንጻያወርሱ አታውቁምን፣ አትሳቱ. . .።

[46] ማቴ13:1-35።

ኤሎሄ፣ ኤሎሄ፣

መንግሥትህ ትምጣ

ይኼን መጽሐፍ ጽፌ ለመጨረስ እየተጣደፍኩ በነበርኩበት ሰሞን፣ የአረቡ ዓለም ሕዝቦች፣ ሳይጠበቅ የገዛ መንግሥቶቻቸውን አምርረው መቃወማቸውን ተከትሎ በተቀሰቀሰ ዐመጽ፣ አገራቱ እየተተራመሱ ሲሆኑ፣ የተወሰኑ መሪዎችም ቀስ በቀስ ሥልጣናቸውን እየለቀቁ እንደሆኑ እየተሰማ ነው። ይገርማል! ከመሪዎቹ አንዳንዶቹ ለሠላሳና አርባ ዓመት ተንሰራፍተው ከቆዩበት ሥልጣን መፈናቀላቸው ሳያንስ አገራቸውን ጥለው እስከ መሰደድ ደርሰዋል። ሆኖም ነገሩ ባለፉት ዘመናት በዓለማችን በተደጋጋሚ የታየ በመሆኑ፣ የአንድ ሰሞን የዜና ፍጆታ ከመሆን ያለፈ ብዙ የሚያስደንቅ እንደማይሆን እገምታለሁ። ግና ብዙ ጊዜ ሲሆን እንደሚታየው፣ በወረዱት እግር ተተክተው ሥልጣን ላይ የሚወጡት መንግሥታት ሕዝበኞቻቸው የሚያስቡትን ያህል ሆነው አይገኙም፣ ስለዚህ የተሻለ መንግሥት ፍለጋ እንደገና ዐመጽና ብጥብጥ ይሆንና ደግሞ ይኼኛው ወርዶ፣ ሌላኛው ይተካል። የሥልጣን ውደቱም እንዲህ ከአንዱ ወደ ሌላው ይተላለፋል። እንደው ለመሆኑ፣ በዚህ ጉዳይ የሰዎች ጥማትና ፍላጎት ፍጹም የሚረካው መቼ ይሆን?

በአንጻሩ ያለንበት ዘመን፣ ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ዋስትና የሌለበት መስሎ ይታያል። ሁሉ ነገር መገመት እስከማይቻል ድረስ እጅግ ግራ የሚያጋባ ሆኗል። አንዳንዴማ፣ ምድር ፈጣሪና ባለቤት የሌላት እስከትመስል ድረስ ምስቅልቅል ብላ ትታያለች። ይኼ ደግሞ የወደፊቱን የበለጠ አስፈሪ አድርጎታል። በዚያ ላይ ብዙ ሰው የችግሩ እንጂ የመፍትሔው አካል ሲሆን አይታይም። *«ይህ የሆነው፣ እንዲህ ስለሆነ ነው»* የሚለው የእያንዳንዱ ሰው መላምት፣ ከሌላኛው ጋር እየተላተመ ያለሥርዓት፣ በደመ ነፍስ ይተማል።

ተመልከቱ! ሰው ሁሉ ተጠባብቆ ነው የሚኖረው። አንዱ ሌላውን ከቶ አያምንም፤ መታመን የሚባል ነገርም የለም። ውሸት ሠልጥና፣ እውነት ተረግጣለች። ከስንት አንዱ ቃሉን ይጠብቃል፤ የወረቀት ውልና ፊርማ ዋጋው ወርዷል። አባይ ሚዛን በዝቷል። ስለዚህ ዋናው ነገር ቀሎ፣ ተራው እጅግ ገዝፏል። ሕይወት ረክሶ፣ ኑሮ ተወዷል። ቴክኖሎጂ ፍጥነት ቢጨምርም፣ ሰዉ እረፍት የለውም። ከአግረኛው ባለ መኪናው ይቸኩላል፤ በእግሩ የተጓዘው ቀድሞ ሲደርስ፣ ባለ ተሽከርካሪው ያረፍዳል። ከድሀው ይልቅ የባለጠጋው ችግር በርክቷል፤ ከመሃይሙ፣ የተማረው ፈሪ ሆኗል።

ሚድያው ርካሽ በሆኑ ድርሳናት ተሞልቷል፤ ቴሌቪዥኑ በእርኩሰት፣ ሬድዮኑ በማጋነን ተከፍኗል፤ መልካም ነገር ዜና አይሆንም፤ የሚሰማው ሁሉ ግድያ፣ አሰቃቂ አደጋ፣ ዝርፊያ፣ አሉባልታ፣ ጸያፍ ወሬ ነው፤ ጋዜጣው ደጎና ነገር አያወራም። የሚጸፈው ባዶ፣ ለነፍስ ክሳት፣ ለሥጋ ሕመም ነው። ዓይን የሚያየው ይከረፋል፤ ጆሮም የሚሰማው ይገለማል።

ሃይማኖት በሽቃጮች እጅ ወድቋል፤ የሰው ፍልስፍና ነግሷል። ግና ምን ያደርጋል? ብዙዎች ሊሰሙ የሚሰለፉት እሱኑ ነው። ለጽድቅ የሚሆን አቅም ጠፍቷል። ነብያቶቹ ሲጠነቁሉ፣ መምህራኑም የተረት አባት ሆነዋል። ቀሳውስቱ ንዋያተ ቅዱሳኑን፣ መጋቢዎቹም ብሩን ይሰርቃሉ። ሃይ ባይ፣ ቀጪ ተቆጪም የለም። ከጤነኛው በሽተኛው በዝቷል፤ «የባለመድሃኒት ያለህ» ባዩን የሚሰማው የለም። እዚህም፣ እዚያም እሪታ፣ ኡኡታ፣ እሸሽ ነው። ራሱን እንጂ ሌላውን የሚያስታምም አይገኝም። አዋቂው ምንም እንደማያውቅ ሆኗል፤ ሐኪሙ ራሱ ታሟል፤ ታጣቂው ልቡ ርዷል፤ በላተኛው ከስቷል። በሽታው ብዙ፣ መድሃኒቱ ግን ምንም ነው። ወንድ ልጅ፣ እንደ ሴት ያምጣል፤ ነገ ሲታሰብ ጭንቅ ነው።

የዓለም ፖለቲከኞች ቃላቸውን አይጠብቁም፤ ዘወትር ሕዝባቸውን እንደዋሹ ይኖራሉ። እጃቸው በንጹሐን ደም ቆሽሾ፣ ከአንደበታቸው አሰልቺ ውሸት ሞልቶ ይፈሳል፤ ሐፍረት የሚባል ነገር አያውቁም። በየዕለቱ በሚድያ ብቅ እያሉ፣ የማይነጥፍ ሰበብ ይደረድራሉ።

ማንንም እንዳይሰሙ ጆሮአቸው በትዕቢት ተለስኖ፣ ልባቸውን የኩራት ስብ ዘግቶታል። አንዳንዶች ይኼን ይጠየፋሉ፤ አምርረው ተቆጥተው ለትግል ይሽምቃሉ፤ ግን ምን ያደርጋል? ሥልጣን ላይ ሲወጡ የቀደሙትን ስህተት አሻሽለው ይደግሙታል። ለብቻቸው ያገኙት ነፃነት፣ መላው ሕዝብ እንዳገኘ ይደሰኩራሉ፤ እነርሱ የጠገቡ ዕለት *"የሕዝቡ ችግር ቁንጣን ነው"* ይላሉ። ከሰው እንደተፈጠሩ ቶሎ ይረሳሉ፤ ራሳቸውን ከአምላክ ጋር ያስተካክላሉ፤ ቀድሞ የነበረው ምን እንደገጠመው ዘንግተዋል። ተራ ሰው እንደነበሩ እንደሆኑ ማሰብ አይፈልጉም። ዱሩን ገደሉን ሸሽተው፣ በሙስና ጫካ መሽገዋል፤ ትናንትን የሚያስታውሳቸው ጠላታቸው ነው፤ የሚገስጻቸውን ያስራሉ «ተዉ» የሚላቸውን ይገድላሉ፤ የእነርሱ ሰሞን ደርሶ፣ ደግሞ ትቢያ እስኪሆኑ ድረስ ሁሌም እንዲሁ ናቸው። አምባገነን፣ ፈሪ፣ ውሸታም፣ ጨካኞች፣. . . ስለእነርሱ ማሰብ ልብ ያደክማል።

ብርሃን የለም፤ ዓይን ቢጓጉ አይታይም፤ በጠራራ ፀሐይ ጨልሟል። በረዶው እንደ እሳት ይፋጃል፤ ዝናብ ሞልቶ ተርፎ ምድሩ ደርቋል። ዓተራውና ሱቁ ሙሉ ሆኖ፣ ሰዉ በጠኔ እያለቀ ነው፤ ራስ ወዳድነት፣ ግለኝነት፣ ስስት፣ ንፉግነት፣ አጉል ብልጠት. . . የዚህ ዘመን ፋሽን ሆኗል። ከራሱ አልፎ ስለጎረቤቱ ግድ የሚለው ከስንት አንዱ ነው፤ ግብዝነት ተንሰራፍቷል። በየቀኑ በርካታ ቤተሰብ በቀላል ምክንያት እንደ ዘበት ይፈርሳል። ድህነት ስሩን ሰዷል። ህፃናት፣ ሴቶች፣ ወጣቶችና አረጋውያን በየጎዳና ተበትነዋል። ስለ እነርሱ የሚገደው፣ ዞሮ የሚመለከታቸው ከቁጥር የማይገባ ነው። ጉልበታቸው የሰለለ፣ አጥንታቸው የገጠጠ ረሀብተኞችን በቴሌቪዥን መስኮት ማየት ብርቅ ነገር አይደለም። በዚያው መስኮት የ«ባለጠጋ» ውሾችና ድመቶች የቅንጦት ኑሮ ይታያል፤ ሆኖም ማንም ልዩነቱ ሳያሳስበው እንደ ቀላል ነገር ስቆ ያልፈዋል። ግድያ ዝርፊያ አስገድዶ መድፈር፣ ተበራክቷል። ሙስና እንደ ሰደድ እሳት ይፈጥናል። ግፍ ማድረግ ቀላል ሆኗል፤ እውነት ወድቃ ተረግጣለች፤ ፍትህና ፍርድ ጎድሏል። ንጹሐን ተፈርዶባቸው፣ ክፉዎች በሰላም ይኖራሉ። ጻድቁ ተገፍቶ ኃጥኡ ይሾማል፣ ይሸለማል።

የብዙ ሰው ክብሩ ነውሩ ነው፤ የቆመበት ላይ የቆመው ሌላውን ደፍጥጦ ነው፤ እግሩ በደም ጨቅይቷል፤ ጉሮሮው በሐቅ ታንቋል፤ ሳይከረክረው ያወራል፤ ሳይነረብጠው ይዘላል። ውጪው ደምቆ፣ አምሮ ተውቦ፣ ውስጡ ነትቦ እጅግ ነትሟል። ቀን ነው የሚጠብቀው፤ ትንሽ ነፋስ ብቻ ነው የሚበቃው። ላይ ላዩን ኃይለኛ ነው፤ የቀበረው የለም እንጂ፣ እሱስ ከሞተ ቆይቷል። ግን ተስፋ አይቆርጥም ምንም ላያውቅ ይማራል፤ የሚደርስበትን ላያውቅ ጠዋት ተነሥቶ ይጓዛል። ፈቀቅ ላይል ይከንፋል። መቼ ይሆን የሚሰክነው?

እርቃን የማይሸፍን ጨርቅ፤ ውበትና ሙቀት የሌለው ልብስ፤ እንቅልፍ የሌለው ምቹ አልጋ፣ የማያሳርፍ መኝታ፤ የማያጠግብ ምግብ፤ የማያረካ መጠጥ፤ ነዋሪ አልባ ሰፊ ቤት፤ መግዛት የማይችል ብዙ ብር፤ ከፈውስ የማይተዋወቅ መድሃኒት፤ የሚያውክ ሙዚቃ፤ የማይበረክት ደመወዝ፤ የማያረካ ሥራ፤ ኑሮን ፈቀቅ የማያደርግ ዕድገት፤ እረፍት የሌለበት ሥልጣኔ፤ ከጽድቅ የራቀ ሃይማኖት፤ ከእውነት የተጣላ እምነት፤ ባዶና ከንቱ ሥርዓት፤ የረሀብ አድማ የመሰለ ያም፤ የማይሰማ ጸሎት፤ የሚያታክት ኑሮ፤ እርባና ቢስ ሕይወት፤ የሚያጭበረብር ብርሃን፤ ዝብርቅርቅ ያለ ቀለም፤ ግራ የተጋባ ዓለም።

ዛሬን የሚያደንቅ የለም፤ ድሮን ዛሬ የኖረ ባይገኝም፣ ሁሉም ይናፍቃታል፤ ከነገ ደህና ነገር የሚጠብቅ ጥቂት ነው። አፍ ጮኽ ባይናገርም በሁሉ ቤት ምጥና ስቃይ ነው። መቼ ይሆን ፍጻሜው? ለዚህ ሁሉ ገደብ የሚበጅለት? መልስ የሌለው ጥያቄ፤ የማይፈታ እንቆቅልሽ፤ ተስፋ የሚያስቆርጥ አሳብ። እንደ ገደል ማሚቶ ደርሶ የሚያስተጋባ። ናላ የሚያዞር ድብብቆሽ፤ ምንም ላያገኙ መባከን። ላይሰወሩ መደበቅ፣ በየስርቻው መወሸቅ።

ኤሎኼ፣ ኤሎኼ፣ መንግሥትህ ትምጣ! አሜን!

ክፍለ ሐሳብ ፪

ፍጹም መንግሥት

የብሉይ ኪዳን ታሪኮች በአጭሩ